ያደስናል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ቃሉ በመጀመሪያ መጥቶ ከዚያም ሕይወት ይከተላል፤ ውጤቱ ግን ያው አንድ ነው፡፡ "ወዲያውም ዶሮ ለሁለተኛ ጊዜ ጮኸ፡፡ ጴጥሮስም ... የኢየሱስ ቃል ትዝ አለው፤ ከዚያም ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ" (ማር 14፥72) (አመት)፡፡ የእግዚአብሔር ቃል የመማረክ ኀይል የሌለበት ቤተ ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን አይደለችም፡፡ ነገር ግን ቃሉ የመንጻትና የመታደስ መሣሪያ ነው፡፡ ይህን ብቻ ልብ ብንል፤ ሥራውም እንዲሠራ ብንፈቅድ፤ ላይሳካልን ቢችልም፤ ብዙ ሳንቆይ የፈጸምን ስለ መሆናችን ትዝ ይለናል፡፡

እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን፤ አካል የሆነችው፣ ባሕርይዋን ሕይወቷ ከሆነው ከእርሱ ሙሉ በሙሉ በመውሰድ፣ አጋር ሙሽራው ለመሆን የምትዘጋጅበት ቀን ይመጣል፡፡ አካሉ ሆና ሙሉ በሙሉ ከእርሱ ሙላት ስለ ደረሰች (4፥13)፤ በመጨረሻ "ጉድፍ ወይም የፊት መጨማደድ የሌለባት ...ክብርት ቤተ ክርስቲያን" ሆና ወደ እርሱ ትቀርባለች (5፥27)፡፡ ከእርሱ የተነሣ እንደ እርሱ ቅዱስ ስለ ሆነች ለእርሱ ቅድስት ትሆናለች፡፡ ክብሩን ገልጻለች፡፡ የኀጢአት ጠበሳ፣ ያለ ዕድሜ ጫና፣ ጊዜ ምንም ሳይባክንባት፣ ያለ ምንም ዐይነት እንከን፤ ያለ ጉድፍ፣ ቅድስት ሆና ወደ እርሱ ትቀርባለች፡፡ ክርስቶስ በቃሉ አማካይነት ሰይጣን ወይም ኢጋንንት፣ ሰዎች ወይም መላእክት ... በእርሷ ላይ ክስ እንዲያመጡ አንዳች ሥፍራ አልተወላቸውም፡፡ በእርሷ፣ አሁን፣ ሁሉም ዐዲስ ነው፣ ሁሉም የእግዚአብሔር ነው፡፡ ይህ የተባረከ ውጤቷ ከሆነ፣ ታዲያ እኛ ዛሬ እግዚአብሔር ቃሉን ለእኛ የሚናገርበት አድርገን መያዝ የለብንምን?





# ምዕራፍ ሰባት

## በፍቅር መገንባት

ከሰማያዊ ሚስጢር አሁን ወደ ምድራዊ መገለጫ እንመለሳለን፡፡ አካል የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን ከጌታዋ ጋር ባላት ግንኙነት ካየን በኋላ አሁን ደግሞ በሰዋዊ ግንኙነቷ አንጻር እንመለከታታለን፡፡ አባላት እርስ በርስ እንዴት መሥራት አለባቸው? ብለን የምንጠይቅበት ጊዜ መጥቶአል፡፡

ኢየሱስና ሕዝቡ እንዲሁም አባላቱ አካል የመሆናቸው ሐሳብ፣ ከሐዋርያት ሁሉ ለመጀመሪያ ጊዜ የተገለጠው ለጳውሎስ ይመስላል፡፡ በርግጥም ይህ የግሉ የቤተ ክርስቲያን እይታ ነው፡፡ ይህም ከመለወጡና ከመጠራቱ፤ ጌታም ለእርሱ ለመጀመሪያ ጊዜ ከተናገረው ቃል ጋር የተያያዘ ነው፡፡ "አንተ የምታሳድደኝ ኢየሱስ ነኝ" (ሐሥ 9፥5) በሚለው፡፡ ያምኑትን ማሳደድ ኢየሱስን ማሳደድ ነው፡፡ ደቀመዛሙርቱን መጉዳት እርሱን መጉዳት ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህ ቃላት ስለ ቤተ ክርስቲያን ምስጢር ለጳውሎስ ሊገለጥ ያለውን ታላቅ መገለጥ ያውጃሉ፡፡ ስለ ጌታ ዐዲስ ነገር ነገሩት፤ እስከዚያ ዕለት ድረስ በምድር ላይ እያለ ኢርቀዕ በሆነ መልክ ከተናገረው ያላለፈውን ነግረውታል፡፡

ነገር ግን ጌታ ይህን ጉዳይ ለጳውሎስ ከዚያ ላይ አልተወውም፡፡ ሰማያዊ ምስጢር ሆኖ ሳይገለጥለት እንዲቀር አላደረገም፡፡ ቀጥሎ የመጣው ትእዛዝ ከዚህ መገለጥ ተግባራዊ ውጤት በኋላ መጣ፡፡ "ተነሥተህ ወደ ከተማዪቱ ግባና ታደርግ ዘንድ የሚያስፈልግህን ይነግሩሃል፡፡" ይነግሩሃል፡፡ ከእነርሱ በተቃራኒ ቆሞ የነበረባቸው ደቀ መዛሙርት ካላገዙት በቀር ጳውሎስ ምንም ማድረግ አይችልም፤ አንዳች ነገር ከቶ ሊያውቅ አይችልም፡፡ ሕያው በሆነችው ቤተ ክርስቲያን በኩል ካልሆነ በቀር፣ ጳውሎስ ምን ማድረግ እንዳለበት ጌታ ራሱ አይነግረውም፡፡ ለግለሰብ ጥሪና ተልእኮ እገዛውን አይሰጥም፡፡ ግላዊነት ኀጢአት ነውና፤ በክርስቶስ አካል ላይ ጉዳት ያደርሳል፡፡

ስለዚህ ጳውሎስ ደማስቆ ደረሰ፤ በዚያም ትዕግሥት የሚያስጨርስ መጠባበቅ ደረሰበት፡፡ በመጀመሪያ ማንም ሰው አልመጣም፡፡ ከሦስት ቀን የጨለማ ቆይታ በኋላ አንድ ሰው ደረሰ፣ ያም ሆኖ እንኳ፣ "ደቀ መዝሙር" እንጂ ሌላ አልነበረም፡፡ ከዚህ ሉቃስ ካመለከተው ቀላል ሹመት፣ ማለትም ሐናንያ ሕይወቱን የሰጠና የተከበረ ጠባይ የነበረው ሰው ከመሆኑ በቀር "ይህን የቤተ ክርስቲያን ታላቅ ሐዋርያ" እንዲሆን የተለየውን ሰው ለመርዳት ልዩ

ችሎታ የሌለው ተራ ወንድም ነበር ብለን መደምደም ይኖርብናል። ይሁን እንጂ፣ ለጳውሎስ የቤተ ክርስቲያን ምስጢር ተግባራዊ መሆን ያለበት ከዚህ ላይ ነው።

የጠርሴሱን ሳውልን በዝና የሚያውቀው ሐናንያ፣ እርሱን ለመፍራት በበኩሉ በቂ ምክንያት የነበረው ሲሆን ለመለኮታዊው ጸጋ ተአምራት፣ ከልቡ ተግባራዊ የሆነ መግለጫ መስጠት አለበት። ያ ጥንቃቄ የተሞላበት፣ "ስለዚህ ሰው" (9፥13) አሁን "ወንድም ሳውል" ሆኖአል (ቁ. 17)። ኢየሱስ ጠላትነትን ሰይፎአል። ያ ፍርሃትም ተወግዶአል። በወንድማዊ ቃል የሐናንያ የሰላምታ አገላለጽ፣ ስለ ክርስቶስ አካል የመላለማዊቷ ቤተ ክርስቲያን ዕውቅና፣ ሐናንያ ያከናወነውም ግልጽ ተግባር ፤ ዐዲስ የተገኘውን የእነዚህን ሁለት ሰዎች አንድነት በአንድ ቅባት ሥር አጉልቶ ያሳያል። እግዚአብሔር መላለማዊ ውጤት እንዲኖራቸው ያቀዳቸውን መመሪያዎች ባንድ መንፈስ ሰጡ፤ ተቀበሉም (ሐሥ 22፥14-16)።

ጳውሎስ በመልእክቶቹ ላይ ስለ አካል ለየት ያሉ ሁለት አተያዮችን ይሰጠናል፤ እነዚህ አተያዮችም አንዱ በኤፌሶን መልእክት ላይ ሲገኝ ሌላው በ፲ኛ ቆሮንቶስ መልእክት ላይ ይገኛል። አንደኛው ቤተ ክርስቲያንን በሰማያት ላይ ሲያያት፣ ሌላው ደግሞ በምድር ላይ በጽኑ መሠረት ላይ ተመሥርታ ያያታል። በኤፌሶን መልእክት ላይ ቤተ ክርስቲያን ሁለመናዋ አካሉ ናት። ሆኖም ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ጳውሎስ "እናንተም የክርስቶስ አካል ናችሁ" (፩ቆሮ 12፥27) ብሎ ለመጻፍ ችሎአል። ብዙዎች እንደሚያደርጉት፣ የኤፌሶን መልእክትን እንደ ሰርኩላር (ማስታወቂያ) መልእክት አድርገን ካሰብን፣ ጳውሎስ በሰፊው በማሰብ፣ በመላለማዊ አባባል፣ ራሱን በክርስቶስ አካል ላይ ለምን እንደ ተጠመደ ለመግለጽ ይህ ያግዘናል፤ በ፲ቆሮንቶስ መልእክት ላይ ግን በዚህ ጊዜ በተለይ በግሪክ ከተማ ለምትገኘዋ ቤተ ክርስቲያን በመጻፍ፣ ይህች አካል የሆነችዋ ቤተክርስቲያን በምድር ላይ በአንድ ነባራዊ ሁኔታ ውስጥ ስትሠራና አካል እንደሚሠራውም ስታከናውን ያሳየናል።

በ፲ቆሮንቶስ 12፥21 ላይ ትንሿ ፋይዳ ያላት ሐረግ ገለጻም ይኸው ነው ብዬ ዐስባለሁ፤ "ዓይን እጅን፣ አታስፈልገኝም ልትለው አትችልም፤ ወይም ራስ ደግሞ እግሮችን አታስፈልጉኝም ሊላቸው አይችልም"። ጳውሎስ ከዚህ ላይ የሚለውን በሚገባ ሳናስተውል እንዳንቀር መጠንቀቅ አለብን። የክርስቶስ አካል፣ በመላለማዊ መልኩ በሰማይም ይሁን ወይም በዚህ ምድር ላይ፣ አንድ ራስ ብቻ አላት፤ እርሱም ክርስቶስ ራሱ ነው (ኤፌ 4፥15)። የአብያተ





ክርስቲያናት አጥቢያዊ "ራሶች" ሊኖሩ አይችሉም፤ አለዚያ ወዲያውኑ በአካሉ ውስጥ መከፋፈል ይኖራል፤ ጳውሎስም ሊኖር ይችላል በማለት ሐሳብ እያቀረበ አይደለም። ይልቁን የማንነትንና የትግበራን ተግባራዊ መርሖች ለማሳየት በ፲ቆሮንቶስ ላይ የሰው አካልን ዘይቤ ይጠቀማል፤ በዚህ መሣሪያነትም ሰማያዊና ዘላለማዊ የሆነው የክርስቶስ አካል በዚህ ምድር ላይ እንዴት እንደሚሠራ ያሳያል። ራስ የሆነው ክርስቶስ ያለ አነስተኛው አካል ሊሠራ እንደማይችል ሁሉ አንድ ብቸኛ አባልም (ብልትም) ከሌላው ተለይቶ ሊሠራ አንማይችል ያረጋግጣል።

ስለዚህ በ፲ቆሮንቶስ ላይ ጠቅላላው ነገር ከሰው ግንኙነት አንጻር የታየውን ያህል ለመለኮታዊው ዐላማ ትኩረት ተሰጥቶት እናይም። መለኮታዊው ዐላማ አስፈላጊ ነው፤ ያለርሱ ማንም ሊተገበር አይችልምና፣ ጥያቄው ግን፣ ወደ ምድር አውርደን እኛ ዛሬ በምንገኝበት ሁኔታ እየተገበርነው ነውን? የሚል ነው።

ችግሩ ያለው ሁለቱን ከመያዝ ላይ ይመስላል። የኤፌሶን መልእክትን ሐሳብ መቀበሉ ቀላል ነው ይኸውም እግዚአብሔር ምን እንደሚኖረው ሰማያዊ የሆነው አመለካከት ነው። ችግራችን የሚጀምረው በ፲ኛ ቆሮንቶስ ላይ ነው። በመንፈሳዊ ሐሳብ ለተጠመዱት ያ መልእክት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ነው፤ እንዲህ በመሆኑም ወደ ተግባር ሲተረጐም የሚያጋጥሙትን ችግሮች አድበስብሶ የማለፍ እንቅፋት ምንጊዜም ያጋጥማቸዋል። በሚገባ ከተረጋገጠው፣ አመች ሆኖ ከሚገኘውም ከዐዲስ ኪዳን አካሄድ ወይም ከቤተ ክርስቲያን አካሄድ ግንዛቤ በማግኘትና ለዚሁም የሙጥኝ ብሎ በመገዛት መደምደሚያ ላይ ላለመድረስ ይሻሉ፤ እንዲህ ማድረጋቸውም ትክክል ነው። ይህም የዚያ ታሪካዊ ጅማሮን ሕይወት አልባ አምሳያን እንደሚያመጣ በደንብ ያውቃሉ። ስለዚህ በምትኩ በኤፌሶን መልእክት ላይ ፍንትው ብላ በቀረበችው ክብርት በሆነችው ቤተ ክርስቲያን ላይ ዐይናቸውን (ሐሳባቸውን) ጣሉ፤ ይህ ግን ሌላ ሳይሆን ከተቃራኒው ስሕተት ላይ እንዲወድቁ አደረጋቸው ይኸውም ራእዩን በእጅጉ "መንፈሳዊ" ማድረግ ሲሆን ሙሉ በሙሉ ባይሆንም፣ ምናባዊ ከመሆን ደረጃ ላይ ደረሰ።

ነገር ግን ፲ቆሮንቶስ ምዕራፍ 12 በጣም ግልጽ ክፍል ነው፣ ብዙዎች ምንነቱን ሳይገነዘቡት የቀሩትም ግልጽ ከመሆኑ የተነሣ ሳይሆን አይቀርም። ከዚህ ላይ ያለው ሰማያዊ አይደለም፤ ምድራዊም አይደለም፤ ነገር ግን ሰማያዊ ሆኖ በምድር ላይ የተገለጸ ነው። በሰማያት የአካሉ መገለጥ በእጅጉ ተግባራዊ

የሆኑ ውጤቶችን ወዲያውኑ እንዲያስገኝ የታለመ ነው፤ በዚያ ላይ የተብራሩትም እነዚህ ውጤቶች ናቸው።

የእግዚአብሔር መርሕ የትሥጉት መርሕ ነው።[3] እግዚአብሔር ይሻል-በርግጥም ለእርሱ ከመሻት በላይ ነው፤ መለኮታዊ አስፈላጊ ነገር ነው - ይኸውም ሰማያዊ የሆነውን በምድራዊ መገለጫ ማሳየት ነው፤ ይህ ደግሞ በመላእክት ወይም በመናፍስት ሳይሆን በሰዎች በኩል ነው፤ በደብዛዛው ወይም በምናባዊው መልኩ ሳይሆን እማናዊና ተግባራዊ በሆነ መልኩ ነው። በኤፌሶን መልእክት ውስጥ በሰማያት መኖር ምንኛ መባረክ ነው፤ ይሁን እንጂ የኤፌሶን መልእክትን የጻፈ ያ ሐዋርያ የቆሮንቶስ መልእክትንም የጻፈ መሆኑን ልብ በሉ። የእግዚአብሔር ባሕርይ መላለማዊ፣ መንፈሳዊ፣ ሰማያዊም የሆነችው ቤተ ክርስቲያን በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በኩል ጨለማነታቸው ከዚያች አረማዊ ከተማ ከሆነችው ከቆሮንቶስ ከተማ ይልቅ ባላነሰው ስፍራዎች በኩል ምድራዊ መገለጫ ይኖራት ዘንድ ይፈልጋል። ከዚህ ምድራዊ መገለጫ የተነሣ ሰዎች ሐሳባቸውን እንደ ያዙ ለመግባት ዝግጁዎች ናቸው፤ በቤተክርስቲያን አካሄድ ረገድም እጃቸው አለበት። "አንዳንድ ጊዜ ምድራዊ መሆን አለብን!" ይህን በሰበብ በአስባቡ ያሰሙታል። ይሁን እንጂ በእንዲህ ዐይነቱ ምድራዊ ዐውድ እንኳ ቤተ ክርስቲያን ከሰማያዊ አካል መርሕ አኳያ መጓዝ እንዳለባት ፲ቆሮንቶስ ያሳየናል። አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ዛሬ በምድር ላይ የክርስቶስ ማንነት እማናዊ መገለጫ እንጂ ውጫዊ ምስያ አይደለችም። "እናንተም የክርስቶስ አካል ናችሁ" (፲ቆሮ 12፥27) እንደ ተባለው ነው። በዚህ በቆሮንቶስ ከተማ እናንት የቆሮንቶስ አማኞች በዐይነቱ ሙሉ አካል ትሆኑ ዘንድ ተጠርታችኋል።

## ኀላፊነትን መሸከም

ስለዚህ ወደ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 12 እና የአካሉን ተግባራዊ አካሄድ እንደምን እንደ ተመለከትነው ለማስተዋል እንመለሳለን። በዚህ ምዕራፍ ከቁጥር 12 ጀምሮ ያለውን ክፍል በትኩረት ብናስተውል፣ የአካልን ሕይወት የሚገዙት አራት ግልጽ ሕግጋትን ለይተን ማየት የምንችል ይመስለኛል።

የመጀመሪያው በቁጥር 15 እና 16 ላይ ይገኛል። "እግር እኔ እጅ አይደለሁምና የአካል ክፍል አይደለሁም ብትል፣ ይህን በማለትዋ የአካል ክፍል

[3] ቃሎችን የምንጠቀምባቸው በጥንቃቄ ነው። በቤተ ክርስቲያንና ትሥጉት በሆነው ጌታዋ መካከል ያለውን ጉድኝት መሰጠጥ አለማስተዋል ነው።





መሆንዋ ይቀራልን? ጆሮም እኔ ዓይን አይደለሁምና የአካል ክፍል አይደለሁም ቢል ይህን በማለቱ የአካል ክፍል መሆኑ ይቀራልን?" በሌላ አባባል፣ ለመሆን በምትሸበት ሳይሆን ሆነህ በምትገኝበት መሥራት አለብህ። አንተ ሌላውን ሰው ስላልሆንህ ማንነትህን ሆነህ የምትኖርበት ምክንያት የለም። እግር እጅን ለመሆን ቁርጩ ተነሥቻለሁ፤ እጅን ለመሆን ባለመቻሌ ደግሞ አልራመድም! እንደ ማለቱ ያህል ነው። እንዲህ ያለው እምቢተኝነት የሚመነጨው ከተወዳዳሪ ልብ ነው፤ ያ የሚወዳደረው ደግሞ ግለኝነት ብቻ ነው።

ይህ የመወዳደር ልምድ አንድ ነገር ያሳያል፤ ይኸውም የክርስቶስን አካል አለማሳየታችንን ነው። እስቲ ንገሩኝ፣ የትኛው ብልት ነው የተሻለው? እግር ነው ወይስ እጅ? ስለዚህ ጉዳይ ስታስቡ ሁለቱ የሚወዳደሩበት መንገድ የለም። በሰው አካል ውስጥ ተግባራቸው የአንዱ ከሌላው የተለየ ነው። እያንዳንዱም ባለበት ቦታ አስፈላጊ ነው። ይህም ሆኖ እያለ ብዙዎች የእግዚአብሔርን ስጦታ ዝቅ አድርገው ያያሉ። የሚያደንቁትን ልዩ ብልት መሆን ስላልቻሉ የሚገባቸውን ኀላፊነት አንሸከምም ይላሉ። ወይም አገልግሎት ሁሉ በይፋ አገልግሎት ሆኖ ተጀምሮ በይፋ አገልግሎት ሆኖ ያልቃል ብለው ያስባሉ፤ በአደባባይ የማከናወን ስጦታ (ስለሌላቸውም) ምንም አይሠሩም።

በኢየሱስ ምሳሌ ላይ መክሊት ተሰጥቶአቸው ስለ ነበሩት ሰዎች የተገለጸውም በትክክል ይኸው ነበር (ማቴዎስ 25፥14፥30)። ዐምስት መክሊት የተሰጠው ባሪያና ሌላው ደግሞ ሁለት መክሊት የተሰጠው ባሪያ ነበሩ፤ በምሳሌው ላይ ሙሉ በሙሉ አጽንዖት የተሰጠው ግን አንድ መክሊት በደረሰው ባሪያ ላይ ነበር። እዲጋ ያለው አንድ መክሊት ተሰጥቶት ያንኑ በቀበረው ወንድም ላይ ነበር። "ዐምስት መክሊት ወይም ሁለት መክሊት ስለሌለኝ በአንድ መክሊት ምን ልሠራ እችላለሁ በሚታይ መልኩ ማገልገል ስለማልችል ከቶ ምን ጥቅም እሰጣለሁ? ሌሎች ጸሎትን በሚገባ ሊመሩ ስለሚችሉና የጸሎቱንም ጉባኤ በደንብ ስለሚያስኬዱት ታዲያ ለእኔ ዝም ማለቱ መልካም አይደለምን? ዝና የሚያስገኝን ኀላፊነት መያዝ አልችልም፤ ስለዚህ በአንድ የሥራ ቦታ ላይ መገኘቴ ከቶ ምን ጥቅም ይኖረው ይሆን?"

ነገር ግን ምሳሌው ሁለት ወደ አራት፣ ዐምስትም ወደ ዐሥር፣ ማደግ ከቻሉ አንዱ ደግሞ ወደ ሁለት ማደግ እንደሚችል ያስተምራል። የሕይወትን ምስጢር ፈልገን የምናገኘው ስንሠራ ነው። ቤተ ክርስቲያን አንድን መክሊት ቀብረው በሚይዙት ምእመናን የምትሠቃየውን ያህል በባለ ዐምስት መክሊት

ዝና አትሡቃይም፡፡ የመላዋ አካል ሕይወት በአንድ መከሊት ቀበራ ይገደባል፤ ይራቈታልም፡፡

ሰማያዊ አካል የሆነውን ልብ ብንለው ኖሮ ዝቅተኛውን (አነስተኛውን) ስፍራ ለመያዝ በጣም ደስተኞች እንሆን ነበር፡፡ ርግጥ ነው፤ አንድ መክሊት ስላለን ብቻ አንሠራም ማለት ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ ምኞትና ፍላጎት ያለን መሆኑን ሊያሳይ ይችላል፡፡ ግን ልክ አይደለም፣ እኔን ታላቅ አባል ማድረጉ የሚያስደስተው ከሆነ ጌታ ይመስገን! ውራ አባል ሊያደርገኝ ከመረጠም ከዚያ ባላነሰ ሁኔታ እርሱ ይመስገን! እጅ ነኝ ወይስ እግር? የሆንኩትን በደስታ እሆናለሁ፡፡ በእርሱ ምርጫ ፍጹም ደስተኛ ነኝ፤ እርሱ በመረጠው ዘርፍ ለመሥራትም ፈቃደኛ ነኝ፤ ስጦታውን ተቀብዬ ብሠራበት፣ አንዱ ወደ ሁለት ወዲያውም ወደ አምስት፣ ዐልፎ ተርፎም ወደ ዐሥር ሊያድግ ይችላል፡፡

ጳወሎስ "ድፍረት የሌላቸውን አጽኑአቸው" በማለት ጽፎአል (1ተሰ 5፥14)፤ ቃሉም በቁሙ ሲታይ "ባለ ንኡስ ነፍስ" የሆኑትን ማለት ነው፡፡ ባለ አንድ መክሊት የሆነውን ሰው ማደፋፈር አለብን፤ ትልቅ ስጦታ ስላልሆነ በስጦታው ታላቅነት አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ውስጥ ስለሚያድር ማደፋፈር አለብን፡፡ የምኞቱ ተስፋ እግዚአብሔር ራሱ መሆን አለበት፡፡ የቅርብ የሥራ ባልደረባዬ ከሆኑት አንዱ እንደ ገና ከመወለዱ በፊት በጓደኞቹ ዘንድ ዘገምተኛ እንዲያውም የማይረባ ተብሎ ይታሰብ ነበር፡፡ ሆኖም እግዚአብሔር ሕይወቱን ሲይዝና መንፈስ ቅዱስም በእርሱ ውስጥ መሥራት ሲጀምር፣ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ፣ አሁን ሆኖ እንደሚገኘው፣ በቻይና አገር ውስጥ እጅግ ከፍተኛ የሆነ ስጦታ ካላቸው የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች ውስጥ አንዱ ሆነ፡፡

ስለዚህ የሥራ የመጀመሪያ ሕግ የተሰጠንን እንድንጠቀምበት ነው፡፡ ሰበብ ፈልገን እኔ ከዚህ ላይ አልፈልግም ማለት አንችልም፡፡ ወይም መጽሐፍ ቅዱሳችንንና ማስታዎሻዎችን ይዘን ወደ ፊት ላሰብነው አገልግሎት ለመዘጋጀት ገለልተኛ ወደ ሆነ ስፍራ በመሄድ መንፈሳዊ መታደስን አናገኝም፤ ይህን ብናደርግ አሁን ካለው ጎላፊነታችን እየሸሸን ነው፡፡ ሥጋዊ አካላችን ሊታደስ ይችላል፤ መንፈሳችን ግን አልታደስም፡፡ እንግዲህ ዋናው ሐሳብ ይህ አይደለም፤ ደንቡ ምንጊዜም ባለን ነገር ሌሎችን ማገልገል ነው፤ ይህን በማድረጋችንም እኛ ራሳችን የተመገብን መሆናችንን እናስተውላለን፡፡ በውሃው ጉድጓድ ላይ እያለ የኢየሱስን ታሪክ እናስታውስ፡፡ ተርቦ ነበር፤ ደቀ መዛሙርቱን ምግብ እንዲገዙ





ልኮአቸው ነበርና፤ ተጠምቶም ነበር፤ ሰምራዊቷ ሴት ውሃ እንድትሰጠው ጠይቋት ነበርና፡፡ ይሁን እንጂ ደቀ መዛሙርቱ ተመልሰው ሲመጡ በልቻለሁ ማለት ቻለ፡፡ በችግር ላይ የነበረችን ነፍስ አገልግሎ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመፈጸሙ ተበረታቶ ነበር፡፡

የአካሉ ኅብረት ምንጊዜም ባለ ሁለት አቅጣጫ ነው፤ መቀበልና መስጠት፡፡ ዘወትር ለመቀበል መሻት ኅብረት አይደለም፡፡ ሰባኪዎች ላንሆን እንችላለን፤ ለማምለክ ስንመጣ ግን ያለንን ይዘን እንመጣለን፡፡ አትሮኖሱ አጠገብ ላለው አገልጋይ ከጉባኤው ርዳታ መድረስ አለበት፡፡ መቀመጥና መመልከት ምንም አይሠራም፡፡ ለሌሎች የሚጠጡትን መስጠት አለብን፤ ይህም የግድ በመናገር ብቻ ሳይሆን በአርምሞ ጸሎትም (በለሆሳስ ጸሎትም) ነው፡፡ የምንቀመጥና የምንሰማ ከሆን በመንፈስ አዚያው መሆን አለብን እንጂ የትም ቦታ መሆን የለብንም!

"እስከመጣ ድረስ ሥሩ"፤ በተገኘንበት ስፍራ ላይ ሆነን እንዴት ያለ ታላቅ የአገልግሎት ልክ አለን! ዐደራ የተሰጠን የሥራ ድርሻ ለአካሉ ነው፤ ስለዚህ በሌሎች የምንቀናበት ምክንያት የለም፡፡ ውድድር ውስጥ በመግባት ለወንድማችን፣ "እግዚአብሔር አንተን እንጂ እኔን እየተጠቀመብኝ አይደለም" ማለት አንችልም፡፡ አንዳንዶቻችን ጴጥሮስን ሆነን ነፍሳትን ማዳን እንሻለንን? ዐሥራ አንዱ ከጴጥሮስ ጋር ቆመው እንደ ነበር ልብ እንበል፡፡ ጴጥሮስ አፈ ጉባኤ ነበር፤ ሆኖም "እነዚህን ነፍሳት አዳንኩ" ብሎ ከቶ ሊደፍር አይችልም፡፡

ስለዚህ እያንዳንዱ የአካል ብልት (አባል) አገልግሎት አለው፤ እያንዳንዱ አባልም (ብልትም) ጌታ ባስቀመጠለት ስፍራ ይሠራ ዘንድ ተጠርቶአል፡፡ ክብሩ ለእርሱ ከሆነ ሥራውን ማን ሠራው ለውጥ አያመጣም፡፡ እርሱ ወደ ሰጠን ስፍራ ወደ እግዚአብሔር ጥሪ መመለስ እንጂ ጡረታ ስንወጣ እናድጋለን ብለን መሸሽ የለብንም፡፡ "ፈራሁም ሄጄም መክሊትህን በምድር ቀበርሁት፡፡" በዚያ ዐይነቱ አቅጣጫ ምንም ዐይነት ክብር ሊመጣ አይችልም፡፡

### ውስንነትን መቀበል

ሁለተኛው የተግባር ሕግ የሚገኘው በቁጥር 17 እና 18 ላይ ነው፡- "አካል ሁሉ ዓይን ቢሆን መስማት ወዴት በተገኘ? ሁሉም መስማት ቢሆን ማሽተት ወዴት በተገኘ? አሁን ግን እግዚአብሔር እንደ ወደደ ብልቶችን እያንዳንዳቸውን በአካል አድርጎአል፡፡" ከዚህ ላይ የተቀመጠው መርሕ፣

በአንድነት ስንኖር (ሕይወታችን ውስጥ) ምንጊዜም ሌሎች እንዲሠሩ ሥፍራ መፍቀድ አለብን፡፡

ግልጽ በሆነ መልኩ ሲቀመጥ፣ ሁሉንም ለመሥራት እና አንተም ሁሉን ለመሆን ጥረት አታድርግ! ማንም ማሰብ የሚችል ሰው፣ አካል ሁሉ በአንድ ነጠላ (ብቸኛ) መንገድ ብቻ ሲሠራ ማየት አይፈልግም፡፡ ሁሉም ዐይን ብቻ መሆኑ አያስኬድም፤ ወይም ዐይን የሁሉን ሥራ ለመሥራት ማሰቡ አያስኬድም፡፡ ጌታ በአካል ውስጥ ልዩ ልዩነትን በሥርዐት አስቀምጦአል፤ ጆሮንና አፍንጫን፣ ዐይንና እጅን አስቀምጦአል፤ አንድ ወጥ መሆን፣ በርግጥም የአንድ ብልት የበላይነት አይደለም፡፡ ስለዚህ ቀደም ያለው መርሕ ኋላ ኋላ ለሚጐተቱት ከሆነ፣ ይህኛው ደግሞ አካልን በሞላ ለመሆን በመሻት አለ ልክ ወደፊት ለሚጣደፉት ነው፡፡ ለእነርሱ ያለኝ ቃል ደግሜም እናገራለሁ፤ ሁሉን ለመሥራት ወይም ለመሆን አትሞክሩ፤ እናንተ እኮ ሁሉም አይደላችሁም ነው፡፡

ወደ ጸሎት ስብሰባ ሲመጡ ራሳቸው ብቻ መጸለይ የሚችሉ ሰዎች አሉ፤ ሌሎችን መስማት አይችሉም፡፡ በጸሎት ለመምራት እንጂ ለመመራት አይፈልጉም፡፡ ሌሎች እንዲሰሙና 'አሜን' እንዲሉ ይፈልጋሉ እንጂ፣ ሌሎች ሲጸልዩ ለመስማት ስምተውም 'አሜን' ለማለት ትዕግሥት የላቸውም፡፡ የራሳቸውን አስተዋፅኦ ብቻ የስብሰባው ዋንኛ አንኳር እንዲሆን ይፈልጋሉ፡፡ ከሌሎች ጋር ሲጸልዩ እንኳ ግለኝነት ያጠቃቸዋል፡፡

በንግግርም ወቅት ግለኝነት የሚታይባቸው ናቸው፡፡ መናገር የሚችሉት ስለ ራሳቸውና ስለ ሥራቸው ብቻ ነው፡፡ ሌሎች ሲናገሩ ሳለ ራሳቸውን ጣልቃ በማስገባት ካልተናገሩ በቀር መስማት አይችሉም፡፡ የመቀበል ችሎታ የላቸውም፡፡ ግለኝነት በክርስትና ሥራ ውስጥ አሳዛኝ ገጽታ ነው፡፡ የኛ ሥራ፣ የኛ አገልግሎት እጅግ አስፈላጊ ስለሆነ ሌሎች ለሚያከናውኑት ሥራ ግድ የለንም እንደ ማለት ነው፡፡

በዛሬው ዘመን በክርስቶስ አባላት ዘንድ ከፍተኛ ተስፋ መቁረጥና ባዶነት ይገኛል፣ ምክንያቱም ልምድ ያላቸው የእግዚአብሔር ባሪያዎች ሌሎች እንዲሠሩ ስለማይፈልጉ ነው፡፡ ጌታ አገልግሎት ሰጥቶን ነበር፤ በዚህም ምክንያት ሌሎች ማደግና መብሰል ካለባቸው እኛ ራሳችን ኀላፊነቱን ሁሉ መሸከም አለብን ብለን እናስባለን፡፡ ይህን በማድረጋችን ግን የሌሎችን እድገት





እያደናቀፍን መሆናችንን አናስተውልም፡፡ ይህ ስሕተት የተስፋ መቁረጥ ዐልፎ ተርፎም የመከፋፈል መንሥኤ ነው፤ ውጤቱም በዚህ ብቻ አያበቃም፡፡

ለምሳሌ መልሱን ማየት የማልችልበት፣ ስለ እርሱም ራሴን በደብዛዛ ሁኔታ ውስጥ የማገኝበት አስተምህሮአዊ ሐሳብ አጋጥሞኛል ልበል፡፡ በዚህ ጊዜ ምን አደርጋለሁ? እኔም በራሴ መፍትሔ ልሻለት እሞክራለሁን? ወይስ ከእግዚአብሔር የተቀበለው ልዩ ስጦታው ማስተማርና ማብራራት እንዲሁም ሰዎችን ከአስተምህሮአዊ ጭጋግ ውስጥ ማውጣት ወደ ሆነለት አባል እሄዳለሁ? የመጀመሪያውን ብፈጽም ለዐዲስ አስተምህሮአዊ ልዩነት በር እየከፍትኩ ነው፤ አስተምህሮአዊ ልዩነቶች የተወለዱት ከዚሁ ላይ ነውና፡፡ ጌታ አስተማሪ ባደረገው የአካሉ ብልት (አባል) አማካይነት ችግሬን እንዲፈታልኝ እርሱን በማመን ፈንታ፣ በዚሁም ላይ ይህንን በተመለከተ ሌላው አባል ለእኔ እንዲያከናውንልኝ መፍቀድ፣ ሁለታችን የተለዩ ዐልፎ ተርፎም የሚቃረኑ ነገሮችን እንድናስተምር መንገዱን በእጅጉ አመቻቸሁ ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ፣ እኔ እንደ ወንጌላዊነቴ ወደ ጌታ ያመጣኋቸውን ሰዎች የማስተማር ተግባርንም ብይዘው፣ ይህ ዐይነቱ ግራ መጋባት መከሠቱ አይቀርም፡፡ ይልቁን ማገልገል አለብኝ፤ ከዚያም የእኔ ተግባር (ሥራ) ከተፈጸመ በኋላ እኔ ገለል ብዬ ሌላው እንዲሠራ ማድረግ አለብኝ፡፡ የአካሉ የመጀመሪያ መርሕ፣ "የሚተክልና የሚያጠጣ አንድ ናቸው" የሚል ነው (1ቆሮ 3፥8)፡፡

እንደ አባልነቴ፣ ሌላው አባል መስጠት ያለበትን ለመቀበል መዘጋጀት አለብኝ፡፡ በበኩሌ ለውሱንነት ፈቃደኛ መሆን አለብኝ፡፡ ቤተ ክርስቲያን በጸሎት ላይ ናትን? ጸጥ ብዬ ለማዳመጥና ብርቱ የጸሎት ሰው ላልሆኑት ወገኖች ዕድል ለመስጠት መዘጋጀት አለብኝ፡፡ የስብከት ስጦታ አለኝን? ቁጭ ለማለትና ሌሎችን ለመስማት መማር አለብኝ፡፡ የእኔ ሚዛን (መለኪያ) አነስተኛ ወይም ትልቅ ይሁን፣ እንደ አባልነቴ ከእርሱ ዐልፌ መሄድ የለብኝም፤ የመስቀሉ ምልክት ከልክ በላይ በሆኑትና ከአካሉም ውጭ በሆኑት ላይ ነውና፡፡ በተሰጠኝ መስክ ለመወሰን፣ ሌሎቹም በራሳቸው መስክ እንዲሠሩ ፈቃደኛ መሆን አለብኝ፡፡ ሌሎች እኔን ለማገዝ የሚያከናውኑትንና ለእኔ የሚያደርጉትንም እገዛ ለመቀበል ደስተኛ መሆን አለብኝ፡፡

## ሌሎችን ከፍ አድርጎ መገመት

ሦስተኛም ወደ ቁጥር 21 እና 22 እንመጣለን፡- "ዐይን እጅን አታስፈልገኝም ልትለው አትችልም፤ ወይም ራስ ደግሞ እግሮችን፣

አታስፈልጉኝም ሊላቸው አይችልም፡፡ ነገር ግን ደካሞች የሚመስሉ የአካል ብልቶች ይልቁን የሚያስፈልጉ ናቸው፡፡" ጉልሕ በሆነ መልኩ ሲቀመጥም፣ ሌላውን አባል ለማስወገድ ከቶ መሻት የለብንም ማለት ነው፡፡ በራስ ዘይቤነት በተገለጸው ችሎታ ልክ መራመድና ከሌሎችም ጋር አገልግሎት መስጠት እንችላለን ብለን ከቶ ማሰብ የለብንም፡፡ ደካማነት ወይም ኰልታፋነት በአካል መታየቱ ከአባልነቱ እንዲወገድ ምክንያት መሆን የለበትም፡፡[4] ሌላውን፣ "አንተ አታስፈልገኝም" በማለት በድፍረት መናገር የለብንም፡፡ ይልቁን ከእነርሱ እንማራለን ብለን ያልገመትነውን ቁም ነገር የቱን ያህል ልንማር እንደምንችል እናስተውላለን፡፡ ዝቅ አድርገን ከምንገምታቸው የጸሎት እገዛ ልንሻ ይገባል፡፡ ራሳችንን ዝቅ ለማድረግ፣ ይህን በማድረግም መንፈሳዊ ሥፍራችንን ለማግኘት የቱን ያህል ዝግጁዎች ነን! ይሁን እንጂ ጌታ የአካሉ ደካማ ለሆነው አባል ቦታ እንዳለውና ሊጠቀምበትም እንደሚችል ያረጋግጣል፡፡

ከዓመታት በፊት፣ አንድ ጊዜ፣ በሕይወቴ ከባድ ችግር ገጥሞኝ ነበር፡፡ ጉዳዩ (ጥያቄው) ለአገልግሎት በግል የመንፈስ ቅዱስን ስጦታን የሚመለከት ነው፡፡ ይህ በጣም አስፈላጊ እንደ ሆነ ተሰምቶኝ ነበር፤ እንዲሁም ይህን ጉዳይ አስመልክቶ ስላለው አስተምህሮ ግራ ተጋብቼ ነበር፡፡ መጸለይ እንደሚገባኝ ሆኖም የቱንም ያህል ብጸልይ ጌታ ጥያቄዎቼን ለመመለስ ወይም ተመክሮው የሚገኝበትን መንገድ ለማሳየት ፈቃደኛ ያልሆነ መሰለ፡፡ ለእኔ አንድ የተሻለ ነገር እንዳለው ዐውቃለሁ፤ ሆኖም የምደርስበት አልመስል አለኝ፤ በዚህ ጉዳይ ላይ ግልጽ የሆነ ነገር ማግኘት እንዳለብኝ አለዚያም ወደ ፊት መሄድ እንደማልችል ዐውቃለሁ፡፡ አገልግሎቴ ሁሉ በሚዛኑ ላይ ነበር ማለቱ ማጋነን አይደለም፡፡

በዚያ ወቅት እኔ በአገሪቱ ዳርቻ ላይ በሚገኝ ስፍራ ወንጌልን በመስበክ አገልግሎት ተጠምጄ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት እኔ በተሰማኝ ጉዳይ ላይ ዕውቀት ካላቸው የጌታ ባሪያዎች ርቄ ነበር፡፡ ወደዚያ የላከኝ እርሱ ነበር፤ ያለ ጥርጥር ፍላጎት ነበር፤ ወይም በዚያ የነበሩት ሕዝብ ወንጌልን ለመስማት ዝግጁ ነበሩ፡፡ ነገር ግን አንድ ነገር ጐድሎ ነበር፡፡ ስብከቴ ኀይል አልነበረውም፡፡ ብዙ ፍሬም አልነበረው፡፡ ሆኖም እግዚአብሔር ሊሰጠኝ ይሻ የነበረውን ነገር እኔ መቀበል አልቻልኩም ነበር፡፡ ብቻዬን ማከናወን አልቻልኩም፡፡ በዚያን ጊዜ ከሁሉ በላይ ያስፈለገኝ የነበረው ኀብረት ነበር፡፡

[4] ርግጥ ነው፤ ኀጢአትን በተመለከተ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቅጣት አለ፡፡ ስለዚሁ ጉዳይ ኋላ ላይ እንናገራለን፤ ይሁን እንጂ ከዚህ ላይ ያለው አይታ ይህ አይደለም፡፡





ነገር ግን የት ነው የማገኘው? በርግጥ በቤታቸው እኖር የነበርኩባቸው አማኝ ገጠሬዎች ነበሩ፤ ሆኖም ስለ ጌታ እናሳ ግንዘቤ ያላቸው፣ እኔ የምገኝበትን ከባድ ችግር ለማቃለልም እንዳቸ አስተዋፅኦ የሚያደርጉ አልመሰለኝም፡፡ የምገኝበትን ችግር ማቃለል ቀርቶ ለእኔ በሚገባ ለመጸለይ በቂ የሆነ መሠረት ያላቸው አልመሰለኝም፡፡ የሚገርም ነው አካልን ረስቼ ነበር እኮ!

በመጨረሻ መቀጠል ከማይቻልበት ሁኔታ ላይ ደረስኩ፡፡ እንግዲህ ተልእኮዬን አቋርጬ ጓዜን ጠቅልየ መሄድ ከሌለብኝ፣ እነርሱን ከመጥራት በቀር ሌላ አማራጭ አልነበረም፡፡ ስለዚህ ባቀረብሁት ጥያቄ መሠረት እነዚህ ገር ወንድሞች ለምፈልገው ነገር (ላጋጠመኝ ችግር) ደረሱልኝ፡፡ ስለ ችግሬ የቻልኩትን ያህል ነገርኳቸው፡፡ እነርሱም ጸለዩ፤ እየጸለዩ ሳለ ብርሃን ወገግ አለ! የሆነውን ነገር ማብራራት አስፈላጊ አልነበረም፡፡ ተፈጸመ፤ ተከናወነም፤ የተፈጸመውም መደገም በሚያስፈልገው ሁኔታ ነበር፡፡ ከዚያን ቀን ጀምሮ የበረከት ማዕበል ፈሰሰ፡፡

እውነት ነው፣ እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ ብቻችን መጓዝ ወደ ማንችልበት ስፍራ ያመጣናል፡፡ "እኔና እግዚአብሔር በቂ ነን" የሚለው የሕይወት አካሄድ በርግጥ እርሱን እየከለከለው ነውና፡፡ በዚያ ዕለት ደካማ መስለው የሚታዩት የአካሉ ብልቶች ለእርሱ እጅግ ውዶች መሆናቸውን ጌታ አስተማረኝ፡፡

## አንድነትን መጠበቅ

አራተኛው፣ ቁጥር 24 እና 25 እንዲህ በማለት ይነግሩናል፡፡ "እግዚአብሔር ግን የአካል ብልቶችን አንድ ላይ አገጣጥሞ ክብር ለሚጐድላቸው የበለጠ ክብር ሰጥቶአቸዋል፤ ይህን ያደረገው በአካል ብልቶች መካከል መለያየት ሳይኖር፣ እርስ በርሳቸው እኩል እንዲተሳሰቡ ነው፡፡" (አመት)፡፡ በመደምደሚያ ላይ ሐዋርያው የሚለው መለያየትን በብርቱ መቃወም እንዳለብን ነው፡፡ ፈጽሞ አልተፈቀደም፡፡ መለኮታዊ ፈቃድ በአካሉ ላይ መለያየት እንዳይኖር ነው፡፡

ቀደም ባሉት ምዕራፎች ስለ አንድነት በአጠቃላይ ተናግረናል፡፡ ቤተ ክርስቲያን በሰማይ ላይ አንዲት ሆና እንደምትታየው ሁሉ መከፋፈል አትችልም፡፡ እግዚአብሔር ይመስገን፣ ለዘላለሙ አንድ ናት፡፡ ርግጥ ነው፣ በምድር ላይ ባለችው ቤተ ክርስቲያን አንድነት ላይ ድንገተኛ አደጋዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ሰማያዊ ሕይወቷን በተመለከተ ግን አካልን ማንም አይነካትም፤ ይሁን እንጂ በምድር ላይ ስትንቀሳቀስ፣ እውነታው የሚመር ቢሆንም እንኳ

የቆሮንቶስ ሁኔታ እንደሚያሳየው ልትነካና ልትቀራረጥ ትችላለች:: ጳወሎስ ይህንኑ ሁኔታ በግልጽ ያወግዛል::

ታዲያ የተግባራዊ አንድነት ምስጢር ምንድን ነው? ስለዚሁ ጉዳይ ሁለት ሐሳቦች ከዚህ ላይ አሉ፤ "አይሁድ ብንሆን፣ የግሪክ ሰዎችም ብንሆን፣ ባሪያዎችም ብንሆን፣ ጨዋዎችም ብንሆን፣ እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናልና:: ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል::" (1ቆሮ 12፥13) "... አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ" (ኤፌ. 4፥4) ገልጠው የሚያሳዩት በአካልና በመንፈስ መካከል ያለውን አስደናቂ ግንኙነት ነው:: ያ ድብቅ የሆነው እውነታ መንፈስ ቅዱስ በአካሉ መገለጥ በኩል አቻ ያለው መሆኑ ነው:: አካል አንድ የሆነው መንፈስ አንድ በመሆኑ ነው:: ልብ በሉ፣ መንፈስ ቅዱስ አካል ነው:: በመንፈስ ቅዱስ ምንጊዜም አንድነት አለ:: መለኮታዊ ሐቅ ርግጥ ነው:: ብቸኛው ጥያቄ "አንድነትን ለመጠበቅ ዘወትር እንትጋለን የሚለው ነው" (ኤፌ. 4፥3)::

ስለ መንፈስ ቅዱስና ስለ አካል ተጨማሪ ሐሳብ ከማቅረባችን በፊት ለመንፈሳዊ አንድነት መነሻው ጉዳይ ሕይወት መሆኑን ራሳችንን እናስታውሰው:: እኛ ጠቅለል አድርገን ያመለከትናቸው አራቱ መርሖች በትእዛዝ መልክ እንዳልተገለጹ ልብ ብላችሁ ይሆናል:: አካል ምን እንደሚመስል በቆሮንቶስ 12 ላይ በአወንታዊ ዐረፍተ ነገር ተገልጾአል:: የሰው አካል የሕይወትና የእድገት ድንገተኛ መገለጥ መሆኑን በሚያሳዩ ቃላት ይገልጻሉ:: ይህ ዋና ጉዳይ ነው:: የሕይወትን ዋነኛ ገጽታ ይኸውም ልባዊነትን (ነፍስን) ልብ ወደምንልበት ደረጃ ያመጣናል::

የእንስሳት ሕይወት ሁሉ ነፍስ አለው፤ ይህ ደግሞ ከእግዚአብሔር ለሆነው ሕይወት እውነት ነው:: ሕይወት ባለበት ነፍስ አለ:: የሳይንስ ሊቅ ሕይወትን ነጠላ ነገር (የተነጠለ) በማድረግ እኛ እንድንዳስሰው ወይም እንድናየው ለእኛ የሚያቀርብበት መንገድ የለውም፤ ወይም ይህን ቢሠራ ኖሮ እኛ የምናይበት መንገድም የለም:: የውስጥ ነፍስ ያለን በመሆናችን ሕይወት ያለን ስለ መሆናችን ሁሉም ይስማማሉ:: በሕይወት ያለን ስለ መሆናችን ደግሞ ማንኛችንም እንጠራጠርም::

ስለ ዐዲሱ ሕይወትም ይህ ትክክል ነው:: እግዚአብሔር የሚሰጠው ሕይወት የሚዳሰስ ወይም የሚታይ ባይሆንም እንኳ፣ ያ ሕይወት እንዳለን መገንዘባችን በርግጥ ለእኛ የሚቻል ነው:: ዐዲስ ሕይወት እንዳለን





እናውቃለን፤ ምክንያቱም ዐዲስ ግንዛቤ በእኛ ውስጥ ተተክሎአል:: አንድ ሰው ደግሞ ሲወለድ ዐዲስ ሕይወትን ከእግዚአብሔር ይቀበላል፤ ታዲያ መቀበሉን እንዴት ያውቃል? ማንኛችንስ ሕይወት ያለን ስለ መሆናችን እንዴት እናውቃለን? የምናውቀው በዐዲስ ሕይወት ግንዛቤ ነው:: ሕይወት በዚያ ካለ ግንዛቤ ይኖራል፤ ወዲያውኑም ወደ እግዚአብሔርና ወደ ኀጢአት ራሱን ይገልጣል:: ኀጢአት ብንሠራ ጭንቀት ይኖራል:: ከሰላማችንና ከደስታችን አንድ ነገር እናጣለን:: ሕይወት ያለ መሆኑ የሚያረጋግጠውም ይኸው ነው:: የእግዚአብሔር ሕይወት ኀጢአትን ስለሚጠላ፣ ስለ ኀጢአት ዐዲስ ግንዛቤን የያዘው በእኛ ውስጥ ሲሆን ወደ እኛ መጥቶአል:: አንድ ሰው ለእርሱ በደሎቹን ሁሉ የሚያመለክተው ሌላ ሰው ካስፈለገው፣ እርሱ ግን ስለ በደሎቹ ግንዛቤ የሌለው ሰው ከሆነ፣ ለመስማት ፈቃደኛ ሆኖ ቢገኝም እንኳ፣ ሕይወት ያለው ሰው ስለ መሆኑ ያጠራጥራል::

ዛሬ በሕይወት ላይ ታላቅ አጽንኦት እናደርጋለን፤ ነገር ግን ያ በቂ አይደለም:: በሕይወት ልባዊነትም (ንቃተ ህሊና) ላይ አጽንዖት ማድረግ አለብን:: ልባዊነት የሌለው ነገር ሕይወት ያለው ስለ መሆኑ ያጠራጥራል:: ሕይወትን ረቂቅ ሐሳብ አድርጎ ማቅረብ ግንዛቤ ማጣት ነውና:: ገሐድና እውነት ነው:: በሰው ልብ ውስጥ ወይ ዐዲስ ሕይወት አለ፤ አሊያም የለም፤ ልባዊነት ያለው ሕይወትም ሕይወት ያለ ስለ መሆኑ ማረጋገጫ ነው:: ወይም ይህ ልባዊነት ስለ ኀጢአት ግንዛቤ የሌለው አይደለም:: ስለ ራሱ ስለ እግዚአብሔርም የተባረከ አወንታዊ የሆነ አመለካከት አለው:: "የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል::" ይህ እውነት ነው፤ ነገር ግን ለሰዎች ይህንኑ መንገር ምንም ጥቅም የለውም፤ ያውቁታል፤ ወይም አያውቁትም:: የእግዚአብሔር ሕይወት ካላቸው በመንፈስ ቅዱስ ይህንኑ ያውቃሉ:: እንዲህ ማለቱ የሚያሳዝን ነው፤ ብዙዎች ስለ ኀጢአት ግንዛቤ ሳይኖራቸው ወይም በእነርሱ ውስጥ ላደረው እግዚአብሔር ፍቅር ሳይኖራቸው ጸሎት ይጸልያሉ:: አንድ ሰው ይህን ጉዳይ መግለጽ የሚችለው የመላእክት ጸሎት በማለት ብቻ ነው፤ ጸሎታቸው የእግዚአብሔር ልጆች ጸሎት መለዮ የለበትምና::

የተናገርነው ሁሉ ስለ ግለሰብ ሕይወት እውነት ከሆነ፣ ስለ አካል ሕይወትም ከዚህ ባላነሰ እውነት ነው:: ሕይወት ያላቸው ከሌሎች ጋር በጋራ ይይዙታል፤ አካልን የሚያውቁም ስለዚያ ሕይወት የጋራ ሕይወት ግንዛቤ አላቸው:: አካል መርሕ ወይም አስተምህሮ ብቻ አይደለምና፤ እርሱም ግንዛቤ

(ልባዊነት) አለው:: ስለ ዕዲስ ሕይወት ግንዛቤ (ልባዊነት) እንዳለን ሁሉ፣ በአካልም ውስጥ ካለን፣ ለዚሁ የግድ ግንዛቤ ይኖረናል:: አንዳንዶች ጠላቶቻቸውን ለመውደድ ቁርጥ ሐሳብ እንዳደረጉ፣ ውሸት መናገርም ኀጢአት በመሆኑ፣ ይህም የክርስቲያን ተግባር ነውና፣ ለአካሉ ይህንኑ ያሳያሉ:: ውሸት መናገራችን ወይም አለመናገራችን አስፈላጊ የመሆኑን ያህል፣ ከዚህ የላቀው ግን፣ ብናደርግ በውስጥ የመረበሻችን ወይም ያለመረበሻችን ጉዳይ ነው:: ስለ እግዚአብሔር ውስጣዊ የሆነው ግንዛቤ (ልባዊነትና) ውስጣዊ የሆነ ለኀጢአት ያለ ቍጡነት የክርስትና መሠረት ናቸው፤ መሠረት የሆኑትም እነዚህ እንጂ ውጫዊ የሆኑት ደንቦች አይደሉም:: ስለዚህ በመርሑ መሠረት ሳንኖር ስንቀር አንድ ስሕተት ያለ መሆኑን ልብ እስካልን ድረስ በአካሉ መርሕ መሠረት መኖር ብዙ ጥቅም የለውም:: መስማትና ማየት ሁለቱ የተለያዩ ነገሮች ናቸው:: ልባዊነት ሳይነገረው የሚያይ ውስጣዊ እሳቤ ነው:: የመለኮታዊ ብርሃን ወደ እኛ መግባት ስለ እግዚአብሔር ሊኖር የሚገባንን ግንዛቤ (ልባዊነት) የሚያሳድር ከሆነ፣ በእግዚአብሔር ላይ ስለ ተፈጸመም በደል ግንዛቤ የሚሰጥ ከሆነ፣ ደግሞም የአካል ራስ በሆነው በክርስቶስ ላይ ስለሚፈጸመው እካሄድ እንደዚሁ ግንዛቤ የሚሰጥ ከሆነ፣ ስለ አካልም ተመሳሳይ የሆነ ግንዛቤ ሊሰጥ ይችላል:: የአካሉ አባላትን ሲያሳድድ ራሱን ከኢየሱስ ጋር እያጋጨ መሆኑን በማሳየት፣ ለጳውሎስ ስለ አካል ግንዛቤ የሰጠው ከእግዚአብሔር የሆነው ብርሃን ነበር:: ከመገለጥና ከሕይወት የሆነው ልባዊነት ከሌለ፣ ሁሉም በርግጥ ባዶ ነው::

## እርስ በርስ እንድትዋደዱ

እንግዲህ "የአካል-ልባዊነት ስላልኩት፣" ልዩ የተፈጥሮ ችሎታ አካሄድ፣ ለክርስቶስ አካል ያለውን ስስነት (ሴንሰቲቭነስ) ገልጬ ለማሳየት ልሞክር:: ከሁሉ አስቀድሞ በፍቅር ረገድ ይሠራል:: "እኛ ወንድሞችን የምንወድ ስለ ሆንን ከሞት ወደ ሕይወት እንደ ተሻገርን እናውቃለን" (ዮሐንስ 3፥14):: የአካሉ ብልቶች የሆኑ ሁሉ ይወዳሉ:: ይህ አስደናቂ ነው:: እስከሚነገራቸው ድረስ መቆየት አያስፈልጋቸውም:: ስለ ፍቅር ያሰቡ ወይም አያስቡ ከመቅጽበት ያፈቅራሉ:: ምክር ያስፈልጋቸው ይሆናል፤ ይሁን እንጂ ይህ ምክር የሚሰጠው ያላቸውን ለመቀስቀስ ነው:: አንድ ወዳጄ የመጀመሪያ ልጁ በእቅፉ ላይ እንዲሆን ሲደረግ፣ ልቡ በፍቅር መፈንቀሉን እንደ ነገረኝ አስታውሳለሁ:: ልጁን ለመውደድ የአባት ግዴታ መሆኑን ሰው እንዲነግረው አላስፈለገም:: ፍቅርን ከዚያው ላይ አገኘው:: አንድ ወንድም ማን ይሁን ምን፣ ክርስቲያን





መሆኑን እንዳወቃችሁ ልባችሁ ለእርሱ በፍቅር መፈንቀሉ ይህስ እውነት አይደለምን? ይህ የአካል ግንዛቤ (ልባዊነት) ነው::

በመከፋፈል ረገድም እንደዚሁ ይሠራል:: በፍቅር ረገድ ገቢርና (active) አወንታዊ ነው፤ በመከፋፈል ረገድ ግን ተገብሮና (passive) አሉታዊ ነው:: የአካልን ምንነት በእውነት ለተገነዘቡት፣ መከፋፈል ሁሉ፣ እና ለመከፋፈል የሚፈጸመው ማንኛውም ጥረት ሁሉ በእጅት የሚሰቀጥጥ (የተጠላ) ነው:: በክርስቲያኖች መካከል ልዩነት ሲፈጥሩ መገኘት፣ ለእነርሱ (ለሚያደርጉት) ወደ ባዕድ ዓለም ማሽቀልቀል ነውና:: በቤተ እምነት ከብር ማግኘት ትክክል ይሁን አይሁን፣ የክርስቶስን አካል የሚያውቁት ሁሉ ግን፣ ይህን መፈጸም የማይቻል መሆኑን ያውቃሉ:: የመከፋፈል መንፈስ፣ በትውፊትና በአገልግሎት የቱንም ያህል የተወደሰ ይሁን፣ ሕይወት ያገኘ ሰው የሚታገሠው ዐይነት አይደለም::

አሁንም፣ መለያየቶችና ቡድኖች ዛሬም በክርስቲያኖች ዘንድ እጅግ የተለመዱ ሆነዋል:: ከመንፈስ የተወለዱ በጌታ ዙሪያ የተሰበሰቡ የሃያ አማኞች አንድነት ሊኖር ይችላል:: ከዚያም አንድ ወንድም ይመጣና ጥቂት ወገኖች የሚገኙበት ቡድን ይፈጥራል:: ያ አካል አይደለም፤ አካል ሊሆንም አይችልም:: ይሁን እንጂ፣ በእርሱ ያለንን አንድነት እያወቅን፣ እንደነዚህ ያሉ ነገሮችን እንድንፈጽም የምናስብ ከሆነ ስሕተት እየሠራን መሆናችን ወዲያውኑ አይሰማንምን? ካልተሰማን ግን፣ አንድ የጐደለ ነገር አለ ማለት ነው:: አካል ምን ማለት እንደ ሆነ ለእኛ ትርጉም የሚሰጥ ከሆነ፣ ከውስጥም ሆነ ከውጭ የሚከፋፍል ነገር ሁሉ ዘግናኝ ይሆናል:: መከፋፈልን ለመፍጠር መጀመር እንኳ የውስጥ ሰላማችንን ማጣት ነው:: እንዲህ መቀጠል እንደማንችል እናውቃለን:: የአንድ ሕይወት ግንዛቤ (ልባዊነት) አይፈቅደውም፤ ይህም በቂ መልስ ነው::

ይህ አስተምህሮ አይደለም፣ ግን በክርስቶስ ኅብረት ያለን ሕያው ልባዊነት ነው፤ እርሱም እጅግ ውድ የሆነ ነገር ነው:: ቅጽበታዊ ሕይወት ወደ እኛ ይመጣል፤ በእኛ ውስጥ አዳጊና ጥልቅ የሆነ "አንድነትን" ይቀሰቅሳል:: ከዚያም በራስ ወዳድነት አንኖርም፣ በራስ ብቃት የሚተማመን ክርስቲያናዊ ሕይወትም ሊኖረን አይችልም:: "ምንጊዜም ብቻን መጓዝ" የሚለውን የቢራቢሮን ተፈጥሮ ትቶ፣ የንብን ባሕርይ ማለትም ሁልጊዜ ከቀፎው የመሥራትንና (የማከናወንን) ዘወትር ለራስ ሳይሆን ለሁሉ የመሥራት ባሕርይን በእኛ ውስጥ አሳድሮአል:: የአካል ልባዊነት ማለት ራሳችንን በእግዚአብሔር ፊት እንደሆንን የምናይበት

ነው፤ ይህም እንደተነጠለ ጓድ (አሐድ) ሳይሆን አንዱ በሌላው እንደሆኑ (እንደማይነጣጠሉ) አባላት ነው:: ::

ኦሐዶች (ቡድኖች) የተለየ ጥቅም የላቸውም፤ ምንም ዐይነት አገልግሎት አይፈጽሙም፤ በቀላሉ ይዘነጋሉ ወይም አስቸጋሪ ሁኔታ ሲያጋጥም በቀላሉ ሹልከ ብለው ያመልጣሉ:: ይኑሩም አይኑሩም ማንም ግድ የለውም:: በአሐዝ ውስጥ እንኳ ቦታ የላቸውም:: አባላት የሆኑት ግን ከዚህ የተለዩ ናቸው:: በአካሉ ውስጥ ተቀማጭ ሊሆኑ አይችሉም፤ ተመልካች ሆነው መቆም አይችሉም:: እንደ ተመልካች ያለ ጉጂ ማንም የለምና:: በነገሮች ላይ የይፋ ድርሻ ይኑረን ወይም አይኑረን፣ ይህ ግምት ውስጥ አይገባም፤ አለመገኘታችን ስለሚያጉድል፣ ምን ጊዜም ሕይወት መስጠት አለብን:: "ምንም አላጉድልም" ማለት አንችልም:: ሌሎች እየሠሩ ሳለ፣ እንደ ዐልፎ ሃጅ (መንገደኞች) በስብሰባዎች ላይ መገኘት የለብንም:: እኛ አካሉ ነን፤ በተለይ ደግሞ የአካሉ ብልቶች ነን፣ ሕይወት የሚፈሰውም ሁሉም ብልቶች (አባላት) አገልግሎታቸውን ሲፈጽሙ ነው::

ሁሉም ከሕይወትና ከሕይወት ምንጭ ጋር ታስረዋልና:: ራስ የሰው አካል ሁሉ የሕይወት ምንጭ ነው:: በእርሱ ላይ ጉዳት ቢደርስ የእንቅስቃሴ ቅንብር ሁሉ ያቆማል:: ራስ የሌለው አካል ሕይወት ወይም የሕይወት ልባዊነት የለውም:: እንደ ክርስቶስ አባልነታችን፣ ከእርሱ ዐዲስ ሕይወትን እንቀበላለን፤ ይሁን እንጂ ያ ሕይወት "በወልድ" ነው፤ ከእርሱ ተለይተን ተሸከመን የምንጓዘው ነገር አይደለም:: ለትንሽ ጊዜ ከክርስቶስ ብትለዩን፣ ሕይወት አይኖረንም:: በእኛና በእርሱ መካከል ለአፍታ ያህል ጥላ ሲያጠላ ምን እንደሚሆን እናውቃለን:: ሕይወታችን በእርሱ ነውና፤ በራሳችን ምንም ዐይነት ሕይወት የለንም:: ወልድ ያላቸው ሕይወት አላቸውና::

ስለዚህ እግዚአብሔር "ራስ ከሆነው ጋር እንድንጣበቅ" እንጂ ከአባል ወዳጆቻችን ጋር እንድንጣበቅ አይነግረንም:: ይህ የአንድነት (የኅብረት) መንገድ ነው፤ ክርስቶስ አልተከፈለምና፤ እርሱ አንድ ነው:: እርሱን አጥብቃችሁ ያዙ፤ ከዚያም ይህንኑ ለሚያደርጉት በልባችን ውስጥ ድንገተኛ ፍቅር ሲፈልቅ እናያለን::

አንድ መሆን የክርስቶስ እንጂ የእኛ አይደለም:: የእርሱ በመሆናችን አንድ ነን:: ለምሳሌ፣ ስለምንወደው ብቻ ከአንድ ወንድም ጋር ኅብረት አለን ማለት በአንድነት ላይ ማመጽ ነው:: አንዳንዶችን እንደ ሌሎች የኅብረት አባላት





አድርገን ወዲያውኑ መቀበል ቢያቅተን፣ ይህ በኅብረታችን ላይ ተጽዕኖ እንዲኖረው መፍቀድ ማለት ሐሰተኛ መሠረቱን ማጋለጥ ነው:: ወይም ደግሞ ለአንድ ወንድም አንድ በጎ ነገር አድርገንለት ባለማመስገኑ ቅሬታ እናሰማለን? ያ የሚሆነው በመጀመሪያም ስለ ክርስቶስ ብለን፣ በመጀመሪያም እግዚአብሔር እኛን ስለ ወደደን ብለን ሳይሆን ምስጋናን ስለ ፈለግን ብቻ ነው:: ራስ ከሆነው ጋር ያለን ግንኙነት ጉደሎ በመሆኑ፣ አነሣሽ ምክንያታችን ስሕተት ነበር ማለት ነው::

አባል ወገኖቻችንን "የሙጥኝ ብለን መጣበቃችን" ወደ ግል ወዳጅነት ያመራል:: አካል ለእንደዚህ ዐይነቱ ሁኔታ ቦታ የለውም:: አንድ ክርስቲያን ከሌላ ክርስቲያን ጋር ጤነኛ ያልሆነ ወዳጅነት እስከሚዳብር ድረስ በፍቅር ቢናወዝ፣ ይህ ወዳጅነታቸው ያለጥርጥር መከፋፈልን ያመጣል:: ከሥጋ የሆነ አንድነት በስሕተት መሠረት ላይ የቆመና ውሎ አድሮም ወደ ሐዘን የሚመራ ነውና:: ሁለት አባላት ብቻቸውን እርስ በርስ የሚጣበቁ ከሆነ፣ የሚገልጹት ፍቅር ሙሉ በሙሉ ከእግዚአብሔር ላይሆን ይችላል ብለን ልንሠጋ እንችላለን:: "እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ" የሚለው አንድም በአካሉ ዙሪያ ነው፤ በመሆኑም ክርስቶስ ተኰር ነው፤ አሊያም ስሕተት ነው:: ካልተሠዋ ምርጫ እግዚአብሔር ይጠብቀን፤ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ መንፈስ ቅዱስን እንድንከተልም ይርዳን::

የመንፈስ ቅዱስ ቅባት በክርስቶስ ሕፃን (ልጅ) ለሆነው ሁሉ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው (1ዮሐ 2፥18-20፤ 27):: ክርስቶስን ራስ አድርገን ስንቀበለው መቀባትን እንቀበላለን፤ የቅባቱ አለመኖር ከእርሱ ጋር ተባብረን እንዳልነበር በርግጥ ብርቱ ማስረጃ ነው (ሮሜ 8፥9):: ይህ መቀባት የውስጥ መሆኑን ዮሐንስ ይነግረናል፤ የመንፈስን ትምህርት ማለትም፣ "ሁሉንም ነገር" በክርስቶስ ሕፃን ለሆኑት በመግለጥ ያሳያል፤ "ሁሉን ነገር" ሲባልም ቅዱሳት መጻሕፍትን ብቻ ማለቱ አይደለም:: ምን ማለቱ ነው? እስቲ ተግባራዊ የሆነውን ማስረጃ እንመልከት:: ለምሳሌ ወደ ሆንግ ኮንግ ጉዞ ማድረግ ወይም አለማድረግ እንዳለብኝ ለማወቅ እፈልጋለሁ:: እንዴት ልወስን? ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስን አሻለሁን? ወይስ ትክክል የሆነውን ወይም ስሕተቱን ለመወሰን አእምሮዬን አዘጋጃለሁን? አይደለም፤ ብዙ ጊዜ እንዳልነው የሕይወታችን መሠረት "ጥሩ ወይም መጥፎ" ሳይሆን መቀባት ነው:: "መንፈስ ቅዱስ በዚህ ጉዳይ ላይ አለበትን? ወደ ጉዳዩ ስቀርብ ልቤ ባዶ ነው ወይስ ሙሉ?" የስሜት ወይም የማወዳደር ጉዳይ ሳይሆን ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ልመና ነው::

"መንፈስ ሕይወትን ይመሰክራልን?" አስተማማኝ የሆነው መፈተኛ ይህ ነው:: ለጊዜው የመረጥነው መንገድ በራሱ ፍጹም ትክክል ሊሆን ይችላል፤ ዋናው ጉዳይ ግን መንፈስ ቅዱስ በዚያ መንገድ መንቀሳቀሱ ላይ ነው::

የእግዚአብሔር ልጆች ሕይወት ቀናነት ከዚህ ላይ ይገኛል:: ብዙ ጥያቄ ማቅረብ አያስፈልግም:: ለቅባቱ አለመታዘዝ በአፋጣኝ ከጌታ ጋር ባለን ግንኙነት ላይ አስቸጋሪ ነገር ይፈጥርብናል፤ በአንጻሩ ስለ መንፈስ ቅዱስ ማሰብ ግን ምንጊዜም ሕይወትና ሰላም ነው (ሮሜ 8፥6)::

መንፈስ ቅዱስ አንድ ስለ ሆነ፣ ልጆቹ እንዲህ ሲንቀሳቀሱ፣ ስለ ኅብረት ችግር አይኖርም:: አካል አንድን ሕግ ያውቃልና፤ ይኸውም የመቀባትን ሕግ ነው:: ደንቦች በኅብረተሰብ ዘንድ አስፈላጊ ናቸው፣ ለአካሉ ግን አይደሉም:: የብሉይ ኪዳንን ደንብ አስመልክቶ ፈሪሳውያን አክራሪዎች ነበሩ:: ከሕጉ ዝንፍ አላሉም፤ ደንቦችን ያውቁ ነበር፤ ምናልባት እኛም እናውቃለን ብለን ሊሰማን ይችላል:: ይሁን እንጂ የተርሴሱ ሳውል እንዳደረገው ስለ እነዚያ ደንቦች ያለን ዕውቀት የመንፈስ ቅዱስን ድምጽ እንዳንሰማ ቢያደርግስ? እውነት ነው፣ ሕጉን ያውቃል፤ ሆኖም በሰማይ ላይ ስላለው የሰው ልጅ የሚያውቀው ነገር አልነበረም (ሐሥ 7፥55-56):: መንፈስ ቅዱስን ማሳዘን ማለት ሰማያዊ ሰው መሆናችንን ጨምሮ የሕይወታችንን ግንዛቤ (ልባዊነት) ማፈን ነው:: እጅና እግር በማእከላዊ ቁጥጥር ሥር እንዲሆኑ በማድረግ የነርቭ ጉዳትን የማድረስ ያህል ራስ ከሆነው ጋር ባለን ግንኙነት ላይ ጉዳት ማድረስ ነው:: ይህን ብናደርግ፣ ልክ እንደ ሳውል ሳንዘገይ ማሳደድንና ግድያን ስናካሄድ እንገኛለን::

የሳውል የኅብረት ሕይወት የጀመረው፣ "ጌታ ሆይ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ?" ባለ ጊዜ ነው:: ምስጢሩ ያ ነው:: "ራስ ከሆነው ጋር መጣበቅ" ማለት በመንፈስ አማካይነት ክርስቶስን *መታዘዝ* ማለት ነው:: መንፈስ ቅዱስን መከተል ማለት በሁሉም ነገር ለጌታ ኢየሱስ መገዛት ማለት ነው:: መንፈስ ቅዱስ ያን መታዘዝ በአባላት ላይ ከቶ፣ በፍጹም፣ አይጭንም፤ ይሁን እንጂ በዚህ ቅባት የሚኖሩ ሁሉ ከመቅጽበትና በደስታ ለክርስቶስ ራሳቸውን ሁልጊዜ ያስገዛሉ፤ ይህን በማድረግም አንድነታቸውን ፈልገው ያገኛሉ:: ታዲያ፣ አቤት፣ እርሱን ጥርጥር እንደ ሌለበት ጌታ ሆኖ ማየት እንዴት መባረክ ነው!





# ምዕራፍ ስምንት

## ሕይወትን ማገልገል

ዛሬ ለቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር እጅግ ከፍተኛ ዐላማ በሕይወት አገልግሎት ውስጥ ራሷን በፍቅር እንድትገነባና በነገር ሁሉ ወደ ክርስቶስ እንድታድግ ነው:: በኤፌሶን ምዕራፍ 4 ላይ የተቀመጠለት ግብ ይኸው ነው:: በተጨማሪም ጳውሎስ በ1ቆሮንቶስ ምዕራፍ 13፣ ቀደም ሲል አይተነው በነበረው ማለትም ስለ አካል የተገለጸውን ምንባብ ተከትሎ በመጣው ላይ፣ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ ምንጊዜም የሚጠቀመው ስጦታዎችን ሳይሆን ፍቅርን መሆኑን ያሳያል:: ስጦታዎች በሥራዎችና በንግግር፣ በታምራት፣ በፈውሶች፣ በትንቢትና በመሳሰሉት በውጫዊ (በሚታይ) ሁኔታ ይገለጣሉ:: ፍቅር በመስቀሉ በኩል በአባላት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ የውስጥ ሥራ ፍሬ ነው:: ስጦታዎች የእግዚአብሔር ጊዜያዊ ዘዴዎች - እንደ እውነቱ ከሆነም የእግዚአብሔር ስልቶች ናቸው፣ ይሁን እንጂ አካል ራሱን የሚገነባው በፍቅር ነው (ኤፌ .4፥16):: እናም ሁሉ ነገር ካለፈ በኋላ፣ ፍቅር ጸንቶ ይኖራል::

ከዚህ ላይ የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ለማስተዋል ስንመጣ ልብ የምንለው የአንድ ነገር ምሳሌ አለ፡ በጳውሎስ መልእክቶች ላይ ተዘውትረው አጽንዖት የሚሰጥባቸውን ከሁለት መልካም ነገሮች ውስጥ የተሻለ የሆነውን አመለክታለሁ:: አንዳንድ ጊዜ በአንድ በተወሰነ ዐውድ ውስጥ አጽንዖቱ ብርቱ ነው፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ ውስጠ ታዋቂ ነው፣ ይሁን እንጂ ትኩረት የሚደረግበት ነው:: በዚህ አጋጣሚ በጽናት ላይ አጽንዖት ያደርጋል:: በ1ቆሮንቶስ ላይ ከፍቅር ጋር ሲያወዳድራቸው፣ ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች ያብራራ ቢሆንም እንኳ፣ በአንጻራዊ ፋይዳቸው ላይ የሐሳብን ትኩረት ይሰባል (ቁ 8-11)::

እግዚአብሔር መንፈሳዊ ስጦታዎችን በአንድ በተወሰነ አጋጣሚ ውስጥ በዘላቂነት እንዲቀጥሉ ላያቀዳቸው ይችላል፤ ስጦታዎች ስጦታ ባለው ሰው መንፈሳዊ አቋም ላይ መወሰን የለባቸውም:: የእነርሱ አገልግሎት ነባራዊ (objective) ነው፤ በአንጻሩ ግን የእግዚአብሔር የመጨረሻ ዐላማ በሰው ውስጥ መንፈሱን በማስቀመጥ፣ ይኸውም በጊዜያዊነት በእርሱ ላይ በማደር ሳይሆን የውስጥ ጉዳይ (subjective) ነው:: ስለዚህ ስጦታዎች "መንፈሳዊ" ተብለዋል፤ ይህም ተቀባዩ መንፈሳዊ በመሆኑ ሳይሆን ስጦታዎቹ ከመንፈስ ቅዱስ ስለ መጡ ነው::

ሰዎች አግራሞታቸውን ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን ተስፋችን እነዚያ የሚመጡት ሁሉ ከወትሮው የተሻሉ ሰዎች እንደሚሆኑ ነው፤ ይህም የላቀ አስተምህሮ በመማራቸው ወይም በሰባኪነት የላቀ ኪሂል በማግኘታቸው አይደለም፡፡ ፍላጎት ያለው ለታላላቅ ስጦታዎች ሳይሆን እግዚአብሔር ሊጠቀምባቸው በሚችል ሰዎች ሁሉ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ሌሎች በእኛ ስጦታዎች ይታገዛሉ፤ ነገር ግን ሆነን በተገኘነው ይደናቀፋሉ፡፡ ሕያው የሆነው ውሃ ንጹሕ ባልሆኑ ዕቃዎች የግድ ሊቀመጥ ነው፡፡ ይህ በራሱ አሳፋሪ ነው፡፡

ወደዚያ የመግባታቸውን ሁኔታ ከማስተዋላቸው ከዓመታት በፊት እግዚአብሔር ተገቢ ያልሆኑት ሰዎች ቃሉን እንዲናገሩ መፍቀዱ እውነት ነው፤ ነገር ግን ማንኛችንም ከዚያ ላይ እንድናቆም አይፈልግም፡፡ በዚያ መንገድ ለተወሰነ ጊዜ ልንሄድ እንችላለን፤ ነገር ግን ሥርዐት በማስገባትና በቅጣት መሣሪያነት እግዚአብሔር የመቅረጽ ሥራውን በእኛ ውስጥ ሲሠራ ሳለ፣ ስንናገር የነበረውን በቅጡ አለማወቃችንን እያደር የምንገነዘብ መሆናችን እውነት አይደለምን? ስጦታዎች ግልጽ ተደርገውም ሆነ ሳይደረጉ፣ እርሱ እኛ ለመናገር ወደምንችልበት ደረጃ (ሥፍራ) እንድንደርስ ያስባል፣ ምክንያቱም እኛ የምንለውን ስለሆንን (ስለምንመስል) ነው፡፡ በክርስቲያን ተመክሮ ውስጥ የእግዚአብሔር መንፈሳዊ ነገሮች ውጫዊ የመሆናቸው ጉዳይ ያውም በስጦታ መልክ እያነሱ እያነሱ፣ በውስጣዊ ረገድ ያውም በሕይወት ረገድ እየጨመሩ እየጨመሩ የሚሄዱ ናቸው፡፡በዘለቄታ ሲታይም አንድ ሥራ ዋጋ አለው የሚባለው በጥልቀቱና በውስጣዊ ገጽታው ነው፡፡ ጌታ ራሱ ለእኛ እያደር ከሁሉ በላይ ሲሆንልን፣ ስጦታዎቹንም እንኳ ጨምሮ ሌሎቹ ነገሮች፤ እያነሱብን ይሄዳሉ፡፡ ከዚያም፣ አንድ ዐይነት አስተምህሮ ብናስተምርም፣ አንድ ዐይነት ቃሎች ብንናገርም እንኳ በሌሎች ላይ የሚኖረው በጎ ተጽዕኖ የተለየ ይሆናል፡፡ ይኸውም በእነርሱ ላይ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ቀጣይ በሆነ ጥልቀት በመከሠት (በመግለጥ) ጭምር ነው፡፡

እግዚአብሔር ለባሪያዎቹ የትንቢት ስጦታ ይሰጣል፤ ለቤተ ክርስቲያንም ነቢያትን ይሰጣል፡፡ ነቢዩ ደግሞ እግዚአብሔር የሠራው፣ የመንፈስ ቅዱስን የማበጀት ሥራ ተመክሮው ያደረገ ታሪክ ያለው ሰው ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ሰባኪያን እንሁን በሚሉት አማኞች፣ አንድን ስብከት ለማዘጋጀት ምን ያህል ቀን እንደሚያስፈልግ እንጠየቃለን፡፡ መልሱ፣ ቢያንስ ቢያንስ ዐሥር ዓመት ምናልባትም ወደ ሃያ ዓመታት ይጠጋል ነው! በዚህ ረገድ እንዲህ የሚለው ምሳሌ እውነት ነው፤ "ዕድሜ የጠገበው የላቀ ነው፡፡" ሰባኪው የተሰበከውን





ቁም ነገር ያህል ለእግዚአብሔር ወድ ነገር ነውና፡፡ እግዚአብሔር የዘሬ መልእክቱ እንዲሆኑ ዐስበ የሠራቸውን ነቢያቱ አድርጎ ይመርጣልና፡፡

አስተምህሮን መገንዘብና እግዚአብሔርን ማወቅ ሁለቱ የተለያዩ ነገሮች ናቸውና፡፡ መንፈሳዊ ነገሮች በአእምሮ ከቶ ተይዘው አያውቁም፡፡ ለመልካም ቃላት ብዙ ትኩረትን እንሰጣለን፤ እግዚአብሔር ግን መልካም ሰዎችን ይሻል፡፡ አንዳንዶች ይናገራሉ፣ እኛም ርዳታ አግኝተናል፤ ሌሎችም ያንኑ ቃል ይናገራሉ፣ ውጤቱ በዶ ነው፡፡ ልዩነቱ ያለው በራሳቸው በሰዎቹ ማንነት ላይ ነው፡፡ በመንፈሳዊ ፋይዳ (እሴት) ምትክ የአእምሮ በሆነ ነገር ቤተ ክርስቲያንን ልናታልል አንችልም፡፡ ቤተ ክርስቲያን ታውቃለች! በእግዚአብሔር ፊት ያለ ሰው ተተቶ ሌላ ነገር የእርሱ ትክ ሊሆን አይችልም፡፡

ስለዚህ ጥያቄው መሆን ያለበት የምንገረውን ቃል እንመስላለን? ነው፡፡ "ጌታ ሆይ፣ አንተንና የመስቀሉን ትርጉም፣ በእኔ ላይም የመንፈስ ቅዱስን ሠሪ እጅ ሳላውቅ በድፍረት ከመናገር አድናኝ፤ ዛሬም ጉድለትን ሁሉ በማስተካከል የሚያስፈልገውን ሥራ ሁሉ በእኔ ውስጥ ጀምር፤ የማውቀውን እናገርም ዘንድ ስበረኝ፤ ቀረጸኝ፤ ፈትናኝ፤ ሞክረኝም፡፡" ጩኸታችን መሆን ያለበት ይህ ነው፤ የማናውቀውን በእርሱ ስም መናገር የሚያገለግል ከሆነ የሚያገለግለው በጥቂቱ ነውና፡፡

## ስጦታዎችና ሕይወት

"የጸጋም ስጦታ ልዩ ልዩ ነው፤ መንፈስ ግን አንድ ነው፡፡ አገልግሎትም ልዩ ልዩ ነው፤ ጌታም አንድ ነው" (1ቆሮ 12፥4-5)፡፡ የኋለኛው ሐሳብ እቻነት ያለው ስለ ክርስቶስና ስለ አካሉ የጋራ ሕይወት በሚናገረው ከቍጥር 12 እስከ 27 ባለው ክፍል ላይ መሆኑን ቀደም ሲል አመልክተናል፡፡ ይሁን እንጂ በሁለቱ ሐሳቦች ውስጥ ሌላ ልዩነትን ልናስተውል የምንችል ይመስለኛል፤ ይኸውም በስጦታዎችና በሕይወት፣ ለአገልግሎት በዋለው መሣሪያና በተገለገለው ነገር መካከል ነው፡፡

ስጦታዎች ከክርስቶስ የሆነውን ለአካል የምሰጥበት ከመንፈስ ቅዱስ የተቀበልኳቸው መሣሪያዎች ናቸው፡፡ አገልግሎት (ወይም ማገልገል) የክርስቶስ የሆነውን ለአካል የምሰጠው ስጦታ ነው፡፡ እያንዳንዱ አገልግሎት ስለ ክርስቶስ የሆነውን አንዳንድ ነገር አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡ የሰው አካል ተግባራትን ልብ ለማለት ስለ ማየት፣ ስለ መስማትና ስለ መንቀሳቀስ በጳውሎስ ንጽጽር የተደረገው በስጦታዎች ላይ ሳይሆን በአገልግሎት ላይ ነው፡፡ ስለዚህ የተለያዩ

ሰዎች አንድ ዐይነት ስጦታ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ በዚህ ምንባብ ቋንቋ በተመለከተውም፣ ልዩ ልዩ ስለ ሆኑት "አገልግሎቶች" እንደ ሌላው ተመሳሳይ ነገር ሊባል አይችልም፡፡ እያንዳንዱ ልዩ ነው፡፡ ከሕዝቡ ጋር እንጋራው ዘንድ አንተ ወይም እኔ በተለይ ከጌታ የተቀበልነው ነገር ነው፤ እንዲያውም አካል ከዚህ ቀደም ከቶ ያልተቀበለው ነገር ሊሆንም ይችላል፡፡ ይህን "ክርስቶስን የመስጠት" በሚል የቀረበውን አገልግሎት፣ ለመፈጸም መንፈሳዊ ስጦታዎች ሌላ ሳይሆኑ መሣሪያዎች ናቸው፡፡ የማውቀውን ክርስቶስ ለአካል ለመስጠት እነርሱን ልጠቀም እችላለሁ፡፡

ይህ አስፈላጊ ነው፤ መንፈሳዊ መነቃቃት የተባለው በስሕተት መሠረት ላይ የቆመ መሆኑን በአያሌው ያሳያልና፡፡ ስጦታዎች ይፋ ሆነዋል፤ ነገር ግን ያለ ክርስቶስ ነው፤ ይህም አንዳች ጥቅም ላይ ሊውሉ የማይችሉትን እያሌ የወጥ ቤት ዕቃዎችን ገንዘብ እንደማድረግ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ከዚህም የከፋ ነው፤ ያለ ክርስቶስ፣ ስጦታዎች ባዶዎች ብቻ አይደሉም፣ አታላይም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ አንዳንዶቹ ከቶ የክርስቶስ አገልግሎት ሊሆን በማይችለው መልኩ አስመሳይ ሆነው ሊቀርቡ ይችላሉ፤ በአንጻሩ ግን ለአካል ዋና ጉዳይ የሚሆነው የእኛ ስጦታዎች ሳይሆኑ፣ በእነርሱ አማካይነት የምንገልጸው ለሟላችን እውን የሆነልን የክርስቶስ ዕውቀት ነው፡፡ በሐኪም ቤት ውስጥ ሁለት ነርሶች አንድ ዐይነት ማንኪያ ሊጠቀሙ ይችላሉ፤ ሆኖም ዋና ጉዳይ የሚሆነው በማንኪያዎቹ የሚሰጡት ነገር ነው፡፡ አንደኛዋ ውድና ፈዋሽ የሆነ መድኅኒት ልትሰጥ ትችላለች፣ ሌላዋ ደግሞ ማስታገሻ ብቻ፡፡ ዋናው ነገር የምናገለግለው ላይ ነው፡፡ የአካል ጤንነትና እድገት የሚመጡት ከክርስቶስ አገልግሎት ብቻ ነው፤ እንዲሁ ከስጦታዎች ሊመጡ አይችሉም፡፡ ስጦታዎች የሚፈለጉ ቢሆኑም ("ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል")፣ የክርስቶስ ትክ ከቶ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ የሥራ ግዴታችን "የምሰጠው ነገር አለኝን?" ብለን ራሳችንን መጠየቅና ክርስቶስን ለአካል እንዴት መስጠት እንደሚቻል በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት መማር ነው፡፡

ልዩ አገልግሎት እንዴት ሊኖረኝ ይችላል? ቀድሞ በአስተምህሮ ሳይሆን በሕይወት ነው፡፡ አብርሃም እምነትን የተማረው አስተምህሮን በመማር ሳይሆን በእግዚአብሔር መታመን ብቻ በተቻለበት ሁኔታ ነበር፡፡ አቤል በደም የሚገኘውን የይቅርታ ፋይዳ ከተመከሮ ተማረ፡፡ በመጀመሪያ መከራ፣ ተስፋ መቁረጥ፣ ተመክሮ *ከዚያም ሕይወት* ይቀድማሉ፤ ከዚያ በኋላ ደግሞ አስተምህሮ ይመጣል፡፡ እግዚአብሔር ሕይወትን የሚሰጠው ከተስፋ መቁረጥ





ስፍራ ላይ እንጂ፣ በፍለጋ፣ በጥናት፣ ወይም በማወዳደር አይደለም፡፡ ለማጥናትና ለማወዳደር ማንኛውንም ዕድል መጠቀም እንችላለን፤ በዚያ ላይ ግን አገልግሎታችንን አናገኘውም፡፡ እዚህ ላይ ሰባኪዎች ዘወትር ከቅዱሳት መጻሕፍት ዐዲስ ብርሃንና ለሰብከታቸው ርዲስ ዋና ሐሳብን በመፈለግ ለጉዳት የተጋለጡ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ወደ አገልግሎት የሚወስደው መንገድ በዚያ የለም፡፡ አገልግሎታችን የሆነው ከክርስቶስ ጋር ያለን ልዩ ተመክሮ ነው፤ በእኛ ውስጥ ተመክሮን የሚሠራውም የእምነታችን መፈተን ነው፡፡

ከዚህ ላይ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፋቸው መልእክቶች ላይ ጉልሕ የሆነ የአጽንዖት ለውጥ ወዳደረገው ሐሳባችሁን ልስብ እወዳለሁ፡፡ 1ቆሮንቶስ በዋናነት በስጦታዎች አገልግሎት ላይ ያተኩራል፤ 2ቆሮንቶስ ምዕራፍ 12 እና 14 ላይ ብዙ ስጦታዎች ተወስተዋል፦ ጥበብ፣ ዕውቀት፣ መፈወስ፣ ታምራት፣ ትንቢት፣ መናፍስትን መለየት፣ ልሳናት፣ መተርጐም፣ ወዘተ፤ እነዚህ ስጦታዎች የተሰጡት መላዋን ቤተ ክርስቲያን ለማነጽ በመሆኑ፣ በዚያ ላይ የተብራራው ጉዳይ፦ ልዩ ፋይዳቸው ምንድን ነው? የሚለው ነው፡፡ በሌላ በኩል ግን በሁለተኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 3 እና 4 ላይ፣ ጳውሎስ ስለ ራሱ አገልግሎት ለመናገር ሲነሣ በስጦታዎች ላይ ከቶ አያተኩርም፡፡ ይልቁን ክርስቶስ በውስጥ ስለ መቀረጹ ግልጽ በሆነ መልኩ ተጨንቆበታል፡፡ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ምንጭና ዋና ሐሳብ፣ በሸክላ ዕቃው ውስጥ ያለው 'መዝገብ'፣ ክርስቶስ ነው (2ቆሮ 4፥7)፡፡ "እንገፋለን እንጂ አንጨነቅም፤" "እስደዳለን እንጂ አንጣልም፤" "እንወድቃለን እንጂ አንጠፋም፤" ወይም "አልቆለታል - ሆኖም አላለቀለትም!" እንደምንለው ነው፦ ምስጢሩ *የዚህ መዝገብ* ድል አድራጊነት በጳውሎስ ውስጥ መኖሩ ነው፡፡ በእርሱ ውስጥ እየሠራ ያለው የክርስቶስ ሞት ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር የሚጋራው የሕይወት ምንጭ ሆኖአል፡፡

በቍጥር 10 ላይ "የኢየሱስን ሞት ዘወትር ተሸክመን እንዞራን" (አመት) የሚለውን የጳውሎስን አገላለጽ "በእኔ ላይ ሞትን የሚሠራውን ኢየሱስን ለሞት መዳረግ" ብለን ልናመለከተው እንችላለን፡. ይህ የሞት ሥራ፣ በሌላ ስፍራ ላይ እንዳመለከትኩት፣ በሮሜ ምዕራፍ 6 ላይ ለአንዴና ለመጨረሻ ከሆነው ሞት የተለየ ነው፤ ይኼ በእግዚአብሔር ልጅ ውስጥ የዕለት ተዕለት ሂደት (ሞት) ነውና፡፡ ከሁሉ አስቀድሞም በእኔ ውስጥ ወዳለው ሕይወት ይመራል (ቍ 10)፡፡ ይሁን እንጂ፣ ከዚህ ላይ ያለው ሐሳባችንም ይኸው ነውና፤ እዚህ ላይ አይቆምም ሕይወቱም *በእናንተ እንዲሠራ* (ቍ 12) ባለው መሠረት፣ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁንና፣ ሳያቆም ይጓዛል፡፡

ጳውሎስ የሚነግረን ሕይወት፣ ቤተ ክርስቲያንን የሚያገለግልበት መሣሪያ ነው፤ ይህን በማለቱም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እውነተኛ አገልግሎት ሁሉ የተመሠረተበትን ጉዳይ ይገልጻል:: ሞት በእግዚአብሔር ባሪያ ውስጥ በመሥራት ሕይወትን ያስገኛል፤ እርሱ ሕይወት ያለው በመሆኑም ሌሎች ሕይወት አላቸው:: ቤተ ክርስቲያን ትቀበላለች፣ ምክንያቱም አንዳንዶች መስቀሉን ለመሸከም ፈቃደኞች ናቸው:: ዋናው ጉዳይ የኢየሱስን ሞት መቀበላቸው ነው:: ይህ ለቆሮንቶስ ሰዎች የጳውሎስ ዐዲስ ትምህርት ነው:: በፈተናቸውና በመከራቸው እግዚአብሔር እንዲሠራ በመፍቀድ፣ እርሱን በማመስገንና ለፈቃዱ በመገዛት ወደ ሌሎች ሕይወትን እንዲያመጣ ልጆቹ ያመቻቹለታል:: ይሁን እንጂ ይህን ውድ አገልግሎት የሚቀበሉት ይህን ዋጋ የሚከፍሉት ብቻ ናቸው:: ሕይወት የሚለቀቀው በሞት በኩል ነውና፣ በዚህም ብቻ ነው:: በአንጻሩ ግን ስጦታዎች በራሳቸው ይህን ያህል ውድ አይደሉም፤ ስጦታዎች እንድንፈጽምና እንድንናገር የሚያስችሉን ሁሉ የእግዚአብሔር ባሮች እንደመሆናችን በእኛ ላይ ጉልሕ የሆነ ጉድለት ከቶ ሊያስከትሉ አይችሉም::

ስለዚህ አካል የተገነበባቸውን ሁለት አገልግሎቶችን አናያለን፤ እነርሱም ስጦታዎችና ሕይወት ናቸው፤ እንዲህ በማለትም ራሳችንን ልንጠይቅ እንችላለን፦ የእግዚአብሔርን ሉዐላዊ ዐላማ በየትኛው ነው የምንለየው? እንዲህ እመልሳሁ፦ በስጦታዎች አይደለም፣ ግን በሞት በኩል እውን በሚሆነው ከክርስቶስ በሆነው ሕይወት ነው:: ስጦታዎች መወገድ የለባቸውም (1ጢሞ 4፥14፤ 2ጢሞ 1፥6፤ 1ጴጥ 4፥10)፤ ይሁን እንጂ በእነርሱ ላይ በእጅጉ መታማመን በመንፈሳዊ ጉዳዮች ረገድ "እንደ ሕፃን ማሰብ" ነው (1ቆሮ 13፥11):: ጳውሎስ በሁለተኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 3 እና 4 ላይ ታላቅ ዋጋ ሆኖ መታየት ስላለበት ቁም ነገር ያመለክታል፤ ይኸውም እርሱ በመራን መንገድ በኩል ስለ ክርስቶስ ካገኘነው ዕውቀት የተነሣ፣ መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ የቀረጸውን ሕይወት ለወንድሞቻችን ማገልገል ነው::

ዛሬ ብዙዎች በስጦታዎች ያገለግላሉ፤ በንጽጽር ሲታይ ደግሞ ጥቂቶች በሕይወት ያገለግላሉ:: አማኞች በጌታ ገና ለጋ በሆኑበት፤ በእነርሱም ውስጥ የመስቀሉ ሥራ መጠነኛ በሆነው መንፈሳዊ ታሪካቸው በተገደበበት ዘንድ ይህ ስሕተት ላይሆን ይችላል:: ከዚያም ለጋ እብያተ ክርስቲያናትን ለማነጽና ነፍሳትን ለማዳን፣ መንፈሳዊ ስጦታዎች ልዩ ፋይዳ ሊኖራቸው ይችላል:: ይሁን እንጂ በራሳቸው የበሰለት ምልክቶች አይደሉም፤ ከቶ የሚኮራባቸውም አይደሉም:: የእነርሱ መታየት እምነትን ይመሠርታል፤ ይሁን እንጂ በቤተ





ክርስቲያን ውስጥ እያደር በሚያድገው መንፈሳዊ ሕይወት ልኬት እንጻር፣ በእነርሱ ላይ የመታመኑ ጉዳይ ይቀንሳል፣ ተከትሎአቸውም የትዕቢት አደጋ ይመጣል:: እንዲህ ያለው እድገት የተነገረው ወይም የተፈጸመው ነገር የግድ የተለየ ነው ማለት አይደለም፣ ሆኖም ምንነቱ በእግዚአብሔር ባሪያዎች ውስጥ ያድጋል:: ቃላቱ አልተለወጡ ይሆናል፣ ነገር ግን ጥልቅ ከሆነ ውስጣዊ ልባዊነት መንጭተዋል:: ስጦታዎች ሳይሆኑ የመስቀሉ ሥራ ነው፤ ይህም የሰው መንፈሳዊ አቋም መለኪያ ነው:: እግዚአብሔር በሰጣቸው ቃሎች የሚኩራሩት ቂሎች ብቻ ናቸው፤ አስፈላጊ ከሆነ በአህያም እንደሚናገር አላሳየም እንዴ!

እንግዲያውስ፣ እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ስጦታዎችን ተጠቀምን ወይም አልተጠቀምን ፋይዳው እስከዚህም ነው:: ዋናው ቁም ነገር ከጌታ የተቀበልነውን ሕይወት የማስተላለፉ ጉዳይ ነው:: እግዚአብሔር አንዳንድ ግለሰቦች የተወሰኑ ስጦታዎችን እንዲይዙ መፍቀድ አለመፍቀዱ፣ ወይም እነርሱንም የመጨመሩ ሁኔታ፤ የእርሱ ሥራ ነው:: ይሁን እንጂ አንድ ነገር ርግጥ ነው፤ እግዚአብሔር *በቤተ ክርስቲያኑ* እድገት ውስጥ፣ ሕይወትን በከፍተኛ ደረጃ ሲጠቀምበት ስጦታዎችን ግን በዝቅተኛ ደረጃ ይጠቀማል:: ቢያንስ ቢያንስ ስጦታዎች በጉልሕ ከሥተታቸው እየቀነሱ ሲሄዱ ሕይወት ግን ይጨምራል:: ንግግር፣ ርቀብ አንደበት፣ ታምራት ወይም ልሳናት ለቤተ ክርስቲያን ውጤታማ አገልግሎት ቅድመ አስፈላጊ ጉዳዮች አይደሉም:: እግዚአብሔር ለተወሰነ ወቅት ሰዎችን አፉ አድርጎ ይጠቀምባቸዋል:: ከዚያም ነገሮችን በተመለከተ እነርሱን ገለል ማድረግ ሊመርጥ ይችላል:: ነገር ግን የአካል ሕይወት ይቀጥላል:: ስለዚህ ሕይወትን ከሚሰጠው ሕይወትን ካላገለገሉ በቀር፣ በስጦታዎች መታመን ቂልነት ነው::

## በሞት የቤተ ክርስቲያን ጥቃት

በምድር ላይ ሳለ ኢየሱስ ራሱ የመለኮታዊ ሕይወት መቀመጫ ነበር:: ሰዎች እርሱን በዳሰሱ ጊዜ እግዚአብሔርን ዳሰሱ፤ እርሱን ባዩ ጊዜ እግዚአብሔርን አዩ:: የግጻዌ መለኮት ሙላት ሁሉ በአካላዊ መልክ በእርሱ ላይ አደረ (ቆላ 1፥19፤ 2፥9):: ዛሬ ያ መለኮታዊ ሕይወት ለአካሉ ለቤተ ክርስቲያን በዐደራ ተሰጥቶአል:: እስከ እግዚአብሔር ሙላት ድረስ እንድትደርስ ዕድል የተሰጣት የዚያ ሕይወት መቀመጫ ናት (ኤፌ 1፥23፤3፥19):: በክርስቶስ የነበረው ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ላይ ይታይ ዘንድ የታቀደ ነው:: እግዚአብሔር እርሷን ከዚህ የተወበት ዐላማ ይኸው ነው:: የልጁን ሕይወት መያዝና ማሳየት አለባት::

እርሱ ብርሃን፣ መንገድና እውነትም ነው፤ እርሱ ወልድ፣ ንጉሥ፣ 'እኔ ነኝ' ያለውም ነው:: ነገር ግን እጅግ ልዩ የሆነው ሚናው ምንድን ነው? በዮሐንስ 11፥25 ላይ፣ 'ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ' በማለት ይነግረናል:: በርግጥም የእርሱ መገለጫ ባሕርዩ ይኸው ነው፤ በዮሐንስ ራእይ የመግቢያ ምዕራፎች ላይ እንደሚያሳየንም፣ ቤተ ክርስቲያን ይህንኑ ባሕርይ እርሷም ትሸከም ዘንድ፣ ከሞት የተነሣና ሕያው አምላክ አድርጋ፣ እርሱን በዚህ መልክ ማወቅ አለባት:: ተግባሯ የክርስቶስን ሕይወትና ትንሣኤ ማሳየት ነው::

ከዔድን ጀምሮ፣ እግዚአብሔር ከሰይጣን ጋር የነበረው ሙግት በዚሁ በሞትና በሕይወት ላይ ነበር (ለምሳሌ ዘፍ 3፥3፣ 4፤ ሮሜ 5፥12፣ 17፣ 21፤ 1ቆሮ 15፥22 ይመ):: የእግዚአብሔር የሆነው ሁሉ መገለጫ ባሕርዩ ሕይወት ነው፤ የሰይጣን ደግሞ ሞት ነው:: የቅድስና ጉዳይ ብቻ አይደለም፣ በዓለም ውስጥ አያሌ የሐሰት ቅድስና አለ፤ በእርሱም በቀላሉ እንታለላን፤ ሕይወት ግን አስመስሎ ሊቀርብ የሚችል ዐይነት አይደለም:: በእኔ ውስጥ ሕይወት አለን? በሌላው ላይ ሕይወትን እዳስሳለሁን? ጥያቄዎቹ እነዚህ ናቸው:: ሕይወት ከሐሳብ እጅግ የጠለቀ፤ ከስሜትና ከአስተምህሮም ይበልጥ አማናዊ ነውና:: ሕይወት ባለበት እግዚአብሔር አለ:: በሌሎች ሁሉና በክርስቶስ መካከል ትልቁ ልዩነት ሌሎቹ ሞተዋል፤ እርሱ ግን በሕይወት አለ:: ሞት ሊነካው አልቻለም:: በክርስቶስ ሞትን የገደለው እግዚአብሔርም ቤተ ክርስቲያንን ለተመሳሳይ ዐላማ ይጠቀምባታል:: ዛሬ፣ ቤተ ክርስቲያን ትንሣኤ ያገኘውን የልጁን ሕይወት ታሳይ ዘንድ፣ ሰዎችንም ወደዚያ ሕይወት ዕውቀት ታመጣ ዘንድ የሕይወት የእግዚአብሔር ሸክላ ናት::

ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን ሥራና አገልግሎት ይህ ከሆነ፣ በእርሷ ላይ የሰይጣን ጥቃት ባሕርዩ ምን እንደሚሆን ጐልቶ ማየት እንችላለን:: ሞት መሣሪያው ይሆናል:: የዚህን አስፈላጊነት ልብ በሉ:: ጥቃቱ በኀጢአት በኩል፣ ወይም በዓለም፣ ወይም በቀጥታ ጥቃት ብቻ ከመጣ፣ ይህንኑ እንዴት መከላከል እንደሚቻል ማወቅ አለብን:: ነገር ግን የኀጢአት ጉዳይ እልባት ካገኘ በኋላ እንኳ፣ ዓለምም የማትማርከን ብትሆንም እንኳ፣ ሰይጣን አሁንም ኀይል አለው:: ዕቃው በዚህም በዚያም ሌሎች ቀዳዳዎች ካሉት፣ አንድን ቀዳዳ ብቻ መድፈን ዋጋ የለውም::

ኀጢአት ሌላ ሳይሆን መንገዱ ነው፤ ሞት ግብ ነው:: ለኀጢአት መፍትሔ ማግኘት ሞትን ማሸነፍ አይደለም:: ከዚያ ቦታ ከደረሳችሁ፣ የመንገዱ መፍረስ (የመንገዱ መበላሸት) ከዚያ ቦታ እንድትርቁ አያደርጋችሁም:: የሰይጣን ኀይል





ያለው ዓለምን በመውደድ አይደለም፣ ወይም ኀጢአትን በመውደድም፣ አይደለም በአእምሮ ወይም በሰውነት ወይም በሌላ አካል ላይ በቀጥታ ጥቃትም አይደለም:: እነዚህን ነገሮች ሁሉ ልናሸንፍ እንችላለን፤ ይሁን እንጂ በሞት በኩል አሁንም ኀይል ያለው በመሆኑ አሸናፊዎች ላንሆን እንችላለን::

ለስሙ ምስጋና ይሁንና፣ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚመጣው ጥቃት ከየት እንደ ሆነ ገና ከመጀመሪያውኑ አሳይቶናል:: "ከገሃነም ደጆች" ይኸውም ከሞት እንደሚመጣ ማሰብ አለብን:: ይህ አገላለጽ የተከሠተው በዐዲስ ኪዳን ላይ ለአንድ ጊዜ ብቻ ነው፤ ይሁን እንጂ በማቴዎስ 16፥18 ላይ በትክክለኛው ቦታ ላይ ገብቶ ይገኛል:: የቤተ ክርስቲያንን መቋቋም (አሸናፊነት) በተመለከተ የሰይጣን ታላቅ ፍርሃት፣ ኀጢአት በመሥራት ላይ አይደለም፣ ወይም ዓለምን በመውደድም አይደለም፣ ወይም ማናቸውንም ቀጥታ ጥቃቱን በተመለከተም አይደለም፣ ነገር ግን በሞት ላይ ባለው ሥልጣን ረገድ ነው::

የሰይጣን ኀይል በሞት በኩል ነበርና፤ ግዛቱ ባለበትም የምትጎንጡት ሞትን ነው:: መገለጫ ባሕርያቱ በአጋንንት መያዝ፣ ወይም ኀጢአት ሳይሆን ሞት ነው:: ከዚህ የተነሣ፣ የክርስቶስ ሥራ ከቤዛነት ባነሰ ሊቆም አይችልም:: የሥራው ዋና ማዕከል በሞት በኩል የዚያ የሞት ኀይል ያለውን ሥራ መና ማስቀረት ነበር (ዕብ 2፥14):: ይህ ሐቅ በጣም ታላቅ ነው:: በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት፣ በሞት ላይ የሰይጣን ሥራ ባለጋራውን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አገኘ:: ያ ሞት ሞትን ሁሉ ያሸንፋል:: በአዳም ያለው ሞት አንድን ሰው አይደመድመውም፤ በክርስቶስ ያለው ግን እንዲያከትምለት ያደርገዋል፤ ኀያል ሞት ነው:: በክርስቶስ ሞት የሚገባቸው ሁሉ ሞተዋል፤ ይህም የሆነው የሞት ኀይል ያለው በእነርሱ ላይ ሥልጣን እስከማይኖረው ድረስ ነው፤ ሞተዋልና:: ዐመድ ከቶ እሳት የምታነዱበት ነገር አይደለም:: አንድ ቤት ዐመድ እስከሚሆን ድረስ ከተቃጠለ፣ ከንዋዩው የሚደገምበት አንዳች መንገድ የለም፤ የመጀመሪያው እሳት የራሱን ሥራ ስላከናወነ ቀጥሎ ያለው እሳት የሚሠራው ነገር የለም::

ስለዚህ በዔድን ገነት በሕይወትና በሞት መካከል ተጀምሮ የነበረው ሙግት በጌቴሴማኒ ላይ በጎልጎታ አከተመ:: በዚያ ሞት ወደመ፤ ሕይወትና ኢመዋቲነትም እውን ሆኑ:: የወደመው ሰይጣን ብቻ ሳይሆን እኛ በክርስቶስ ሞትን ስለሞትን፣ ለእኛ ለተቤዡነው ኀጢአተኞች ሞት የለም፤ እኛም የማይጠፋውን ሕይወቱን ወራሾች ሆነናል::

ይሁን እንጂ ከርከሩ በዚያ እንዳለቀለት ማሰብ የለብንም:: "የገሃነም ደጆች" ኀይልን የሚያመለክቱ ከሆነ፣ "አይችሉአትም" የሚለው ቀጣይ ዘመቻን ያመለክታል:: ዛሬም በመካሄድ ላይ ነው:: ዛሬ የሰይጣን ልዩ ዐላማ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሞትን ማስፋፋት ነው:: በዚህ አጭር ወቅት ሞት አሁንም ኀይሉ ነው:: በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ አሁን ሞትን ማምጣት ከቻለ ይረካል፤ ወይም ሞት ከእርሱ ጋር ያለና አሁንም የሚሠራ ከሆነ የቱንም ያህል በጎ ምግባር ይኑር ርካታን አግኝቶአል::

"የሥጋን ነገር ማሰብ ሞት ነው፤ የመንፈስን ነገር ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው:: ... ስለዚህ ወንድሞች ሆይ፤ ግዴታ አለብን፤ ይሁን እንጂ እንደ ሥጋ ፈቃድ እንድንኖር ለሥጋ አይደለም:: እንደ ሥጋ ፈቃድ ብትኖሩ ትሞታላችሁና፤ ከፉ የሆነውን የሥጋ ሥራ በመንፈስ ብትገድሉ ግን በሕይወት ትኖራላችሁ" (ሮሜ 8፥6፤ 12-13) (አመት):: እንደነዚህ ያሉ ቃሎች ለክርስቲያኖች የተነገሩ እንደ መሆናቸው፣ ራሳችንን በሕይወት እንድንጠብቅ ያስጠነቅቁናል:: ነገር ግን ዋጋው ሞት የሆነውን ኀጢአት ወደ ጐን እንተወውና ሕይወትን በተመለከተ ዝም ብሎ መታዘብ ማለት ሞትን ማስፋፋት መሆኑን ልብ የምንለው፥ ስንቶቻችን ነን? ይህን በማድረግ ለሥጋ ዕድል እየሰጠነው ነው::

እስቲ አንድ የተለመደ ምሳሌ እንመልከት:: የቱንም ያህል ሐቅ ይሁን፥ እንደ ሀሜትና እንደ ነቀፋ ያለ የሞት አራማጅ የለም:: እግዚአብሔር ጸጥ እንድንል ይፈልጋል፤ ይሁን እንጂ አንደበታችን መሥራት አለበት! በእርሱ ፊት ጸጥ ብለን እንድንቆይ ይፈልጋል፤ እግራችን ግን እንደ ተራመደ ነው! እንድንቆይ ሲፈልግ መሄድ፣ ወይም ጸጥ እንድንል ሲፈልግ ማማት፣ ልክ እንዳልተሸሻለ መገለጫው ሁሉ እነዚህም ነገሮች ከሥጋ ፍላጎት የመነጩ ናቸው:: የሥጋን ፍላጐት - "ገለልተኛ" እንኳ ቢሆን - ወደ እግዚአብሔር ሥራ ማምጣት፣ ከገሃነም ደጆች ጥቃትን መጋበዝ ነው፤ እግዚአብሔር ሳይል (ሳይጠይቅ) ብንናገር በቃሎቻችን ሞት እንደሚኖር ርግጠኞች ሁኑ::

ሕይወት ሊብራራ አይችልም:: ስንዳሰሰው፣ ሕይወት እንደ ሆነ እናውቃለን:: ነገር ግን እንዴት? በሐሳብ ወይም በስሜት አይደለም፤ ወይም "በስድስተኛው የስሜት ህዋስ" አይደለም:: የሚያውቁ፤ ያውቃሉ:: የማያውቁ፤ አያውቁም:: እነርሱ ራሳቸው እስካላወቁ ድረስ፤ የሚያውቁት ለማያውቁት ከቶ ሊያብራሩ አይችሉም:: ሕይወትን የሚያውቁ በሌሎች ላይ ያለውን ሕይወት ልብ ይሉታል:: በራሳቸው ላይ ሞትን የተሸከሙ ሕይወትንም ሆነ ሞትን





መገንዘብ አይችሉም:: ተፈጥሮአዊው ሰው በሙቀትና በቅዝቃዜ፣ በመልካምና በመጥፎ አስተምህሮ መካከል ያለውን ልዩነት ሊለይ ይችላል፤ በሕይወትና በሞት መካከል ግን መለየት አይችልም:: ብዙዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጉድለት በሚታይ መልኩ እስከሌለ ድረስ፣ ሁሉም መልካም ነው ብለው ያስባሉ:: ይሁን እንጂ ሕይወትም ሆነ ሞት ምን እንደ ሆነ መለየት አለመቻል ብርቱ ጥፋት ነው:: መቼ እንደምንጠቃ አናውቅም:: እግዚአብሔር ይህን መለየት ይስጠን!

ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ምድራዊ መገለጫ እና፣ የእርሱ ውድ በመሆኗ፣ ሰይጣን ዐቅም ቢኖረው ኖሮ ተመልሶ የሚታይባት መድረክ በሆነች ነበር፤ በእኛ በኩል ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሞትን ማስፋፋት ከእርሱ ጋር ተባብሮ መገኘት ይሆናል:: የሚያሳዝን ነገር ነው፤ እንዳንዶቻችን የምንፈጽመው ይህንኑ ነው! በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ የምንከራራበት "ችሎታ" ሁሉ በእጁ የገባ መሣሪያ ይሆናል:: በመስቀሉ አማካይነት ልጓም ያልተበጀለት ተፈጥሮአዊ ምጡቅነትና ብሩህ አእምሮ በቤተ ክርስቲያን ላይ ሞትን ያመጣል:: ጤነኛ የሆነው አስተምህሮአችን እንኳ፣ በተፈጥሮአዊው አእምሮ ከተያዘ፣ እንደዚሁም መንፈሳዊ "ስጦታዎቻችን" ሥጋዊ በሆነው ሰው ከተያዙና አላግባብ ከዋሉ፣ የሚያራምዱት ሞትን ብቻ ነው:: ሳምሶንን ልብ በሉ! የሕይወት ምንጩ በርግጥ የእግዚአብሔር ካልሆነ በቀር፣ ከሞት በቀር ሌላ የሚያገለግለው ነገር አይኖረውም:: በዐጭሩ፣ ሰዎች በእኔ ያለውን ክርስቶስን በመዳሰስ ፈንታ እኔን የሚዳስሱ ከሆነ ሕይወትን ሳይሆን ሞትን ይዳስሳሉ::

በዚህ ረገድ ማስመሰል ዋጋ የለውም:: እውነቱ ይፋ ይወጣል:: ሌሎች ነገሮች መስለው (በማስመሰል) ሊቀርቡ ይችላሉ፤ ሕይወት ግን ከቶ እንዲህ ሊሆን አይችልም:: የእኛ መንፈስም እንደዚሁ ነው፣ በሌሎች ላይ የምናሳድረው ስሜትም እንደዚሁ ነው:: ሞት በዚያ ካለ ሰዎች የሚያገኙት ያንኑ ሞት ነው፤ ሕይወት ካለም ሰዎች የሚያገኙት ያንኑ ሕይወት ነው::

እንደ እውነቱ ከሆነ ይህ ሕይወትን ወይም ሞትን የማሠራጨቱ ጉዳይ፣ በቤት ውስጥ፣ በቤተ ክርስቲያን፣ በፀሎት ስብሰባና በየትኛውም ቦታ አለ:: እንዳንዶች ባሉበት መስበክ ቀላል ነው፤ ሌሎች በዚያ ካሉ ግን ከባድ ነው:: ለምን? ከሰዎች ጋር ግንኙነት የለውም:: ሕይወትን ከመስጠት ወይም ሕይወትን በማድረቅ ላይ የተመሠረተ ነው:: አካል የክርስቶስ መገለጫ እስከ ሆነች ድረስ ለአካል አስተዋፅኦ ማድረግ የምንችለው ክርስቶስን በማገልገል ብቻ

ነው፤ ክርስቶስም ሕይወት ነው። ሕይወት ያላቸው በጉባኤዎች (በስብሰባዎች) ክርስቶስን ያገለግላሉ። ሌሎች ግን "አሜናቸው" እንኳ ሙት ነው! የጌታን እራት በመካፈል ላይና በጸሎት ያለው መንፈሳዊ ኀይል የሚመሠረተው፣ በዚያ የተሰበሰቡት አሉታዊ ብቻ ወይም ሕይወትን የሚያመጡ በመሆናቸው ላይ ነው። ከዚህ ላይ በዚህ ዘመን በዔድንና በጐልጐታ የነበረው ክርክር ይስተጋባልና። ትንሣኤ ያገኘ ሕይወት አለን? በየትኛውም ቦታ ጥያቄው ይኸው ነው። እያንዳንዱ አባል በእግዚአብሔር ፊት የተነሣውን የክርስቶስን አገልግሎት ወደ ቤቱ የማምጣት ኀላፊነት አለበት።

## ለአካሉ ሕይወትን አገልግሎት ላይ ማዋል

ራሳችን በተደጋጋሚ ወደ ኋላ ተመልሰን እንድናስተውለው የተደረገው ሐቅ የክርስቶስ አካል አንድ የመሆኑ ጉዳይ ነው። ያን ሐቅ ልናመልጠው አንችልም፤ ጳውሎስ ይህንን እንዲህ በማለት በድጋሚ ወደ መፍትሔ ያመጣዋል፤ "አንድ ብልት ቢሠቃይ ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ይሠቃያሉ፤ አንድ ብልትም ቢከበር ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ደስ ይላቸዋል" (1ቆሮ 12፥26)።

ከዚህ ላይ የተነገረውን በጥንቃቄ ልብ ማለት አስፈላጊ ነው። አንድ ብልት የሚሠቃይ ከሆነ፣ የተነገረን ሌሎቹ ብልቶች መሠቃየት አለባቸው የሚል አይደለም፤ ከእርሱ ጋር ዐብረው ይሠቃያሉ ተብሎ እንጂ። አንድ ብልት ቢከብር ሌሎቹም መከበር አለባቸው አልተባልንም፤ ከብሩን ዐብረው እየተጋሩት ነው። የአካሉ አንድነት ሐቅ ካልሆነ፣ እንግዲያውስ እነዚህ ከውብ ስሜቶች የዘለሉ አይደሉም። ነገር ግን የአካል አንድነት መለኮታዊ ሐቅ በመሆኑ፣ ሁሉም (ብልቶች ሁሉ) ከሚሠቃየው ብልት ጋር መሠቃየታቸው ሐቅ ነው። "ለመሠቃየት እየሞከሩ ነው፤" ወይም "መሠቃየት አለባቸው" ሳይሆን እየተሠቃዩ ነው። ቍጥር 26 መነበብ ያለበት፣ ክርስቲያኖች እንዴት መፈጸም እንዳለባቸው የሚያሳይ መመሪያ ወይም ምክር ተደርጎ ሳይሆን፣ በመከናወን ላይ ያለ ሐሳብ ተደርጎ ነው። አካል ለዘላለሙ አንድ ስለሆነ፣ አንድ ብልት ሲሠቃይ መላው ይሠቃያል፤ አንድ ብልት ከፍ ከፍ ሲደረግም መላው ከፍ ከፍ ይደረጋል።

አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ልጆች ይህን እንደ ተመክሮ ጉዳይ ሆኖ ይገነዘቡት ዘንድ ይደረጋሉ። በደቡብ ቻይና ውስጥ የምትኖር አንዲት ወድ ወዳጄ የሆነች ሴት አንድ ጸረ ባዕዳን የሆነ እንቅስቃሴ በሌላው የአገራችን ግዛት ውስጥ በተነሣ ጊዜ ብርቱ መንፈሳዊ ሸክም ተሰምቷት እንደ ነበር





ነገረችን፤ የዚህ አሳዛኝ ሁኔታ ዜና ግን እርሷ ለነበረችበት ወረዳ ገና እልደረሰም ነበር፤ እንደ ገናም በብርታንያ በዌልስ መነቃቃት ተከሥቶ ሳለ፣ ስለ ከሥተቱ የተዛባ ነገር ብትሰማም እንኳ፣ የሕይወት ሽታና በመንፈስ ከፍ ከፍ የማለት ስሜት ተሰምቷት ነበር፤ በምዕራቡ ደግሞ የጐበኘሁት ሌላ ወዳጄ፣ በቻይና በነበረን ሥራ ላይ ስለ ደረሰብን ብርቱ መከራ ስነግረው፣ "ርግጥ ነው ደብዳቤያችሁ ለእኛ ከመድረሱ በፊት አጸፋዊ መልስ ከዚህ ተሰምቶናል በማለት አግራሞት ፈጠረብኝ።

ነገር ግን ስለ እነዚህ ዐይነት ነገሮች ይነገረንም አይነገረንም ዐይነተኛው ጉዳይ ይህ አይደለም። ሐቁ በጌታ በኩል እንቅስቃሴ ባለ ቍጥር፣ በአካሉ በኩል አጸፋዊ መልስ አለ፣ ሁሉም አባላት ደግሞ ለዚያ አጸፋዊ ምላሽ ተገዢች ናቸው። ይህንኑ ልብ የማለታችን ጉዳይ በተነግሮ (በመረጃ) ሳይሆን በሕይወት መንፈስ አማካይነት ስለ ጌታ ያለን ዕውቀት ነው።

አንድ የአካል ብልት ዘግናኝ ኀጢአት ቢሠራ፣ ወይም በታላቅ ሥቃይ ውስጥ የሚገኝ ቢሆን፣ ጫናው መንፈሳዊ አባላት ለሆኑት በርግጥ ይሰማቸዋል። በአንጻሩ ደግሞ ዐዲስ የሕይወት ማዕበል ወደ አንዱ ብልት (አካል) ቢመጣ፣ በአካሉ ውስጥ በብርቱ ተጠብቀው የሚገኙት ሌሎች ብልቶች (አባላት) ምጥቀትን በርግጥ ያውቃሉ። እንዳንድ ጊዜ ከእግዚአብሔር መገለጥን ከመቀበላችሁ በፊት በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ልታልፉ ትችላላችሁ፤ በሌላ ጊዜ ደግሞ እናንተ ፍሲጋ ሳታካሂዱ ብርሃን ዘልቆ ይታያል። በመጀመሪያው ሁኔታ፣ ለሌሎች መገልገያ በሚሆነው በዐዲስ የሕይወት ማዕበል እያለፋችሁ እንደ ሆነ ሐሳብ እስነዝራለሁ፤ በሁለተኛው ኢጋጣሚም የሌሎችን መከራ መኸር (ውጤት) እየሰበሰባችሁ ሲሆን፣ በዚሁም በኩል ለአጠቃላይ ለአካሉ የሚሆን ጭማሬ ወዲያውኑ መጥቶአል።

ይሁን እንጂ የዚህ ሌላ ገጽታ አለ። ለግል ዐላማ ጭማሬን የምትፈልግ ዐይነት ከሆንህ፣ ከአጠቃላዩ አካል ወደ አንተ የሚወርደውን የሕይወት ፍሰት እያስቀረህ ነው፤ የምትሻውን ጭማሬ የምታገኝ ብትሆን፣ ለአንተ የማይጠቅም መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ጉዳቱ ለራስህና ለተቀረው አካል ይሆናል። ለእንደዚህ ዐይነቱ ሁኔታ ተወዳዳሪ የሚሆነው በሚታየው አካል ላይ የተከሠተው ካንሰር ብለን የምንጠራው በሽታ ነው። ካንሰር የሚመጣው አንድ ህዋስ ከልክ በላይ ሲያድግ ነው። አንድ ህዋስ ያለንዳች ገደብ ወይም ቁጥጥር ራሱን ያባዛል፤ እንዲህ በማድረጉም የሚመጣውን ምግብ ወደ ሌላ አካል በማስተላለፍ ፈንታ ሁሉንም ይጨርሳል። ተገንጣይ (አሐድ) ሆኖ በመሥራት፣ የተወላገደውን

ባሕርይ በአካሉ ላይ በመጫን፣ በሰውነት የሕዋሳት ቡድን ላይ ጫና ይፈጥራል:: በአንጻሩ ደግሞ የተፈጥሮ ድንገተኛ አሠራር ሌሎችን በሽታዎች የማስተካከል ሚና ቢኖረውም፣ የካንሰር ማስተካከያ ግን አይደለም፤ አካል በሕመም ወደ ተያዘው ክፍል ሕይወትን በሰደደ ቁጥር፣ ካንሰር ለራሱ ጥቅም ሲል የባሰውን ያጋብሳል:: ፍሰቱ በመገደቡ፣ ወደ ውስጥ የሚፈሰው ሁሉ ችግሩን ያባብሰዋል:: አቤት፣ ይህ በመንፈሳዊ ነገሮች ረገድ የቱን ያህል እውነት ነው! በዘወትራዊው (በተለመደው) አካሄድ፣ ዐዲስ የሕይወት ፍሰት ወደ ማንኛውም የአካል ብልት (አባል) መምጣት ወዲያውኑ ለሁሉም ጭማሬን ያስገኛል፤ ሆኖም ለራሱ ጥቅምን በመሻት ገለልተኛ ቢሆን (ቢለይ)፣ ባደገ ቍጥር ለጠቅላላው ለክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ታላቅ ሥጋት ይሆናል::

አቤት፣ ስለዚህ የክርስቶስ መስቀል የቱን ያህል ውድ ነው! ይኸው መስቀል በጠቅላላው አካል ላይ የሕይወትን እንቅስቃሴ ከፍ ለማድረግ እያንዳንዱ አባል ሊያገኘው በሚችለው ስፍራ ላይ ይገኛል፤ ይህም አባሉ በውስጡ ባለው ተፈጥሮአዊ ሕይወት ላይ መስቀሉ ሥር ነቀል በሆነ መልኩ ይሠራ ዘንድ እስከ ፈቀደ ድረስ ነው:: ስለ አካሉ ስንል እንጸልይ:- "ጌታ ሆይ፤ ራስ ወዳድ በሆነ መልኩ ግለሰባዊ የሆነብኝን፣ አካልንም የሚያዳክመውን፣ ስለ ራስህ ሙላትም ስትል በውስጤ ያለውን ሰባብረው፤ ከዚህ ቀደም ከቶ ያልደረስሁበትን የሕይወት ግዛት እንድደርስበትም ዘንድ አግዛኝ!"

በሁለተኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 4 ላይ በአንድ ስፍራ ላይ የክርስቶስ ሞት እንዴት እየሠራ እንደሆነ ቀደም ብለን አይተናል (በአካል ቍጥር 10፤ በእኛ ቍጥር 12):: ይህም ትንሣኤው በሁለት ስፍራዎች ይገለጥ ዘንድ እንዴት እንዳስቻለው አይተናል በሥጋችን፣ ቍጥር 10፤ በእናንተ፣ ቍጥር 12):: ከዚህ ላይ የሕይወት ፍሬያማነትና የአገልግሎት ፍሬያማነት አለን፤ ርግጥ ነው ብቸኛው ልዩነት የመገለጫው ቦታ እንጂ በመጨረሻ አንድ ናቸው:: በመጀመሪያው ደረጃ፣ ሕይወት የተገለጠው ሞት በሚሠራበት ስፍራ ነው፤ በሁለተኛው ደረጃ፣ ባንድ በሌላ ስፍራ ነው:: መገለጫው በእኔ ሲሆን ሕይወት ብዬ እጠራዋለሁ፤ በሌሎች ላይ ሲሆን ግን አገልግሎት እለዋለሁ::

መስቀል በሌለበት ሕይወት የለም፤ የሕይወት አገልግሎትም የለም:: የመሠቃየት ዐላማ ሙሉና የተትረፈረፈ አገልግሎት እንዲኖር ነው:: ትወራ የዚህ ትክ ሊሆን አይችልም:: የአገልግሎት ድኽነት የሚመጣው የተመቾ መንገድን ከመምረጥ ነው:: አመቾ ጊዜ ያላቸው አብዛኛውን ጊዜ የሚሰጡት ነገር የሚኖራቸው በጥቂቱ ነው:: የሰዎችን ችግር አይረዱም:: ርግጥ ነው





ችግርን በመጋበዝ ወይም ለቁጠባ ሲባል አካላታችንን መጐዳት አለብን ማለቴ አይደለም:: መንፈስ ቅዱስ ራሱ በአካል፣ በልብ፣ ወይም በመንፈስ ልንገጣጠም በምንችልበት መንገድ በመምራት፣ "የኢየሱስን ሞት" በሚመጥን መልኩ ከአገልግሎታችን ብቃት እስከንደርስ ድረስ ስለተመከሮአችን ኀላፊነት ይወስዳል:: የእኛ ድርሻ መከተል ብቻ ነው::

ሕይወትን ለአካል ለማገልገል እንዴት ጥቅም ላይ ማዋል እንደምትችሉ ትጠይቁኛላችሁ:: ብዙ ለመሥራት ሆን ብሎ በመኳኳት አይደለም፤ ወይም ወደ ጡረታ ለመጣደፍና ምንም ነገር ባለመሥራት አይደለም፤ ይልቁን ከጌታ ጋር በተለመደው አካሄድ ስትራመዱ መስቀሉ እንዲሠራ በመፍቀድ ነው:: በቃልና በሥራ ብቻ የሚያገለግሉት በማናቸውም ወቅት ወደ ሥራ ፈትነት ወይም ወደ ዝምታ የሚወርዱ ከሆነ አገልግሎት እንደሌላቸው ሆነው ያገኙታል:: ይሁን እንጂ የአገልግሎታችሁ መጠን የሚለካው በከንዋኔያችሁ ልክ አይደለም፤ ስለዚህ "ሞቱ በእኛ ሕይወቱም በእናንተ ይሠራል" የሚለው የአካል ቋሚ መርሕ ነውና:: እንግዲህ በዚህ ዐይነት መንገድ በአካል ላይ ሙላትን ለማምጣት የተለየ ጥረት ማድረግ የለባችሁም፤ ወይም እግዚአብሔር በሚወስዳችሁ የመስቀሉ መንገድ በዚያው መንገድ ላይ ወዲያውኑ ሙላትን ያመጣል::

ወይም ብዙ መናገር አያስፈልጋችሁም፤ ያው ለሌሎች ዋና ጉዳይ ይሆን ዘንድ ስለ ሞት ተመከሮአችሁ መመስከር አስፈላጊ አይደለምና:: ለመሞት ፈቃደኛ እስከ ሆናችሁ ድረስ፣ ሌሎች ሕይወትን ያውቃሉ፤ እውነታ ራሱን ይገልጻል፤ በሰው ተግባቦት ላይ የተደገፈ አይደለም:: "ትንቢትን አንንቅም፤" ይሁን እንጂ በአካል ውስጥ ያለው አገልግሎት ስበከት ወይም ምስክርነት ብቻ እንዳልሆነ እኛ ራሳችን እናረጋግጣለን:: ከጌታ ጋር ሆነን በምስጢር የምናልፍበት ሁኔታ፣ የራሱ አባላት የሆኑትን ለማገልገል በቂ ነው:: ለጌታ ስንል የምንሠቃይ ከሆነ፣ የሥቃያችን ታሪክ እንዲታወቅ ሳናደርግ ያ ሥቃይ ለሌሎች ሙላትን ያመጣል:: ስለ ጉዳዩ መናገር ከሚፈለገው በላይ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በአንዳንድ ሁኔታ አስጸያፊም ነው::

አንድን ወንድም ይቅር ብትሉ፣ የይቅርታችሁ እውነታ ያለንዳች ገለጻ (ይህን በተመለከተ ጌታ ይቅርታው ይፋ እንዲሆን የሚፈልግባችሁ ሊሆን ቢችልም) ለአካል ሕይወትን ይሰጣል:: አንድን ወንድም ብትወዱ፣ ያን ወንድም የቱን ያህል እንደምትወዱት ከቶ ባትናገሩትም፣ ያ ፍቅር አካልን ያንጻል:: በእንግሊዝ አገር ይካሄድ በነበረ ትልቅ ጉባኤ ላይ እኔ ባለወቅሁበት

ወስዶባቸዋልና፡፡ በአስተምህሮ ረገድ 'ወግ አጥባቂ' ወይም 'አርቶዶክስ' ከሆኑ፣ ለዚህም አእምሮአዊ ቅበላን ከሰጡ፣ ለዚያም አእምሮአዊ ቅበላን ካልሰጡ ሁሉም በጎ ነገር እንደ ሆነ ይሰማቸዋል፡፡ በዚህ አመክንዮ የተነሣ፣ ጥንተ ነገራውያን (fundamentalists) ከዘመናውያን ይልቅ ከፍ ባለ ደረጃ ላይ እንገኛለን ብለው ያስባሉ፤ ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር ዐይን የሚለኩት በሌላ ሳይሆን እውነተኛን የክርስቶስ የውስጥ መገለጥ እስከያዙ ድረስ ነው፡፡ ፍጹም ትክክል ሊሆኑ ይችላሉ፤ ነገር ግን ሕይወትን ካልያዙ ልዐላዊ ዐይነተኛ ነገር የላቸውም፡፡

ዛሬ ቤተ ክርስቲያን የቃሉ ፊደል አላት፣ ቃሉን ስለ ያዘችው እግዚአብሔርን እናመሰግናለን! መጽሐፍ ቅዱሶቻችንና ትርጕሞቻችን አሉን፣ ስለ እነዚህ ሁሉ እርሱን እናመሰግናለን፡፡ ነገር ግን ፊደል - መሠረታዊ ፊደል እንኳ ይገድላል፤ ሕይወት የሚሰጠው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው (2ቆሮ 3፥6)፡፡ ሕይወትን ወደ ሌሎች የምናመጣ ከሆነ፣ ከምእት ዓመታት በፊት በነበረው በእግዚአብሔር ሐሳብ መሠረት ቃሉን መስበክ ብቻ የለብንም፤ መንፈስ ቅዱስ ያንን ቃል ዛሬ ላሉት ሰዎች እንዴት ተግባራዊ እንደሚያደርገውም ማወቅ አለብን፡፡

በዐዲስ ኪዳን ውስጥ 'ነቢይ' ሲባል፣ እንደ ኤልያስ ወይም እንደ መጥምቁ ዮሐንስ፣ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለውን የወቅቱን ዐላማ ማወጅ ነው፡፡ የእርሱ (የነቢዩ) ስብከት ወሳኝ ስብከት ነው፤ ምክንያቱም በቃሉ በኩል የእግዚአብሔርን ሐሳብ ለራሱ ዘመን ወደ ብርሃን ያመጣልና፡፡ ሦስት ነገሮች ያንድን ነቢይ ማንነት ይገልጻሉ፦ በእግዚአብሔር ፊት ያለ ታሪክ፣ ውስጣዊ ሸክም፣ ሸክሙን የሚገልጹና የሚተረጕሙ ከመለኮት የተሰጡ ቃሎች ናቸው፤ ይኸውም ቃሉን ካገለገለ በኋላ ሸክሙ ተነሥቶለት ወደ ቤት ይመለሳል፡፡

ዛሬ ለእንዲህ ዐይነቱ አገልግሎት የቅዱሳት መጻሕፍት ጥናት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ርግጥ ነው የተደላደለ አእምሮ ያለው ማንኛውም ሰው በአንድ ዓመት ውስጥ ከመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ሊማር ይችላል፤ ሆኖም እርሱን በብርቱ የምንከተለው ከሆነ፣ እግዚአብሔር እኛ ራሳችን ከምንናገረው ጋር አቻዎች መሆናችንን ለማረጋገጥ ርምጃ ሳይወስድ እንዲሁ እንዲያልፍ አያደርግም፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍትን መገንዘብ በሁለት መንገድ ይመጣልና፣ እንደኛው ከጥናት ብቻ ሲሆን፣ ሌላው ግን ጌታን ራሱን ከማወቅና ከመከተል ነው፤ በሁለቱ መካከል ብዙ ልዩነት አለ፡፡ አስተምህሮን በማወቅ ረገድ ብቻ የነገረ-መለኮት ምሩቅ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ያዘዘውን ሁሉ ፍጹም በሆነ መልኩ ቀማምሮ ያቀርብ





ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ ያ ቃል ከእግዚአብሔር ለእርሱ በቀጥታ እስካልመጣለት ድረስና እርሱም ምላሽ እስካልሰጠ ድረስ፣ ቃሉን እያወጀ ያለ ሰባኪ አይደለም፡፡ ሌላው ሰው፣ ስለ ነገረ-መለኮት ሳይንሳዊ የሆነ ዕውቀት ሳይኖረው፣ ስለ እግዚአብሔር ጥልቅ የሆነ ዕውቀት በማግኘት ሊያገለግል ይችላል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በቃሉ ይናገረዋል፤ እግዚአብሔር በተናገረ ቊጥር፣ እንዲህ በማድረጉ ያላንዳች ጥያቄ ይታዘዛል፡፡

አንድ ወንድም ቢነሣና ቢናገር፣ አጽንዖት የሚያደርገው በአስተምህሮ ላይ ወይም በሕይወት መሆኑን ወዲያውኑ ታውቃላችሁ፡፡ በመጀመሪያው (በአስተምህሮ) ላይ ከሆነ ራሱን አደጋ ላይ ከቶ አይጥልም፡፡ ስሕተት ላይ ፈጽሞ ላለመውደቅና አጉል ግንዛቤ እንዳይደርስበት በአስተምህሮአዊው ሥርዐት ውስጥ ይጓዛል፡፡ እያሌ አመክንዮቹን አሳማኝ በሆነ ቅደም ተከተል ያቀርባል፤ ከብዙ ሐተታ በኋላም በአመክንዮአዊው ሂደት መሠረት ከማይለወጠው ድምዳሜው ላይ ይደርሳል፡፡ ነገር ግን በሕይወት ላይ አጽንዖት የሚያደርገው፣ በቴክኒካዊ እርማት ወይም የያዘውን ርእሰ-ጕዳይ አድቅቆ በማቅረቡ ላይ ብዙ አይጨነቅም፡፡ አቀራረቡ በጣም የተለየ ይሆናል፤ አስተምህሮ ብቻውን ዳር እንደማያደርስ የሚያመለክቱትን ሁኔታዎች እርሱ ራሱ ዐውቆአልና፡፡ ስለዚህ፣ አንድ ርእስ ጕዳዩን ብቻ ይኸውም ክርስቶስን ለአድማጮቹ የሚያቀርብ ከሆነ፣ ለዚሁ ጕዳይ አመክንዮአዊ የሆነና ጥያቄ የሚያስነሣ ነገር ባለማቅረቡ አይጨነቅም፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ እንደዚያ አይደለምና፡፡ እግዚአብሔር በቃሉ ላይ ስለ ማናቸውም አስተምህሮ፣ ሥርዐትን በምንገነዘበው መልኩ፣ ሙሉ በሙሉ የሆነ ገጽታ ከቶ አልሰጠንም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ድምዳሜ ላይ የሚደርሰው በአመክንዮአዊ ስልት አይደለም፤ በትክክል ግንዛቤ ሳይጨበጥባቸው ሊታለፉ የሚችሉ እያሌ ምንባቦችም በውስጡ አሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ፣ ያን ምንባብ እኛ ብንጽፈው ኖሮ ነገሮችን የላቀ ግልጽ አድርገን እናስቀምጥ ነበር ብለን ለማሰብ እንደፍር ይሆናል ብዬ እሠጋለሁ! ታላላቅ መንፈሳዊ ሐቆች፣ የእግዚአብሔር ኀይል ዘላለማዊ እውነቶች፣ በቃሉ ላይ ግማሽ ደብዛዛ ይመስላሉና፤ ይኸውም ተፈጥሮአዊው ሰው በቀላሉ ለይቶ ሊያገኛቸው አይችልም፡፡ ይሁን እንጂ፣ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት፣ ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች የተደበቁት ነገሮች ለሕፃናት ተገልጠው ነበር፡፡ የራሱ መንገድ ስላለው ምስጋና ለእግዚአብሔር ይሁን! ድነት፣ ጽድቅ በእምነት፣ ቅድስና፣ ሕይወት - እነዚህን የምናውቃቸው የአስተምህሮ ዋና ሐሳብ አድርገን ነው? ወይስ እውን የሆኑ ነገሮች አድርገን?

የእግዚአብሔር ሐሳብ በአእምሮአችን ብቻ እንድንይዛቸው ብቻ ሳይሆን በሕይወት ውስጥ ተመክሮ እንድናደርጋቸው ነው::

ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ዕውቀት ማግኘት በመጠኑም እንኳ ጌታን ለማወቅ አያዘጋጅም:: እርሱን ማወቅ አለብን፣ መጽሐፍ ቅዱስ የርሱ ቃል እንደሆነ ማወቅ አለብን:: ሕዝቡን በተመለከተ የአሁን ሐሳቡን መግለጫ ማወቅ አለብን:: እንዲህ ብላችሁ ትጠይቁኛላችሁ የእግዚአብሔርን ሐሳብ ማወቅ እንችላለን? አዎን በርግጥ ታውቃላችሁ፤ እግዚአብሔር ራሱን ከሕዝቡ አላራቀምና:: ዛሬ ቤተ ክርስቲያን በሚያሳዝን ሁኔታ ተሸንፋ እያለች እንኳ፣ ምንጊዜም እንደሚያደርገው በቅዱሳት መጻሕፍት ይናገራል:: በትውልዳቸው መካከል የእርሱ አፈጉባኤ እንዲሆኑ፣ በእርሱ ፊት ታሪክ ያላቸውን ዛሬም ይመርጣል:: ሰዎች በአብዛኛው ስለ መለኮታዊ ነገሮች ግድ ባልተሰኙበት ዘመን፣ የቤተ ክርስቲያን ብርቱ ፍላጎት እንዲህ ያለ ዕውቀት ያላቸውን ሰዎች ነው::

እግዚአብሔር ከቅዱሳኑ ዘንድ እውነተኛ አገልግሎትን ይሻል:: መጥፎ ጊዜያት ያሉንም ከዚህ የተነሣ ነው! ባልታሰበ መንገድ ቢመራን ጥያቄ ማቅረብ የለብንም፤ ይህን ዘወትር ያደርጋልና፤ ይህን የሚያደርገውም ጉልሕ የሆነ ግብ ይዞ መሆኑን ርግጠኞች ልንሆን ይገባል:: ክርስቶስን በግል በማወቅ አካልን ማገልገል፣ እያንዳንዱን አባል ወደ ዐዲስ መንፈሳዊ ስፍራ ከፍ ያደርገዋልና:: ምናልባት ለጌታ ታላቁ አገልግሎታችን ያልታሰበውን በእኛ ላይ እንዲያደርግ፣ በመላው የክርስቶስ አካልም ላይ ዐዲስ የሕይወት መታደስ እንዲደርስ ለእርሱ መንገድ መጥረግ ሳይሆን አይቀርም::

ክርስቶስ በዐዲስ እይታ ይታይ ዘንድ አስተዋፅኦ እንድናደርግ በደስታ ራሳችንን በእጁ ሥር ማድረግ የለብንምን? 'ጌታ ሆይ፤ አካል ከዚህ ቀደም ያልተቀበለውን ሕይወት እንዲቀበልና ሕዝብህም እንዲታደስ፣ ልብህም እንዲረካ ከአንተ የሆነውን ሕይወት እባክህ ልቀበል!'





# ምዕራፍ ዘጠኝ

## በስሙ መሰብሰብ

ቀደም ባሉት ምዕራፎች ላይ በቤተ ክርስቲያን አንድነት ላይ ብርቱ አጽንዖት አድርገናል:: ምንጊዜም አንድና ያልተከፋፈለች ብቻ ሆና አይተናታል:: እንግዲህ ራሳችንን ጥያቄ መጠየቅ አለብን፦ ስለ እርሷ ያለው ይህ እይታ ብቁ የሚሆንበት መንገድ አለን? ቅዱስ መጽሐፍ ስለ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን ስለ አብያተ ክርስቲያናትስ አይናገርምን? የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት የሆነው የትና ከምን ላይ ነው?

ይህንኑ በጥንቃቄ ብንመለከት የመለያየት ምክንያት (ይህን ቃል መጠቀም ብንችል) አንድ ብቻ ነው - ይህም አጥቢያነት ብቻ ሆኖ እናገኘዋለን:: ዐዲስ ኪዳን መመሪያችን መሆን ካለበት፣ ልዩነት የተደረገበት *ብቸኛ* ምክንያት መልከዐ ምድራዊ ነው:: በታሪክ ወይም በአስተምህሮ፣ ወይም በሚሲዮናዊ ትስስር፣ ወይም በግላዊ ታማኝነት፣ ወይም በልዩ ልዩ መልእክት ወይም በአገልግሎት እንኳ ክርስቲያኖች አብያተ ክርስቲያናት ተብለው የሚመደቡበት መሠረት (ዕድል) በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ አይገኝም:: በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ ለአብያተ ክርስቲያናት የተሰጡት ስሞች የማኅበረ ሰባዊ ሕይወት አካባቢ ማእከላት ለሆኑት ለከተሞች ነው:: "በቆሮንቶስ ላለች የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን"፣ "ለተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን፣" "በእስያ ላሉ ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት" (እያንዳንዳቸው በነጠላ (ባለበት) ከተማ ስም የተጠሩ ናቸው) ወዘተ፣ የሚለውን እናነባለን:: በምድር ዙሪያ ተሠራጭታ የምትገኘው የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን የተሰየመችው በእንዲህ ዐይነቱ ስያሜ ነው፤ ቅዱስ መጽሐፍ ከዚህ ስያሜ በቀር ሌላውን አያውቅም::

ነገር ግን ይህ ወደ ሌላ ነገር ያመጣናል፣ ይህም እንዲህ ነው፤ "ቤተ ክርስቲያን" የሚለው ያው መጠሪያ ለመላለማዊው እንደሚውለው ሁሉ ለአጥቢያውም ይውላል (ርግጥ ነው በግሪክኛ ቋንቋ በዋና ከተማና በትንሽ ከተማ ስያሜ መካከል ልዩነት የለም):: "አካል ስለ ሆነች ቤተ ክርስቲያን" እናነባለን፤ እንዲሁም "በቆሮንቶስ ስላለችው የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንም" እናነባለን፤ ደግሞም "በቤት ውስጥ ስላለች ቤተ ክርስቲያን" እናነባለን (ኤፌ 1፥23፤ ቆሮ 1፥3፤ ፊል 2):: ርግጥ ነው ይህ ማለት በአጥቢያ የምትገኝ ቤተ ክርስቲያን አካሉ የሆነች ቤተ ክርስቲያን ናት (ይህ በዚያ ስያሜ ያለው ጥልቅ

የተነሣ፣ ከነዚህ ከመለኮታዊ ስጦታዎች ውስጥ ሦስተኛ የሆነውን ሙሉ በሙሉ ማስወገድ ዝንባሌ አለን:: ይሁን እንጂ ማንኛውም ስሕተት የሚመነጨው እውነትን ከማጣመም የተነሣ ነው:: ከዚህ ላይ ያለው እውነት አካል አንድ መሆኑ ነው፤ የአካል ኅብረትም በመንፈሳዊ ዐብርሆት ውስጥ ዐይነተኛ ጉዳይ ነው:: የእግዚአብሔርን ሐሳብ ማወቅ አለብኝ፤ ይህም ለእኔ በሆነው በእግዚአብሔር ቃል ብቻ አይደለም፣ ወይም በእኔ ውስጥ ባለው በእግዚአብሔር መንፈስ ብቻም አይደለም፣ ግን ከእነዚህ ከሁለቱ ጋር በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል በቤቱ ውስጥ የድርሻዬን ቦታ በመያዝ መሆን አለበት::

የግል ጸሎትና የቤተ ክርስቲያን ጸሎት የሚባል ነገር እንዳለ ሁላችንም እንስማማለን:: ነገር ግን እኩል በሆነ መልኩ ለግል የተሰጠ ብርሃንና ለቤተ ክርስቲያንም የተሰጠ ብርሃን አለ:: የችግራችን ምንነት ለማንም ሳይታወቅ፣ ብዙ ጊዜ በቤት ውስጥ እያለን በቃሉ ውስጥ ፈልገን ማግኘት የማንችለውን ብርሃን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንቀበላለን የሚለው ነገር እውነት አይደለም? ይህ ለምን እንዲህ ሆነ? ርግጥ ነው ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤት በመሆኗ የመለኮታዊ ብርሃን መገለጫ ቦታ ናት:: በውጭ የተፈጥሮ ብርሃን ሊኖረን ይችላል፤ ነገር ግን ከራሱ ከእግዚአብሔር ሽኪናህ (ህልዎት) በቀር፣ ተፈጥሮአዊም ይሁን ኢተፈጥሮአዊ፣ በማደሪያው ውስጥ የለም::

ይህ የኅብረት መርሕ የጳውሎስ ሕይወትና አገልግሎት መሠረቶች ከሆኑት አንዱ ነበር:: ከሌሎች ጋር ሆኖ ጌታን ሲጠባበቅ ሳለ መንፈስ ቅዱስ፣ "በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ" የሚለውን በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 13 ላይ እናያለን:: ቀደም ሲል የመንፈስ ቅዱስ ቅባት ለእያንዳንዱ አማኝ ለግል ምሪት ይሰጣል ብለናል፤ ይህንኑ ሐሳብ ተከትሎም፣ ቢያንስ ቢያንስ ለሁለት ጊዜያት ሳውል ወደ አሕዝብ እንዲሄድ የግል ጥሪ ተቀብሎ እንደ ነበር እናውቃለን (ሐሥ22፥21፤ 26፥16-18):: ነገር ግን አሁን የዚያ ምሪት ጊዜና መንገድ በአንድ ላይ እያሉ ለሌሎችም ተገልጦአል:: ሉቃስ "አሰናበቱአቸው" ይላል፤ ይሁን እንጂ በመንፈስ ቅዱስ ተልከው በማለትም ይገልጻል (13፥3፡4):: ከዚህ ላይ ቤተ ክርስቲያንና መንፈስ ቅዱስ በአንድ ላይ ሲሠሩ እናያለን፣ የአንዱ መንፈስ መሪነት ባንዱ አካል ተገልጾ እናገኛለን::

እንደ ገናም፣ በምዕራፍ 15 መጨረሻ ላይ ጳውሎስና ሲላስ ወደ ሶርያና ኪልቅያ በወጡ ጊዜ "ወንድሞችም ለእግዚአብሔር ጸጋ ዐደራ ወደ ተሰጡት" የሚለውን እናገኛለን:: ሳይነገር ዝም ተብሎ ከታለፈ ነገር ድምዳሜ ላይ





መድረስ ከቶ የሚያዋጣ ባይሆንም፣ ይህ የቤተ ክርስቲያን ዐደራ ያልታከለበት የበርናባስ ወደ ቆጵሮስ ጉዞ በግላዊ ስሜት የተካሄደ እንቅስቃሴ ሲመስል በቅዱስ መጽሐፍ ሰነድ ውስጥ እንዳይከተት አድርጎታል (ቊ 36-41)::

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ጳውሎስ በጢሮአዳ እያለ፤ "ወደ መቄዶንያ ተሻገርና እርዳን" የሚል ራእይ አየ (ሐሥ 16፥9):: ሉቃስ ይህን ከገለጸ በኋላ፣ ራእዩንም ካየ በኋላ "ወዲያው ወደ መቄዶንያ ልንወጣ ፈለግን፤ ወንጌል እንሰብክላቸው ዘንድ እግዚአብሔር እንደ ጠራን መስሎናልና" ይላል (16፥9፤ 10):: ጌታ ብዙ ጊዜ ለግለሰብ ራእይን ይሰጣል፤ ነገር ግን እንቅስቃሴው በግለሰቡ ላይ ብቻ የተመሠረተ አይደለም:: እግዚአብሔርን በጋራ በመሻት ላይ የተመሠረተ ነው:: በዚህ ምንባብም ላይ መሪነቱን የፈጸመው መንፈስ ቅዱስ ነው (ቊ 6-5):: ከአካል ጋር ስንንቀሳቀስ የምንታየው ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ስለምንቀሳቀስ ነው:: የራእዩ እውነተኛ መፈተኛ የእውነት መንፈስ ስለ ጉዳዩ መመስከሩ ላይ ነው::

## 'እንዲህ ያለውን ሰው አቅኑት'

በማቴዎስ ምዕራፍ 18 ላይ ጌታ በአንድ ወንድም መገሥጼ የቱን ያህል እንደሚያስፈልገኝ ይነግረኛል፤ እርሱ በመጣ ጊዜ፣ እርሱ ያለኝን ልብ ባልል፣ ስሕተቴን ወደማይበት ደረጃ አደርስ ዘንድ የቤተ ክርስቲያን ምስክርነት ከሚያስፈልግበት ደረጃ ሊደርስ እንደምችልም ይነግረኛል:: (ወይም ሁኔታው ሊለዋወጥ ይችላል፤ ወንድሜ በዳዩ ሊሆን ይችላል::) ሐሳቡ ወዲያውኑ ራሱን ግልጽ ያደርጋል፦ አንድ ኀጢአተኛ ሌላውን ለመውቀስ መነሣሣቱ የቱንም ያህል አግባብ የሌለው ነው! በእንደዚህ ባለው የእርምት አገልግሎት ውስጥ አንዳች ወይም ብዙ ድርሻ የሚኖረን ከሆነ፣ ልናነጋግራቸው በምንሻቸው ሰዎች ላይ በበላይነት ስሜት ሊሆን ከቶ አይቻልም:: እኛና እነርሱ ኀጢአት ሠርተናል፤ ከእነርሱ ጋር ለመነጋገር ያለን ተስፋም ለእኛ እንዲታይ የተደረገው ጸጋ ለእነርሱም እንዲታይ እንዲደረግ ነው::

አሁን ደግሞ በተሰጠው ምሳሌ መሠረት፣ አንተ ተበዳዩ ብትሆን፣ ከበዳዩ ጋር ያለውን ቅሬታ እንድትፈታ ኀላፊነት የተሰጠህ አንተ ነህ እንበል:: ይህን እንደምን ታከናውነዋለህ? በቊጣ መቀስቀስና ቊጣህን በእርሱ ላይ በማውረድ እንደ ጠላት መቊጠር እርሱን ከአንተ ማራቅ ነው:: ይሁን እንጂ እርሱን ይቅር ማለትና ሁሉንም ነገር መርሳት ይህም የተሻለ አይሆንም:: ይልቁን እንደ ባዕድና እንደ ዝቅተኛ ሰው አድርገህ እያየኸው ነው፤ ከዚያም በኋላ አንተን ባየህ ቊጥር

እንደ በደለህ ያስታውሳል፤ አንተም ባየኸው ቀጥር እርሱን ይቅር በማለትህ የቸርነት ሥራ እንደ ሠራህለት ታስታውሳለህ::

እንዲህ አይሆንም፣ እርሱ ወንድምህ ነው፤ ለእርሱ ያለህ አተያይም ወንድም ከወንድሙ ጋር እንደሚተያየው ዐይነት መሆን አለበት:: ጉዳዩን መያዝ ያለብህ በደሉ በአንተ ላይ እንደ ተፈጸመ አድርገህ ሳይሆን በሌላ ሰው ላይ እንደ ተፈጸመ አድርገህ ነው:: ነገሩን አንተ ሦስተኛ ወገን እንደ ሆንክ አድርገህ ያዘው (አስፈላጊ ነገር ቢከሠት በኋላ ላይ ለአንተ እንደሚደርስልህ ወንድም አድርገህ ያዘው):: ጌታም ይህን ስታደርግ ዐላማህ ምን መሆን እንዳለበት ግልጽ አድርጎ ይናገራል:: አንተ አሸናፊ የመሆንህ ጉዳይ ሳይሆን “ወንድምህን ገንዘብ አደረግኸው” የተባለው ጉዳይ ነው::

ይህን ሐረግ በርግጥ ማየት ያለብን፣ ሁሉንም ነገር እንደሚያካትት አድርገን ነው:: ይኸውም ወንድምህ ምላሽ ባይሰጥ ሁለት ወይም ሦስት ወገኖችን ምስክር አድርገህ መውሰድ ካለብህና እንደ ገና እርሱን መሻት ካለብህ፣ ዝንባሌህ የተለየ መሆን የለበትም:: አሁንም ቢሆን በእርሱ ላይ ክስ መመሥረት ሳይሆን ወንድምህን ገንዘብ ለማድረግ የመሻት ጉዳይ መሆን አለበት:: ጉዳዩ መጨረሻ ላይ ደርሶ መላው ቤተ ክርስቲያን ቢጠራ፣ በዚያም ላይ የዐላማ ለውጥ አይኖርም:: የተግሳጹ ግብ ያ ወንድም እንዲመለስ ነው:: በመንፈሳዊ ልቅና (መሻሻል) ረገድ ቢሆንም እንኳ፤ ሌላው “በእበልጠዋለሁ” ደረጃ ላይ ሆኖ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለውን ለማስተካከል እገኛለሁ በሚል ስሜት መቆም የለበትም::

ጳውሎስ እንዲህ ይላል፤ “መንፈሳውያን የሆናችሁ እናንተ እንደዚህ ያለውን ሰው በየዋህት መንፈስ አቅኑት፤ አንተ ደግሞ እንዳትፈተን ራስህን ጠብቅ” (ገላ 6፥1)::

ይህ አንድ ርምጃ ወደፊት ያመጣናል፣ ብልቶች (አባላት) በአንድ ላይ ሆነው ስላላቸው ስልጣን በማቴዎስ 18 ላይ ያለው ምንባባችን በእነዚህ ዋና ዋና ቃሎች ወደፊት ይጓዛልና፡- “በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል:: በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል” (ቊ 15-18):: ይህ ምንድን ነው? የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ፈላጭ ቈራጭነት አይደለም፣ በአናሳው ላይ የአብዛኞች ፍርድም አይደለም:: ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ የቤተ ክርስቲያን መነሣት ነው::





የአንድ አባል እርምት የሥራ ጉዳይ ተደርጎ ከቶ መታየት የለበትም፤ ይልቁን መላዋን ቤተ ክርስቲያን ከልብ የሚያሳስብ ጉዳይ መሆን አለበት:: የአንድ አባል እርምት ተራ ሥራ ሆኖ ከቶ መታየት የለበትም፤ ይልቁን መላዋን ቤተ ክርስቲያን ከልብ የሚያሳስብ ጉዳይ መሆን አለበት:: የእግዚአብሔርን ልጅ መገሠጽ እንደ ቀላል ነገር ተቈጥሮ በተራ አያያዝ ሲያዝ ማየት አስጸያፊ ነገር ነው፤ ጉዳዩን አግዝፎ በማየት ፍርድ ቤት ድረስ የመሄዱ ርምጃም አስጸያፊነቱ ከዚያ ያነሰ አይደለም:: ማንኛውም የእርምት ርምጃ በፈጻሚዎቹ ላይ ሐዘንና እንባ ማስከተል አለበት፤ ወይም ቤተ ክርስቲያን ምን እንደሆነች ቢያስተውሉ ኖሮ በግድየሽነት የሚታይበት ሁኔታ ከቶ አይኖርም ነበር:: ጳውሎስ “በእናንተ መካከል ዝሙት እንዳለ ይወራል” በማለት ጻፈ:: አስቀድሞ ነገር፣ ያን ኀጢአት ከአንድ ግለሰብ አማኝ ጋር አላላከከውም፤ ከቤተ ክርስቲያን ጋር እያያዘው እንጂ:: “እናንተም ታብያችኋል፤ ይልቅስ እንድታዝኑ አይገባችሁምን?” (1ቆሮ 5፥1፡2) አለ:: ያ ኀጢአት የመላ አካሉ ኀጢአት ነበር፤ ውርደቱና ሐዘኑም የአንዱ አባል ብቻ ሳይሆን የሙሉው አካል መሆን አለበት::

በቤተ ክርስቲያን የእርምት ርምጃ ውስጥ የክርስቶስ አካል አንድነት ያለው መሆኑን ማየት ያስፈልገናል፤ ይሁን እንጂ ማየት የሚያስፈልገን ሐቁን ብቻ ሳይሆን ኀጢአት ሊያደርስ የሚችለውን ጭምር ነው:: በወንድሜ ላይ የተከሠተውን ኀጢአት በመጀመሪያ በእኔ ላይ ማየት ያስፈልገኛል፤ ያን ኀጢአት በእኔ ላይ እስካልፈረድኩበትም ድረስ በእርሱ ላይ ለመፍረድ አልደፍርም:: በእግዚአብሔር ጸጋ የተነሣ ተመሳሳይ በደል ላልፈጽም እችላለሁ፤ ይሁን እንጂ ለዚያ ድርጊት የሚያነሣሣ ኀጢአት በእኔ ውስጥ አለ::

የእርምት ርምጃ ምንጊዜም የማስተካከል ርምጃ ነው፤ ዐላማውም ኀጢአት እየሠራ ያለውን ወንድም መመለስ ነው:: እጅግ በከፋው ሁኔታ ላይ እንኳ በአይታ ላይ ያለው ግብ “መንፈሱ በጌታ በኢየሱስ ቀን ትድን ዘንድ” የሚለው ነው (1ቆሮ 5፥3-5):: የእግዚአብሔርን ልጆች በተመለከተ በፍርዱ ሁሉ ምሕረት አለ፤ ስለ እርሱ ሆነን በልጆቹ ላይ ስንፈርድ፣ እንደ ቤተ ክርስቲያን ወይም እንደ ግለሰብ እንሁን (በቤተ ክርስቲያን ወይም በግለሰብ ደረጃ ይሁን)፣ በምሕረት የተሞላን ሰዎች መሆን አለብን:: የውጭው ሥራችን የእርምት ርምጃ ቢሆንም እንኳ የውስጥ ዝንባሌያችን ግን የፍቅር መሆን አለበት::

ጌታችን ከትንሣኤው በኋላ፣ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አለ፤ “መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ፤” ወዲያውኑም ቀጥሎ ያለውን አከለ፤ “ኀጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል፣ የያዛችሁባቸው ተይዘባቸዋል” አላቸው

(ዮሐንስ 20፥22፣ 23)፡፡ ሮም ይህን በተሳሳተ መንገድ አዋለችው፤ እኛም ሮምን በመቃወም፣ ይህን ሐሳብ ሳንቀበለው ቀረን፡፡ ነገር ግን ይህን በማድረጋችን እኛ ፕሮቴስታንቶች ያጣነው የቱን ያህል ነው! እግዚአብሔርስ ያጣው የቱን ያህል ነው! የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን የሆነው ሁሉ በቀላሉ ሊጣል አይችልም፡፡ "ቤተ ክርስቲያን" በአንድ ቤት የሚሰበሰቡ ጥቂት የገጠር አማኞች ቢሆኑም እንኳ፣ ራሳቸውን የክርስቶስ አካል መገለጫ አድርገውም ቢመለከቱ፣ ድካማቸውን በእርሱ ፊት በመናዘዝ ጥበቡንና ኀይሉን የእኛ ነው ቢሉ፣ ጌታ በዚያ ጸንቶ ይገኛል፡፡ "ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁ፡፡"

## የእግዚአብሔር ሐሳብ ሊገደብ የሚችል መሆኑ

አመራርንና ተግሣጽን (እርምትን) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አይተናል፤ አሁን ደግሞ ወደ ቤተ ክርስቲያን ጸሎት እንመለሳለን፡፡ ከዚህ ቀደም እንዳልነው በመሠረቱ ሁለት ዐይነት ጸሎቶች አሉ፡፡ የመጀመሪያው ግለሰባዊና አስተንትኖአዊ (devotional) ነው፡፡ ቀጥሎ ባሉት ተስፋዎች ላይ በዮሐንስ ወንጌል በጕንዮሽ አነጋገር ተገልጾ እናገኘዋለን፤ "አብም ስለ ወልድ እንዲከብር በስሜ የምትለምኑትን አደርገዋለሁ (14፥13፤ ከቍ 14 እና ከምዕራፍ 15፥7፣ 16፤ 23፣ 24 ጋር ያነጻ)፡፡ ከዚህ ላይ ቅድመ ሁኔታዎች የሉም፡፡ ለክርስቶስ አካል ሁሉ የተሰጠ ተስፋ ነው፤ ጸሎትንም ታላቅ ነገር ያደርገዋል፡፡ ከእነዚህ ሐሳቦች አኳያ፣ እግዚአብሔር ባይሰማና የግል ጸሎታችንን ባይመልስ በጸሎታችን ላይ (በልመናዎቻችን ላይ) አንድ ስሕተት አለ የሚል ስሜት ሊያድርብን ይችላል፡፡

ነገር ግን ሁለተኛው ዐይነት ጸሎት የመጀመሪያውን እንደ ያዘ ከዚያም በላይ ያልፋል፡፡ ይኸውም በማቴዎስ ምዕራፍ 18 ምንባባችን ላይ የተገለጸው ነው፤ "ደግሞ እላችኋለሁ፤ ከእናንተ ሁለቱ በምድር በማናቸውም በሚለምኑት ነገር ሁሉ ቢስማሙ በሰማያት ካለው ከአባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል" (ቍ 19)፡፡ ይህ የቤተ ክርስቲያን ተግባር ነው፣ ስለ ጸሎት ከእግዚአብሔር የተሰጣት አገልግሎት ነው፡፡ ከዚህ ላይ ያለው ተስፋ ቅድመ ሁኔታ አለውና፤ ቢያንስ ቢያንስ ሁለት መሆን አለባቸው፤ እነርሱም ደግሞ መስማማት አለባቸው፡፡

ጸሎታቸውስ ለምን ተሰማ? የሚቀጥለው ቍጥር ይገልጻል፦ "ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና፡፡" 'በሚሰበሰቡበት' (ገቢር ግስ)፤ እንዲሁ አይገናኙም፡፡ ልዩነቱን እናያለን፣ መሰብሰብ በራሳችን መንገድ መሄድ ማለት አይደለም፤ ዳዊትን ንጉሥ





ለማድረግ በኬብሮን ተሰብስበው የነበሩት በመንፈስ እንደ ተመሩት፣ በመንፈስ ቅዱስ መመራት ማለት ነው፡፡ የሚመጡት ለራሳቸው ጉዳይ ሳይሆን ለእርሱ (ለጌታ) አንድ የጋራ ጉዳይ ስላላቸው ነው፡፡ 'በስሙ' አንድ እንዲሆኑ ያደረጋቸው ይህ ነው፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ "በመካከላቸው እሆናለሁ" ሲል እየመራኋቸው፣ እየገለጥሁላቸውና እያበራሁላቸው ማለቱ ነው፡፡ ይህ ተስፋ ሳይሆን ሐቅ ስለሆነ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን! እርሱ ሲገኝ ለናውቃለኝ ያ መገኘት ደግሞ በምድር ሁለቱ እንዲህ ያለ ኀይል ለምን እንዳላቸው ይገልጻል፡፡

መንግሥቱን እውን ለማድረግ እግዚአብሔር የልጆቹን ጸሎት ይጠባበቃል፡፡ ይህ ዘመን አስፈላጊ ከሆነ፣ ቀጥሎ ያለው ዘመን ደግሞ ይበልጥኑ በርግጥ አስፈላጊ ነው፡፡ ዛሬ ያገኘነው መብትና ኀይል ሁሉ የሚመጣው ዘመን ቅምሻ ነው፡፡ ዛሬ የተደበቀው የእግዚአብሔር ሙላት በዚያ ዘመን ይታያል፡፡ ከዚህ አኳያ፣ "የጌታ ጸሎት" ብለን የምንጠራው የቱን ያህል አስፈላጊ እንደ ሆነ እናስተውላለን፡፡ ለብዙ ሺህ ዓመታት እግዚአብሔር ሕዝቡ እንዲጸልይ አዘዘ፤ ይሁን እንጂ ብምእት ዓመታቱ ዘመን፣ ከዚያ ጸሎት ውጭ ሌላ በምን ላይ መጸለይ እንዳለባቸው መመሪያ አልሰጣቸውም፡፡

"መንግሥትህ ትምጣ!" ለዚህ መጸለይ አለብን፡፡ መንግሥቱ በራሷ የምትመጣ ቢሆን ኖሮ ያ ትእዛዝ አይሰጠንም ነበር፡፡ ሥራው ሁልጊዜ ለሕዝቡ ለቀሰ ምላሽ ሆኖ የሚፈጸም በመሆኑ የእግዚአብሔር ሕዝብ መጸለይ አለበት፡፡ የጌታ ጸሎት ለእኔ የናሙና ጸሎት አይደለም፤ የእግዚአብሔር ልብ መገለጥ ነው፡፡ "እውነተኛ ጸሎት በእግዚአብሔር ልብ ይጀምራል፤ ለሰዎች ልብ እንዲታወቅ ሆኖአል፤ ተመልሶ ወደ እግዚአብሔር ተጸልዮአል፤ እግዚአብሔርም ይመልሳል፡፡" ይህ ከገለጻ በላይ ነው፤ እኔ እንደማምነው ከሆነ እግዚአብሔር በመላለም ውስጥ እየሠራበት ያለ መርሕ ነው፡፡

"ፈቃድህ ..... እንዲሁ ...... ትሁን!" እውነት ነው፤ ግን የት? "በምድር?" ዛሬ የእግዚአብሔር ፈቃድ የማይፈጸምበት ቦታ ይህ ብቻ ነውና፡፡ ታዲያ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደዚህ እንዴት ሊወርድ ይችላል? የዲያብሎስ ዐመፀኛ ፈቃድ እንዲወገድ በመሻት፣ ካልተፈጠረው ፈቃድ ጋር ኅብረት በማድረግ፣ በተፈጠረው ፈቃድ አማካይነት ነው፡፡ ጸሎት ምንጊዜም ባለሦስት ጕንዮሽ ነውና፡፡ በፊቱ ጸሎት የሚቀርብለትን፣ የሚጸለይለትን፣ በእርሱ ላይ ጸሎት የሚቀርብበትንም ያካትታልና፤ በምድር ላይ ደግሞ በእርሱ ላይ ጸሎት የሚቀርብበት ነገር አለ፤ ይኸውም የእግዚአብሔር ታቃዋሚ የሆነው ፈቃድ

ነው:: በዚያ ዐመፀኛ ፈቃድ ላይ እግዚአብሔር ብቻውን አይሠራም፤ የእኛን ጸሎት ይጠብቃል::

እግዚአብሔር ለውሱንነት በፈቃዱ ራሱን የሰጠ ስለ መሆኑ የሚያረጋግጡ በወንጌላቱ ውስጥ አያሌ ምንባቦች አሉ:: ኢየሱስ ወደ ገሊላ ከተማ እንዳይገባ የተከለከለ ስለ መሆኑ ወይም ወደ ሰማርያ አገር እንዳይገባ ስለ መከልከሉ፤ ወይም ደግሞ በናዝሬት የታምራት ሥራ ለመሥራት እንዳልቻለ እናነባለን (ማር 14፥5፤ ሉቃ 9፥53፤ ማር 6፥5):: "እንዴት አጨነቃለሁ!" "ልጆችሽን እሰበስብ ዘንድ ስንት ጊዜ ወደድሁ! አልወዳዳችሁምም ብሎ መጮኽ ቻለ፤ ነገር ግን "ሕይወት እንዲሆንላችሁ ወደ እኔ ልትመጡ አትወዱም::" (ሉቃ 12፥50፤ ማቴ 23፥37፤ ዮሐ 5፥40):: ስለዚህ የስንዴ ቅንጣት በምድር ወድቃ ካልሞተች ሌላ ምርጫ የላትም፤ ዛሬም ቢሆን የእግዚአብሔር ቃል "በእሾክ መካከል" መዘራት አለበት (ዮሐንስ 12፥24፤ ማቴ 13፥22):: በብሉይ ኪዳን በየትኛውም ቦታ እንደሚገኝ ሁሉ፣ ተመሳሳይ ነገር በኋለኛው የዐዲስ ኪዳን ታሪክ ይቀጥላል:: የመለኮታዊ የትድግና ውሃ የተደገፈው በሰው ቦይ አመችነት ነው:: የምፈስ ዘይት ቀሪ ሌላ ማድጋ እስከማይኖር ድረስ ይወርዳል:: "እነሆ፣ የእግዚአብሔር እጅ ከማዳን አላጠረችም፤ ጆሮውም ከመስማት አልደነቈረችም፤ ነገር ግን በደላችሁ ....." (2ነገ 3፥16፣ 18፤ 4፥6፤ ኢሳ 59፥1፣ 2)::

ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ እንዴት በሰው ሊወሰን ቻለ? ይህስ እስከ ዘላለሙ ይቀጥላልን? ርግጥ ነው፤ እግዚአብሔር ኤልሻዳይ ነው! ሁሉን ቻይ እግዚአብሔር ነው፤ ያለፈው ዘላለምና የሚመጣው ዘላለም እርሱን መወሰን አይችሉም፤ የሚይዘው፣ የሚያደናቅፈው፣ ወይም የሚያዘገየው ነገር አይኖርም::

ነገር ግን እግዚአብሔር ፈቃድ አለው፤ ሕይወቱን የሚጋራ፣ ወልድንም ከሚገልጥለት ሕዝብ ጋር ኅብረት ለማድረግ ይፈልጋል:: ለዚህ ግብ ሰማይንና ምድርን ሰውንም ፈጠረ:: ከዚያም ችግር ተጀመረ:: ዐላማውን ለማሳካት እግዚአብሔር ባለ ፈቃድ የሆነውን ሰው ፈጠረ፤ የሰው ነጻ ፈቃድ እስከሌለም ድረስ ያን ዓለም ላለመፈጸም ውሳኔ አድርጎአል:: ይህ የተቀደሰ መርሕ ነው፤ ከዚህ የላቀ ሌላ ነገር የለም:: ይህ ማለት በዘላለሙ እግዚአብሔር ሉዐላዊ ቢሆንም በጊዜ ውስጥ ከዚህ ላይ ለእነርሱ ነጻ ፈቃድ ሲል ፍጥረቶችን ከማስገደድ ይልቅ የራሱን ሁሉን ቻይነት ለመገደብ መርጦአል:: ሰው ለእግዚአብሔር ኀይል እንዲያመቻች ወይም መንገዱን እንዲያደናቅፍ ሥልጣን ተሰጥቶት ነበር::





መለኮታዊው ፍቅር ድል እንደሚያደርግና ከዚህ ውጤት የተነሣም በሚመጣው ዘላለማዊነት እንደሚገለጥ በማወቅ እግዚአብሔር ለእንዲህ ዐይነቱ ውሱንነት ራሱን ለማስገዛት ተዘጋጅቶ ነበር:: ለዚህም ግብ ይሠራል:: የእርሱ ክብር፣ በሚመጣው ዘመን፣ የሰው ነጻ ፈቃድ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር አንድ የሚሆን መሆኑ ነው:: የዚያኛው ሁሉን ቻይነት ካለፈው ዘላለማዊነት ከፍ ባለ መልኩ በግብረገብ ረገድ የላቀ ይሆናል፤ ምክንያቱም ሊሆን የሚችል ውሱንነት ይኖራልና:: ሰው አሁንም ሳይታዘዝ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል፤ ነገር ግን ይህን ለመፈጸም ከቶ አይመርጥም:: የተለያየው፣ የተፈጠረውም የሰው ፈቃድ ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር ይሆናል፤ ይህም ክብር ነው::

ከዚህ ግብ ለመድረስ እግዚአብሔር ችግር ውስጥ ለመግባት ፈቃደኛ እንደ ነበር እናውቃለን፤ ይኸውም የሰው የመጀመሪያ ምርጫ ወደ አልፈለገው አቅጣጫ በመራው ጊዜ ነበር፤ የጠፋውን ለመቤዠት ሲል አብ የተወደደውን ወልድን ላከ:: የእርሱ ፈቃድ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር አንድ ሆኖ የተገኘበት እርሱ ነው፤ እግዚአብሔር ይመስገን! በሞቱና በትንሣኤው በመንፈስ ቅዱስም ኀይል፣ ሳልተፈጠረው ፈቃድ ብልቶቹ የሚገዙበት አካል እውን ሆኖ ነበር:: በእነርሱ የመለኮት ውስንነቶች ለዘላለሙ ይወገዳሉ:: በመንፈሳዊ ዓለም ውስጥ እነዚህ ከፉ ሁኔታዎች ይወገዱ ዘንድ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ኀይል ወደ ዓለም እንዲለቀቅ ታደርጋለች:: ቤተ ክርስቲያን - በአክብሮት እናገራለሁ፣ የራሱን የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት ወደ እግዚአብሔር ትመልሳለች::

ጸሎት ለእግዚአብሔር ሲባል፣ የእርሱ ፈቃድ እንዲፈጸም በማወጅ፣ የአሁኑን የእኔን ፈቃድ የማሳይበት (የምለማመድበት) መንገድ ነው:: ይህ እውነተኛ ጸሎት ነውና፤ ይኸውም እግዚአብሔር እንዲታወቅ የሚያደርገውን እኛ እንገልጻለን ማለት ነው:: እግዚአብሔር አስቀድሞ ፈቃዱ ያደረገውን፣ ሰው ፈቃዱ ያደርገዋል፤ ይናገረዋልም:: ይህ "የእግዚአብሔር ፈቃድ ነውን?" ብለን እንጠይቃለን እንጂ "የእኔ ጸሎት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ነውን?" ብለን አንጠይቅም:: መነሻው (ጅማሮው) የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፤ እኛ እናሰማዋለን፤ እግዚአብሔር ይፈጽመዋል:: እኛ ካላሰማነው አይፈጸምም:: ስለዚህ የእኛ ጸሎት የእግዚአብሔር ኀይል ሊመጣ የሚችልበትን መንገድ ያመቻቻል:: እንደ ብርቱ ተንቀሳቃሽ ኀይል፣ የእርሱ ኀይል የማይቋቋሙት ዐይነት ነው፤ ይሁን እንጂ ሐዲድ ከሌለ ወደ እኛ ሊደርስ አይችልም:: ሰዎች መጸለይ ሲያቆሙ፣ እግዚአብሔር መሥራትን ያቆማል፤ ያለ እነርሱ ጸሎት

ምንም አያደርግምና:: የሰማይን ኀይል ችግር ወዳለበት ቦታ የሚመሩት እነርሱ ናቸው::

ማቴዎስ 18፥18-20ን እንደ ገና አንብቡ፤ በጸሎት ረገድ የቤተ ክርስቲያንን አያሌ የኀላፊነት አድማስንም አስተውሉ:: የቤተ ክርስቲያን የኀላፊነት ልክ ዛሬ በምድር ላይ የእግዚአብሔር ኃላፊነት ልክ ነው:: እርሱ ራሱ በኢየሩሳሌምና በገሊላ በኢየሱስ በኩል እንደ ተገለጠ ሁሉ፣ ዛሬ ደግሞ በዓለም ውስጥ ቤተክርስቲያን ባለችበት በየትኛውም ቦታ በእርስዋ በኩል ተገልጦአል:: የሚመጣውን ትውልድ የምትወክል ቤተ ክርስቲያን ብቻ ስለሆነች እርስዋ ካለችበት መጠን (ስፋት) ሊሄድ አይችልም:: በምድር ላይ ቤተክርስቲያን እግዚአብሔርን ወክላ ትገኛለች፤ እርሷ ነጻ የለቀቀችውንና ያሰረችውን ሰማይ ነጻ ይለቀዋል፤ ያስረዋልም:: ዛሬ በምድር ላይ የእግዚአብሔር ኀይል ታላቅነት የፀሎቷን ያህል ነው፤ ከዚህ የላቀ አይደለም:: በዘላለሙ ዐላማው አኳያ የሚሠራውን ሁሉ በእርሷ በኩል ይሠራል፤ በሥራዋ ወደ ኋላ በተጐተተችበት መጠን፣ በዚያው ልክ እርሱ ተወስኖአል::

ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ኀይል መጨመር አትችልም፤ ልትገድበው (ልትወስነው) ግን ትችላለች:: እርሱ በፈቃዱ ለመሥራት ያልፈለገውን ቤተ ክርስቲያን እንዲፈጽመው ማድረግ አትችልም፤ ይሁን እንጂ እርሱ የፈቀደውን ልታደናቅፍ ትችላለች:: በመንግሥተ ሰማይ እርሱ የሚያስራቸውና ነጻ የሚለቃቸው ብዙ ነገሮች አሉ፤ ይኸውም የሚያደናቅፉ ነገሮች የሚታሰሩ፣ መንፈሳዊ ፋይዳ ያላቸው ነገሮች የሚለቀቁ ናቸው፤ ይሁን እንጂ በምድር ላይ ያለ እንቅስቃሴ የሰማይ ላዩን እንቅስቃሴ መቅደም አለበት፤ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያኑ ትንቀሳቀስ ዘንድ ምን ጊዜም እንደጠበቀ ነው::

"በምድር የምታስሩት ሁሉ"፣ እነዚህ ወድ ቃሎች ናቸው:: ከዚህ ላይ መንግሥተ ሰማይ በምድር ተለከቶአል:: እኛ ከምንጠይቀው ልክ በላይ ምንጊዜም የላቀ ኀይል አለና፤ እኛ በምድር ከምንጠይቀው በላይ የሚፈታ (የሚለቀቅ) ወይም የሚታሰር ሁልጊዜ በሰማይ አለ:: ከኀጢአት ትድግናን ለምን እንፈልጋለን? ጽናት እንድናገኝ ለምን ወደ እግዚአብሔር እንጮኻለን? "ፈቃድህ በእኔ ይፈጸም" ብሎ መጸለይ መልካም ጅማሮ ነው፤ ሆኖም "በምድር ይሁን" በማለት መቀጠል አለብን:: ዛሬ የእግዚአብሔር ልጆች በጥቃቅን ነገሮች ተይዘዋል፤ ይሁን እንጂ ጸሎታቸው የታቀደው የሰማይ ታምራዊ ኀይል ይለቀቅ ዘንድ ነው:: ለራስ ወይም ለጊዜያዊ የግል ጒዳይ የሚቀርበው ጸሎት ወደ መንግሥቱ ጸሎት ማምራት አለበት:: የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ምንድን





ነው? ለሚለው ጥያቄ መልሱ ይህ ነው:: የሰማይ ኀይል የሚለቀቅባት፣ የእግዚአብሔር ዐላማም የሚፈጸምባት ዘዴ፣ የመንግሥተ ሰማይ መውጪያ ናት:: በመንግሥተ ሰማይ ብዙ ነገሮች ተከማችተዋል፤ ምክንያቱም እስካሁን ድረስ በምድር ላይ መውጪያ ገና አላገኙም:: ቤተ ክርስቲያን ገና አልጸለየችም::

እግዚአብሔር ይህን እንዴት ያስፈጽማል? ቤተ ክርስቲያንን በእርሱ ጐን እንዴት አድርጎ ሊያሰልፍ ነው? በዛሬ ሁኔታዎች፣ የእግዚአብሔር መውጪያ (outlet) የመሆን አገልግሎት ልንፈጽመው የምንችለው ትልቁ ሥራችን እንደሆነ እያንዳንዳችንን በማስታወስ ብቻ ነው:: እግዚአብሔር የሚፈልገውን ያሳያል፤ እኛም ነቅተን እንጠይቃለን፣ እግዚአብሔር ደግሞ ከማይ ይሠራል:- ይህ እውነተኛ ጸሎት ነው፤ በጸሎት ስብሰባዎቻችን ላይ ሙሉ በሙሉ ማየት ያለብንም ይህንኑ ነው:: ሌሎች በታዎች ይቅሩና፣ ከዚህ ያለችው የሻንጋይ ቤተ ክርስቲያን፣ ይህን የጸሎት አገልግሎት የማታውቅ ብትሆን እግዚአብሔር ይቅር ይበለን! ያለ እርሱ፣ ሌላው ሁሉ ባዶ ነው፤ እግዚአብሔር ከዚህ ላይ ሌላ ዕቃ የለውም:: "በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ፤ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም" (ማቴ 7፥21):: መንግሥተ ሰማይን በእይታ ውስጥ በማድረግ፣ ያለን ሁሉና የሆነው ሁሉ ለእግዚአብሔር ፈቃድ መሆን አለበት:: እግዚአብሔር ይህን ይፈልጋል:: በጸሎት የሚጸኑ፣ በጠላት ኀይልም ላይ ጦርነት የሚከፍቱ፣ ደግሞም የሚመጣውን ዘመን እውን የሚያደርጉ፣ ከዓለም ሕዝብ ሁሉ ያሉት በጣም ጥቂት መሆን አለባቸው:: ያ ድል አድራጊነት ነው:: አባላት ብዙ ወይም ጥቂት ይሁኑ፣ ለእርሱ በጥልቅ፣ በብርቱና በድል አድራጊ ጸሎት እንድንበረታ እግዚአብሔር ብርታታችንን ያጽናልን::

## የኀይለኛውን ሰው ሸቀጦች ማበላሸት

"ጠላቶቻችሁንም ታሳድዳላችሁ፣ በፊታችሁም በሰይፍ ይወድቃሉ:: ከእናንተም ዐምስቱ መቶውን ያሳድዳሉ፤ መቶውም ዐሥሩን ሺህ ያሳድዳሉ፤ ጠላቶቻችሁም በፊታችሁ በሰይፍ ይወድቃሉ (ዘሌ 26፥7፣ 8):: ይህ ለእስራኤል እንደ ሕዝብ እግዚአብሔር የሰጣቸው ተስፋ ነበር፤ የሆነ ሆኖ ግን አቈጣጠሩ አስገራሚ ነበር፤ አንዱ አንዱን ሺህ፣ ሁለቱም ዐሥሩን ሺህ አሳድደዋል ተብሏልና (ዘዳ 32፥30):: በግል ወይም በኅብረት፣ ለብቻ ወይም ሁለቱ አንድ ላይ ሆነው፤ ከዚህ ላይ በርግጥ የጸሎት ሥዕል ይገኛል:: በምድር ላይ ሁለቱ ሲስማሙ፣ ሰማይ ዐሥሩን ሺህ ጠላት ያስራል:: የእግዚአብሔር

ሰዎች፣ በችግር ጊዜ፣ እነዚህን የኢየሱስ ቃሎች ብዙ ጊዜ እንዳሉ በመቀበል እውነተኛነታቸውን የቱን ያህል አረጋገጡ! ጴጥሮስ በእስር ቤት ታስሮ በነበረበት ሌሊት በኢየሩሳሌም ዙሪያ ያለችው ቤተ ክርስቲያን ተንበርክካ ጸለየች፤ ለዚያ ጸሎት ከሰማይ የሆነው መልስ የሄሮድስን ኀይል ሁሉ እንዳልነበረ አደረገው:: ሌላ መንግሥት ይዞታውን ወርሶት ነበር፤ ታላቁ የእስር ቤት መዝጊያ እንኳ እጁን ሰጥቶ ራሱ ተከፈተ::

ሌላ መንግሥት ይዞታውን (ግዛቱን) ወርሶት ነበር:: ይህን ሐሳብ ለማብራራት፣ ከዘመኑ ታሪክ ውስጥ ምሳሌ አድርጌ ልጠቀም:: ብዙዎች ምዕራባውያን እንደሚያስታውሱት፣ ከምእት ዓመት በፊት ከቻይና ጋር ይገበያዩ የነበሩት ታላቅ ባዕዳን (የውጭ) ኀይሎች እስከ ዛሬ ድረስ ቻይናውያን ቂም የያዙበትን መርሕ በእነርሱ ላይ ለመጫን የጦር ኀይላቸውን ተጠቀሙ:: ብዙ ጊዜ "የውጭ አገር ግዛት" ተብሎ የሚጠራውን አመለከታለሁ:: በዚህ መርሕ መሠረት የተወሰኑ የቻይና ግዛቶች ለባዕዳን ኀይላት ተሰጥተው ነበር፤ የእነዚህ ኀይላት ገዦችም የቻይናን ሕግ በግላቸው ቢተላለፉ የሕግ ርምጃ እንዳይወሰድባቸው ሆነው የፈለጉትን እንዲሠሩ ተደርገው ነበር:: በሸንጎ ላይ ጒዳያቸው ሊታይ ይችላል፤ ወይም በገዛ አገራቸው የፍርድ አካል ጒዳያቸው ሊታይላቸው ይችላል፤ እንዲህ ሲታይ ደግሞ በቻይና አገር ሕግ ሳይሆን በአገራቸው ሕግ ነበር የሚዳኙት:: እንዳሻቸው የሚከናወን ሥራ ነበር፤ ዛሬ ዛሬ ሁሉም ዜጋ በላዩ ላይ ተጭኖ የነበረው ሕግ ኢፍትሐዊ እንደ ነበር ልብ ይላል:: ሆኖም፣ አሳስቶ መረዳት ሊኖር ይችላል የሚል ሥጋት ሳይኖር፣ በየትኛውም መልኩ ኢፍትሐዊ ያልሆነውን፣ በጣምም ልዩ የሆነውን አጉልቶ ለማሳየት ልንጠቀምበት እንችላለን፤ ይኸውም በዚህ ዘመን ውስጥ ይህች ምድር በሰማይ የቸርነት አገዛዝ መወረሯ ነው::

ይህ ምሳሌ እኛን እንዴት ሊመለከት ይችላል? የሚመለከተው በሁለት መንገድ ነው:: በመጀመሪያ እኛን በተመለከተ እግዚአብሔር እኛን "መንግሥትም . . . እንድንሆን" አድርጎአል (ራእ 1፥5፣ 6):: እንደዚህ ዓለም አመለካከት ከሆነ፣ እኛ 'የባዕድ' ኀይል ዜጎች ነን:: ከጨለማው መንግሥት ትድግናን ያገኘን በመሆናችን በሥልጣኑ ሥር ለምትገኘው ለዚህች ዓለም አለቃ ተገዦች አይደለንም:: በዚህ ፈንታ ግን የሌላ ንጉሥ ተገዦች ነን፤ ብሎም የሚገዛን ሌላ ሕግ ነው:: ማንነታችንን በተመለከተ ከዚህ ምድር ውጭ የሆነ መብት አለን::





ይሁን እንጂ ሁለተኛውም፣ ይህን ዓለም በተመለከተ፣ ከዚህም ላይ የይገባናል ጥያቄ ልናቀርብ እንችላለን:: ሰው በምድሪቱ ላይ የበላይ (ገዥ) እንዲሆን ተፈጥሮ ነበርና፤ ዐጥቶ የነበረውን የሰው ልጅ እንደ ገና አገኘው:: ዛሬ፣ የመንፈሳዊ - ዓለም መሪዎች ያን ግዛት ነጥቀዋል፤ የቤተ ክርስቲያን ተግባርም እነርሱ የነጠቁትን የእኛ ነው በማለት መጠየቅ ነው:: እርሱ ራሱ 'ገዥ' ቢሆንም እንኳ፣ ሰይጣን ነጣቂ ነው፤ በእግዚአብሔር ርስት ላይ ያለ ፈቃድ ሕገ ወጥ የሆነ ተጠቃሚ ነው::

ለምሳሌ አንድ ሰው እንደ ምንም ብሎ ወደ ቤትህ ገብቶ አንተ ሳትፈቅድለት ቤትህን ያዘው እንበል:: ምን ታደርጋለህ? ወደ ፍርድ ቤት ትሄዳለህ፣ በአገሩ ሕግ መሠረት አቤቱታ በማቅረብ በእርሱ ላይ ታስፈርዳለህ:: የፍርድ ማዘዣ ይዘህ በመመለስ ታስወጣዋለህ:: ባለ መታሰሩ ዕድለኛ ሊሆን ይችላል! ይሁን እንጂ በዚህ ዓለም ላይ ያለው ሁኔታም ከዚህ የተለየ አይደለም:: የእግዚአብሔር "የሕግ መጽሐፍ" የዚህ ዓለም ሕገ-ወጥ ያዥ ላይ ፈርዶአል:: እርሱ መልቀቅ ይኖርበታል! ዋና ጒዳይ የሆነው በሰይጣን ዐይን የመንግሥተ ሰማይ ሕግ "ባዕድ" ሕግ ነውን? ቀራንዮ የዚያን መንግሥት የበላይነት መሥርቶአል:: በመስቀል ላይ፣ ክርስቶስ የሰይጣንን ሕጋዊነት ሽሮአል:: አሁን ግን ሕጉ በሥራ ላይ መዋሉን የማረጋገጡ ተግባር የቤተ ክርስቲያን ሥራ ነው:: በምሳሌው ላይ እንዳለችው መበለት ወደ እግዚአብሔር በመጮኽ፣ "ጠላቴን ተበቀልልኝ!" ብላ የመንቅያውን ማዘዣ ይዛ ማስወጣት አለባት:: እግዚአብሔር ያን ጩኸት እየጠበቀ ነው:: በተሰጠን ጊዜና ሁኔታ፣ በቃሉ አማካይነት፣ በክፉ ኀይላት በተያዘው መንፈሳዊ ግዛት ላይ እግራችንን ማሳረፍ አለብን፤ ያን እግራችን ያረፈበትንም ግዛት (ክልል) የእግዚአብሔር ነው በማለት ማወጅ አለብን::

ለዚህ ሥራ የሚያስፈልጉት ምን ዐይነት ሰዎች ናቸው? እንደ ገና እለዋለሁ፤ ተራ አማኞች ናቸው፣ ሁለት ወይም ሦስት አንድ ላይ ሆነው ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ጌታ በመካከላቸው ከነርሱ ጋር ሆኖ ማለት ነው:: ኀይለኛውን ሰው እኛ ማሰር የለብንምና - ያ ተከናውኖአል - እኛ ማድረግ ያለብን ከታሰረበት ስንሰለት ማምለጫ መንገድ የሌለው መሆኑን ማስታወስ ነው! ይህ ምን ማለት እንደ ሆነ አንድ ታሪክ በመንገር ላሳያችሁ::

በቻይና ውስጥ በአንድ ከተማ ሁለት እኅትማማቾች ነበሩ:: የተማሩ አልነበሩም፣ በሰውኛ ቋንቋም፣ "ብሩኅ" አእምሮ ያላቸው አልነበረም፤ ይሁን እንጂ ጌታን በተወሰነ ደረጃ ዐውቀዋል:: ከዕለታት አንድ ቀን ዐመፀኛ፣ አደገኛና

እንናፍቃለን፡፡ ከዚህም በላይ እግዚአብሔር ለዚህ አገልግሎት ሲባል ለቤተ ክርስቲያን "የተወሰኑ ወንጌል ሰባኪዎችን" ብቻ አልሰጠም፤ ያለ ጥርጥር እያንዳንዳችንን፣ "የወንጌል ሰባኪን ተግባር አከናውን" (አመት) ይለናል (ኤፌ 4፥ll፤ 2ጢሞ 4፥5)፡፡

ነገር ግን ከዚያ ላይ እናቆማለን? ሦስት ሺህ ወይም አራት ሺህ አማኞች ሁሉም ድነው ሁሉም በመንፈሳዊ ጉዞአቸው በመልካም ሁኔታ ሲጓዙ ስናይ ሥራው በሚገባ ተከናውኖአል የሚል ስሜት ያድርብናልን? ሥራው ገና ተጀመረ ብለን ማሰብስ የለብንምን? ከሦስት ሺሁ ወይም ከአራት ሺሁ መካከል እግዚአብሔር ወዳመጣቸው ወደዚያ ሰማያዊ ሰው ቀና በማለት የጨረፍታ እይታ ያገኙት ስንቱ ናቸው ብለን ራሳችንን መጠየቅስ የለብንምን? እስካሁንስ አሐድ (ጓድ) ብቻ፣ በወጥመድ ውስጥ ያሉ ፆሦች፣ "በዘመቻ ውጤትም" በዝርዝር ውስጥ የሚገኙ አሐዞች ናቸውን? ወይስ ሉዐላዊ ራእይ ይዞአቸዋል? እኛን አስቀድሞ ከልያዘን በቀር በርግጥ እነርሱን አይዛቸውም፡፡ ስለዚህ እንደ ገና እጠይቃለሁ፤ በሁሉም ረገድ ወደ ራስ - ወደ ክርስቶስ - ያድጉ ዘንድ ሐዋርያት ሸክም እንደ ነበራቸው እኛስ ሸክም አለን?

እነዚህ ጥያቄዎች ከባድ አንድምታዎች እንዳላቸው ዐውቃለሁ፡፡ እነርሱን መጋፈጥ አንዳንዶቻችንን እንደ እነዚህ ያሉ ባለ ክብር ሐሳቦች ከተገደፉባቸው (ከቀሩባቸው) ሐሳቦችና ትውፊቶች ጋር ሊያጋጩን ይችላሉ፡፡ በግል የሚሠራው አብዛኛው ሥራ እንደ ገና መገምገም ይኖርበት ይሆናል፡፡ ብዙ "ራሶች" መቈረጥ፣ የራሳችንን ጨምሮ ብዙ አእምሮዎች እንደ ገና መስተካከል፣ ብዙዎች ሰብአዊ ባለሥልጣናትም ለአንዱ ለጌታ ብቻ የበላይነት (አገዛዝ) ቦታ እንዲለቁ መደረግ ይኖርባቸው ይሆናል፡፡

በእውነት የምችል ከሆነ፣ እናንተ በምንም ሁኔታ ቢሆን ወደ እግዚአብሔር ሙሉ ሐሳብ ትገቡ ዘንድ ለመጫንና ለማስገደድ እንደምሻ መናዘዝ እፈልጋለሁ፡፡ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ምን ሐሳብ እንዳለው የማናይ ከሆነ ማስገደድና መግጸን ዋጋ የለውም፤ ይህን ስል አመክንዮውን ማየት ማለቴ አይደለም፡፡ አመክንዮውን ብቻ የምናይ ከሆነ፣ ከዚያ ድምዳሜ ላይ እንዴት እንደ ደረስን ብዙ ጊዜ ራሳችንን ማስታወስ ሊኖርብን ነው፤ ወይም ብዙ ሳይቆይ እንደ ገና ወደ ኋላ እንመለስ ዘንድ በቀላሉ እንወዘወዝ ይሆናል፡፡ ነገር ግን በክርስቶስ የእግዚአብሔርን ዐዲስ ሰው አንድ ጊዜ ካየን፣ ሰማያዊ እውነታ ለእኛ ግልጽ ይሆንልናል፤ ነገሮችም ደግሞ እንደቀድመው አንድ ዐይነት አይሆኑም፡፡ ብዙ ጊዜ አመክንዮ እንዲህ ይላል፤ "በሌላው በአንዳንድ የዓለም





ክፍል ደህና ሊሆን ይችላል፤ ይሁን እንጂ እኔ ባለሁበት ሁኔታ፣ ነገሮች አስቸጋሪዎች ናቸው፤ እንዲያውም የማይሞከሩ ናቸው፡፡ በቃሉ ላይ የማየውን ልብ በማለት (በመገንዘብ) ተስፋ እንደሌለ አስተውላለሁ፤ ስለዚህ ቀለል ባሉ ነገሮች እፎይ ልበል፡፡" ነገር ግን ወደጆቼ ሆይ፤ ሰዎችን የሚያመጣቸውን የመረቡን የተባረከ አገልግሎት ከቶ መናቅ ባይኖርብንም፣ እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል እንዲያደርና ዛሬም ሙላቱን እንዲገልጥ፣ ጳውሎስንም በመከተል የአካል እይታ እንዲኖረን ጸጋን እንፈልግ፡፡

ስለ ቤተ ክርስቲያን እንዲህ በማለት ይነግረናል፤ እርስዋም አካሉና "ሁሉን በሁሉ የሚሞላ የእርሱ ሙላቱ ናት፡፡" እርሷ ጥበቡን፣ ሕይወቱንና ኀይሉን የምትይዝና የምትገልጽ ዕቃ ናት፡፡ እንዲህ ያለ ሙላት በግለሰብ (በየግል) ሊታወቅ አይችልም፡፡ ሐዋርያው ይህን የሚናገረው በአጽንዖት ነው፡፡ በመንፈስ አማካይነት የእግዚአብሔር መኖሪያ የምንሆነው በአንድነት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ጥበብ ለመንፈሳዊ ኀይሎች የሚገለጠው በቤተ ክርስቲያን በኩል ነው፡፡ የመለኮትን ፍቅር ሙላት የምንቀበለው ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ነው፡፡ ወደ ሙሉው ሰው የምንደርሰው ከክርስቶስ አካል ጋር ነው፡፡ በክፉው ቀን መቋቋም የምንችለው ሙሉውን የጦር ዕቃ ስንለብስ ነው (ኤፌ 1፥23፤ 2፥22፤ 3፥10፣ 18፣ 19፤ 4፥13፤ 6)፡፡ በኤፌሶን መልእክት ላይ የሚጠቀመው ማመሳሰያ፣ የሙሉነት ዕቃ፣ ግለሰቡ ሳይሆን፣ ቤተ ክርስቲያን መሆኗን ክርክሩን አጠንክሮ ያሳያል፡፡

ዛሬ የእግዚአብሔር ልጆች እንደ አካል በአንድ ላይ ስለማይሠሩ፣ የሚያፈስ ዕቃ ሆነዋል፡፡ ብርጭቆውን ሰባብረውና፤ ከዚያስ ምን ይሆናል? እያንዳንዱ ስብርባሪ ትንሽ ውሃ ይይዝ ይሆናል፤ ያልተሰበረው ብርጭቆ ይዞት ከነበረው ጋር ሲነጻጸር ግን ምንም አይደለም፡፡ በመንፈሳዊ ነገሮችም ሁኔታው እንደዚሁ ነው፡፡ ግለሰብ ይቀበላል፣ ግን በሁለት ጐንዮሽ ነው፤ ቤተ ክርስቲያን የምትቀበለው ግን በሦስት ጐንዮሽ ነው፡፡ ዐሥር ሺህ ክርስቲያኖች አንድ ነገር ናቸው፤ ዐሥር ሺህ የአካሉ አባላት ግን የተለዩ ነገሮች ናቸው፡፡

ራእዩ ፍጹም የሚሆነው ለመላዋ ቤተ ክርስቲያን ራእይ ሲሆን ነው፡፡ ራስ የሆነው ዛሬ ብዙ የሚሰጠው ገና አለው፤ አካል ግን ያን መያዝ የማይችል፣ የሚያፈስ ዕቃ ሆኖአል፡፡ በእምነት ረገድ ግለሰቦች የማይናቅ እድገት ማሳየታቸው ፍጹም እውነት ነው፤ ይህ ግን በግለሰብ ደረጃ ብቻ ነው፤ በክርስቶስ ሙላት ክብር ልክ ወደ ፊት ትንሽ (አንድ ኢንች) እንኳ ፈቀቅ አይሉም፡፡ ወደ አንዱ ዕቃ መመለስ ያስፈልጋል፡፡ አንድ ዐይነት አስተምህሮን

ስለ ማመን፣ ወይም አንድ ዐይነት ዘዴን ስለ መጠቀም፣ ወይም ከሁሉም ጋር ኅብረት ስለማድረግ ማለት አይደለም፤ ከእነዚህ ማንኛቸውም በቂ አይደሉም:: በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሆነን ራሳችንን በአንድ አካል ውስጥ ማየት አለብን:: ጌታ ልባችንን ያበራልን ዘንድ እንጠይቀው::





# ምዕራፍ ዐሥር

## ዩሐንስ - እና እውነት

ወደ ሕይወቱ መጨረሻ ሲቃረብ፣ ጳውሎስ ለወጣት የሥራ አጋሩ ለጢሞቴዎስ መልእክት ጻፈ:: ይህ መጨረሻ ላይ የሚገኘው የሐዋርያው መልእክት የመንፈሳዊ መሸቀልቀልና የመለየት ሸክም አለው የሚል አሳዛኝ ስሜት ሊያድርብን ይችላል:: ይሁን እንጂ ከሐዋርያት ሞት በፊት እንኳ፣ ያ መንፈሳዊ መለየት የገባ ስለሆነ፣ ዛሬ በተመሳሳይ ሁኔታ ላሉት ቅዱሳን በዐዲስ ኪዳን ገጾች ላይ መመሪያ የተገኘው ከዚህ የተነሣ ነው::

ብዙዎች እምነታቸውንና ተስፋቸውን እያጡበት ባለ ጊዜ፣ ክርስቲያናዊ መለኪያቸውን እያቃለሉ ባሉበት ጊዜ ግራ መጋባት ቀላል ነገር ነው:: የእግዚአብሔር ልጆች እምነት እንዲህ መለወጥ ከቻለ፣ ሊለወጥ የማይችል ነገር ይኖር ይሆን እንዴ? እንል ዘንድ እንፈተናለን:: እውነት ነው፣ ጌታ ራሱ ከቶ አይለወጥም፤ ወደ ላይ እየተመለከተን እርሱን ብናመሰግነውም እንኳ፣ ያ እንዳለ ሆኖ ዙሪያችን ተመልከተን ግራ እንጋባለን:: ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ በጳውሎስ በኩል የማይለወጠውን አንድ ነገር ያሳየናል:: "ሆኖም፡- ጌታ ለእርሱ የሆኑትን ያውቃል፤ ደግሞም የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ከዓመፅ ይራቅ የሚለው ማኅተም ያለበት የተደላደለ የእግዚአብሔር መሠረት ቆሞአል" (2ቆሮ 2፥19)::

ሰዎች ሁሉ ሊሄዱ ይችላሉ፤ ፊልጎስና ሄርሞጌኔስ፣ ሄሜኔዎስና ፊልጦስ፣ እንዲሁም እስያ ሁሉ፣ ለጌታ ታማኝ ያልሆኑ ሆነው ሊገኙ ይችላሉ፤ አንድ በአንድ ታማኝነታቸውን ሲያጒድሉም ዙሪያችንን ማየት እንጀምርና ማን ነው የሚታመነው? ብለን ልንደነቅ እንችላለን:: ይሁን እንጂ፣ *ጌታ ለእርሱ የሆኑትን ያውቃል፡-* በዚህ እውነተኛ መሠረት ላይ የተቀረጸውም ያ የመጀመሪያው ማኅተም ነው:: እኛ ተሳስተን ይሆናል፤ እግዚአብሔር ግን ከቶ የሚሳሳት አይደለም:: እኛ በተሳሳተ መንገድ እንመዝን ይሆናል በርሱ ፊት መናዘዝ ያስፈልገናል:: እርሱ ግን ልብን ሁሉ ያያል:: እግዚአብሔር በምሕረት ስለ ተጠቀመባቸው ሰዎች ከልክ በላይ እንገምታለን፤ ነገር ግን እኛንም ተጠቅሞብናል፤ ሆኖም የእርሱ ምሕረት እንደሚያስፈልገን እግዚአብሔር ያውቃል! የሰውን ባሕርይ እናውቃለን ብለን ከማሰብ እንጠንቀቅ:: ያ ዕውቀት ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነው:: ሰዎች ተስፋ ሊያስቈርጡ ይችላሉ፤ ሆኖም ሁላችንስ በአንድ አጋጣሚ ጌታን ተስፋ አላስቈረጥነውምን?

ስለዚህ "በንጹሕ ልብ ጌታን በሚጠሩት ሁሉ" ላይ ትዕዛዝ የሆነ፣ በዚህ ማኅተም ወይም ጽሑፍ ላይ ሁለተኛ ነገር አለ:: የሚጠሩ ሁሉ ጽድቅ ካልሆነ ነገር ሁሉ መለየት አለባቸው:: የማይናወጠው የእግዚአብሔር መሠረት ይህን ይነግረናል:: በዙሪያችን መንፈሳዊ ጥሰት ስናይ ራሳችንን ማየት አለብን:: የጌታ የሆኑት ሁሉ መቀደስ አለባቸውና ቀጥለው ያሉት ቍጥሮች ይህን ያብራራሉ:: ከተሟላ ዕቃው፣ የወርቅና የብር ዕቃዎች ካሉት፣ እንዲሁም ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሚውሉ እንጨትና መሬት ስላሉት ያጌጠ ታላቅ ቤት ይናገራሉ:: ሰዎች ከእነዚህ ዕቃዎች ጋር ተመሳስለዋል፤ ሆኖም በዚያ ላለው የከብር ቦታ ራሳቸውን ብቁ እንዲያደርጉ ተመከረዋል::

ከዕቃዎቹ ጋር እንዲያከብር ወይም እንዲያዋርድ የታለመው ይህ "ታላቅ ቤት" ምንድን ነው? ከእነዚህስ ቃሎች በስተጀርባ በአንድምታ መልክ የተመለከቱት ግብረገባዊ ጥራቶች ምንድን ናቸው? በ፲ጢሞቴዎስ ላይ የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤት ናት (3፥15)፤ ይሁን እንጂ፣ ከዚህ ላይ ጳውሎስ በእይታ ውስጥ ያስገባው ያን ሳይሆን የክርስትናን ውጫዊ ምስክርነት እንደሆነ አምናለሁ:: "የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን" ራሷ ከቶ ፍርስራሽ ልትሆን አትችልም፤ ከድብልቅ ነገሮቿ ጋር ወደዚህ "ታላቅ ቤት" ልታሽቆለቁል ከቶ አትችልም:: ሆኖም የሚያሳዝን ነው፤ የቤተ ክርስቲያን ውጫዊ ምስክርነት በአንድ በተወሰነ ወቅት ፍርስራሽ ብቻ ሊሆን ይችላል::

እንግዲህ በእነዚህ ዕቃዎች መካከል ልዩነት የሚያደርገው ምንድን ነው? ተግባራቸው ሳይሆን ተለይቶ የተመለከተው የዕቃዎቹ ዐይነት ብቻ መሆኑን ወዲያውኑ ልብ እንላለን:: በግልጽ እንደሚታየው ቀደም ሲል ያየነውን የቤቱን ግንባታ ልብ በማለት፣ ከዚህም እንደ ገና ዋጋ ያለው አንጻራዊ ጠቃሚነት ሳይሆን የዕቃዎቹ ጥራት ነው:: ከተግባር አንጻር ከወርቅና ከብር የተሠሩ ዕቃዎች፣ ከእንጨት የቤት ዕቃዎች ወይም ከሸክላ ዕቃዎች ያነሰ ጠቃሚነት አላቸው፤ ይሁን እንጂ ከዚህ ላይ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚወያየው ጥቅም ላይ ስለሚውሉበት ጉዳይ አይደለም፤ ለእርሱ ባላቸው የዘለቄታ ፋይዳ እየገመገመ ነው እንጂ:: ነገሮች እያሽቆለቆሉ በመጡበት ዘመን፣ ዕቃው በባሕርይው ካለው ዋጋ ባሻገር እግዚአብሔር ያያል፤ እጅግ አነስተኛ ሚዛን ያለው ወርቅም ሙሉውን አዳራሽ ከሞሉት የእንጨት መቀመጫዎች ጋር እኩል ፋይዳ ሊኖረው ይችላል! በመንፈሳዊ አነጋገር፣ ሁለት የተለያዩ ሰዎች አንድ ዐይነት ቃላትን ሊናገሩ ይችላሉ፤ ኃይሉ ያለው ግን ከሚናገሩት ላይ ሳይሆን ከማንነታቸው ላይ ነው:: በለዓምና ኢሳይያስ ሁለቱም ስለ እግዚአብሔር





መንግሥት ተናግረዋል፤ ይሁን እንጂ በግል ፍላጐት ረገድ ከሁለቱ ወደ ማንኛቸው መመለስ እንዳለብን በደንብ እናውቃለን::

መለኪያዎች እየወረዱ ባሉበት ሁኔታ ዋጋ የምንሰጠው ለየትኛው ነው? እንጨትና ዐፈር ለሆነው ለሰው ጮሌነትና ለዓለም ሀብት ነው? ወይስ ወርቅና ብር በመሆን ከመለኮት ለሆነው በክርስቶስም በኩል በመስቀሉ እውን ለሆነው ቤዛነት? ዛሬ በክርስትና ውስጥ ብዙ ነገሮች በጣም ርካሽ ሆነዋል፤ ይሁን እንጂ ለከበረ መንፈሳዊ ነገር አቋራጭ ነገር የለም:: ስብከት፣ ጸሎት፣ ምስክርነት እነዚህ አስቸጋሪ ላይመስሉ ይችላሉ፤ ነገር ግን ዋጋ ያላቸው እንዲሆኑ በዓመታትና በደም እና እግዚአብሔር በሚሠራው ሥነ ሥርዐት (ተግሣጽ) ውድ ነገሮች ይሆናሉ:: "የከብር ዕቃ" የሆነው ሰው መንፈስ ቅዱስ ያስተምረው ዘንድ እርሱን የጠበቀው ሰው ነው፤ እንዲሁም የማያውቀውን ነገር አላውቅም ለማለት የማያፍር ሰው ነው:: የነገሮች እውነተኛ ባሕርይ የሚፈተንበት ቀን ይመጣልና:: በመለያየትና ግራ በተጋባበት ወቅት የሚሰበከው ስብከት፣ ሰዎች በስብከቱ በኩል እግዚአብሔርን እስከላዩበት ድረስ ብዙ ፋይዳ አይኖረውም:: በእንደዚህ ዐይነት ወቅት ሰውዬው በሚናገረው አማካይነት በእግዚአብሔር መንፈስ ተይዞ እንደ ነበር ሊናገሩ ይችላሉ:: እርሱን በጥልቅ ያልነካው ነገር በዚያ ዕለት ሌሎችን ለመንካት ያለው ኃይል አነስተኛ ነው::

"ዕቃ" ሲባል ለአንድ ነገር መበጀትን ስለሚያመለክት፣ የዕቃዎችን ዕጣ ፈንታ ለእግዚአብሔር እንድንተውና ከሁሉም በላይ ስለ ጥራታቸው ግድ እንድንሰኝ 2ጢሞቴዎስ ሐሳብ ይሰጣል:: "እንግዲህ ማንም ራሱን ከእነዚህ ቢያነጻ፣ ለከብር የሚሆን፣ የተቀደሰም፣ ለጌታውም የሚጠቅም፣ ለበጎም ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ዕቃ ይሆናል::"

## ባሪያው ዩሐንስ

ይህ በስፋት ወደ ተወደደው ደቀ መዝሙር ያመጣናል:: የተጻፈበትን ጊዜ አስመልክቶ የእርሱ ጽሑፍ በአጠቃላይ የሚመጣው ከጳውሎስ መልእክቶች በኋላ ነው፤ ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ ለዐዲስ ኪዳን መገለጥ የእርሱ የተለየ አስተዋጽኦ፣ ከዚህ ቀደም እንዳልነው፣ በመመለስ ላይ አጽንዖት የሰጠበት ጉዳይ ነው:: የውስጥ ሕይወት ችላ ተብሎ ቤተ ክርስቲያን ውጫዊ በሆነ ነገር በተወሰደችበት ጊዜ ዮሐንስ ስለ እውነተኛ መለኮታዊ ጥራቶች ለሰዎች ሊያሳስባቸው ወደ ትዕይንቱ መጣ:: ይህ ቀደም ሲል እንዳመለከትነው፣ ኢየሱስ እርሱንና ወንድሙን ያዕቆብን "በታንኳ ላይ መረቦቻቸውን

በሚጠግኑበት” ጊዜ እንዳገኛቸው በተነገረበት ታሪክ ገና ከጅምሩ ለእኛ ተገልጦ ነበር-መረባቸውን የጠገኑት በትናንቱ ሌሊት ተጐድቶ ስለ ነበር ነው።

ርግጥ ነው ዮሐንስ ከጴጥሮስ ያነሰ “ዓሣ አጥማጅ” አልነበረም፤ እንደዚሁም በተሰማራበት መስክ ከጳውሎስ ያነሰ “ግንበኛ” አልነበረም። በሐዋርያት ሥራ መጀመሪያ ላይ በመጀመሪያው ደረጃ ላይ እያሉ በስብከቱና በኅብረቱ ረገድ ሙሉ በሙሉ ሲካፈል እናገኘዋለን፤ እንደ ጳውሎስም በሥልጣን “ለቤተ ክርስቲያን” (3ዮሐ 9) መጻፍ ይችላል። ይሁን እንጂ በዚህ በዐዲስ ኪዳን ዐውድ ውስጥ በአጠቃላይ ሲታይ ጉልሕ ሆኖ የሚታየው የዮሐንስ ጽሑፎች ገጽታ፣ የነገሮች ጥንተ ነገር ወይም መለኮታዊ ዕቅድ ምን እንደ ነበር ማስታወስ ሆኖ እናገኘዋለን።

ሁላችንም እንደምናውቀው፣ የዮሐንስ ወንጌል ከአራቱ ወንጌላት መካከል የመጨረሻው ነው። መልእክቶቹም የመጨረሻ መልእክቶች ናቸው፤ ራእዩም በእግዚአብሔር ሙሉ መጽሐፍ ውስጥ መጨረሻ ላይ እንዲቀመጥ ሆኖአል። ጽሑፎቹ ሁሉ “የመጨረሻ” ናቸው ማለት ይቻላል። በዮሐንስ ወንጌል ላይ የዚህን ሐቅ ነጸብራቅ በየትኛውም ቦታ ታገኛላችሁ። ለምሳሌ ዮሐንስ፣ በማርቆስ ወንጌል ላይ ተጽፎ ከምናገኘው በተለየ መልኩ፣ ስለ ጌታ ሥራ የሚገልጸው በትንሹ ነው። በማቴዎስ ወንጌል ላይ በተራራው ስብከት ትኩረት የተሰጣቸው የጌታ ትእዛዛትም በዮሐንስ ወንጌል ላይ ትኩረት ተሰጥቶአቸው አናገኛቸውም። አንድ ሰው ኮትህን ቢወስድብህ፣ ወይም ጎረቤትህ አንድ ወይም ሁለት ምዕራፍ ዐብረኸው እንድትሄድ ቢያስገድድህ፣ ምን ማድረግ እንዳለብህ እርሱ አይጨነቅም። ያ አሁን የእርሱ ቀዳሚ ትኩረቱ አይደለም። የእርሱ ሸክም የዘላለሙና ከዚያ ጋር ያለህ ግንኙነት ነው። ወደዚያ እውነት ተመልሰህ ብትሄድ ሁሉም ነገር ተከትሎ ይመጣል ማለቱ ነው። በዚህ ረገድ ከሉቃስም የተለየ ነው። ወደ ኋላ ወደ አዳም በቀጥታ የሚወስዱ ቢሆኑም እንኳ፣ ውጫዊና ጊዜያዊ በሆኑ በእነዚያ ነገሮች ማለትም በዓመታትና በትውልድ ሐረግ ላይ ትኩረት አያደርግም። ጠቅላላ ሸክሙ ቀጥሎ ያለው ነው፤ ከእነዚህ ነገሮች በስተጀርባ የሚገኘውን *ሕይወት* ማግኘት አለብን። ከዚህ ላይ አሁን ሁሉም ነገር ያልታደሰ ነው። “ከሰማይ ወደ ወረደው” ወደ ሕይወት ተመለሱ፤ ወደዚያ ተመልሳችሁ ስትሄዱ፣ ጴጥሮስ እንደዚሁም ጳውሎስ የቆሙለት ነገር ሁሉ ተጠብቆ ተገኙታላችሁ። እንደ እውነቱ ከሆነ ዮሐንስ የሚሰጠው ዐዲስ ነገር የለም። ወደ ሩቅ ቦታ አይወስደንም፤ ሩቅ የሆነውን መዳረሻ እግዚአብሔር ዳሰታልና። ለዮሐንስ በዐደራ የተሰጠው ራእይ





ዐላማ፣ ሕይወት የሆነውንና የተነካውን ጌታ በዐዲስ እይታ እንዲያዩት አድርጎ ሰዎችን ወደ መጀመሪያው ዐላማ መልሶ ማምጣት ነው።

የዮሐንስ ወንጌል ከዳር እስከ ዳር ስታነቡ፣ የመጀመሪያው ምዕራፍ ቀጥሎ ለሚመጡት ምዕራፎች ሁሉ ቊልፍ በመሆኑ ሐቅ ላይ ትማረካላችሁ። በምዕራፍ አንድ ላይ ሁለቱ ምንጮች ጸጋና እውነት በክርስቶስ ሲፈሱ ታስተውላላችሁ። “ሕግ በሙሴ ተሰጥቶ ነበር፤ ጸጋና እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ” (1፥17)። በወንጌሉ ከዳር እስከ ዳር፣ በአንድ በኩል በእውነት ላይ በሌላም በኩል ደግሞ በጸጋ ላይ፣ ተመሳሳይ የሆኑ ጥንድ አጽንዖት ታገኛላችሁ። እውነት ምንጊዜም የሚጠይቃቸው ነገሮች ይኖራሉ፤ ጸጋም እነዚህን ጥያቄዎች ለማሟላት ምንጊዜም በዚያ ይገኛል። በዝሙት ስለ ተያዘችው ሴት በምዕራፍ 8 ላይ በሚገኘው እውነት ሲያበራ ይታያል። ኢየሱስ “ምንም አይደለም፤ ኀጢአት አልሠራሽም” አላላትም። ለአይሁድ፣ የሠራችው ነገር ይህን ያህል የከፋ አይደለም አላለም፤ እርሷ ስለ ፈጸመችው በደል ግድ አልተሰኙሁምም አላላቸውም። እንዲህ አላላም፤ ግን ጌታ፣ “ከእናንተ ኀጢአት የሌለበት አስቀድሞ በድንጋይ ይውገራት” አላቸው (8፥7)። እውነቱ ጉልሕ ሆኖ ይታይ ነበር፤ “ኀጢአት ሠርታለች፤ በሕጉ መሠረትም በድንጋይ መወገር አለባት” ይሁን እንጂ ጸጋም በዚያ ነበር፤ ሁሉም ከሄደ በኋላ ወደ እርሷ ቀና ብሎ፣ “እኔም አልፈርድብሽም” አላት። ከዳር እስከ ዳር ባለው በዮሐንስ ወንጌል ላይ እውነትን በዚህ ዐይነት መንገድ አቻ ለአቻ ሆኖ ታገኛላችሁ።

ነገር ግን ወደ ዮሐንስ መልእክቶች ስትመለሱ፣ ከዚህ ተጨማሪ የሆነ ነገር ታገኛላችሁ። ስለ ጸጋ እንዲሁም ስለ እውነት ቀደም ሲል ከነበረው አነስ ባለ መልኩ ትሰማላችሁ፤ እነዚህ መልእክቶች የተጻፉት በኋለኛው ዘመን በመሆኑ፣ መሠረታዊ የሆነው ዳግመኛ መመለሱ አስፈላጊ ነበር። ስለዚህ ዮሐንስ አሁንም ወደ ኋላ ሲያመለክት ታገኛላችሁ። እግዚአብሔር ብርሃን ነው (1ዮሐ 1፥5)። “እግዚአብሔር ፍቅር ነው” (1ዮሐ 4፥8)። በሌላ በኩል ግን፣ በወንጌሉ ላይ፣ ክርስቶስ ከአብ ዘንድ በመምጣት በሰዎች መካከል ጸጋና እውነት ሆኖ ተገልጦ ነበር፤ ሆኖም እዚህ በመልእክቶች ላይ ክርስቶስ ከአብ ጋር ባለው ሕልውና ብርሃንና ፍቅር ሆኖ ለሰዎች ተገልጦአል። በወንጌል ላይ እውነት የነበረው፣ በመልእክቶች ላይ ፍቅር ሆነ። በወንጌል ላይ እውነት የነበረው፣ በመልእክቶቹ ላይ ብርሃን ሆነ። ይህ ለምን ሆነ? ምክንያቱም በእግዚአብሔር ዘንድ ብርሃን የነበረው ወደ ሰዎች ሲተላለፍ እውነት ሆነ፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ፍቅር የነበረው፣ ወደ ሰዎች እንዲመጣ ሲሆን ጸጋ ሆነ። ፍቅርም ወደ እግዚአብሔር

ተመልሶ ሄደ፤ ጸጋ ግን ከዚህ ቀረ:: ከእግዚአብሔር የሆነው ነገር ሁሉ ብርሃንና ፍቅር ነው፤ ነገር ግን ወደ ሰው ሲመጣ እውነትና ጸጋ ይሆናል:: ጸጋ አላግባብ ሊውል እውነትም በአግባቡ ላይያዝ ምንጊዜም ይችላል፤ ሰዎች እዚህን ነገሮች አላገባብ አውሏዋቸዋል:: ይሁን እንጂ፤ እግዚአብሔር ብርሃን ነው፤ እግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ ወደዚያ መውጣት ያንንም መንካት አትችሉም፤ ያ አላግባብ ከመያዝ በላይ ነው:: ስለዚህ የዮሐንስ ዘዴ እኛን ወደ ዙፋኑ መልሶ መውሰድ ነው፤ ዐዲስ ነገር ለእኛ መስጠት ሳይሆን እኛን ከዋናው (ኦርጅናል) ጋር ፊት ለፊት ማጋጠም ነው:: የጠፋውን መልሰን የምናገኘውና የምንጠብቀው ወደ ምንጩ ተመልሰን በመሄድ ነው::

ነገር ግን ከሙሉው መጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻ፣ በአንዳንድ ሁኔታም እጅግ ዋና ወደ ሆነው፣ ወደ ዮሐንስ ራእይ ስንመጣ፣ ይህ የሐዋርያው መርሕ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ሆኖ እናያለን፤ ይኸውም አጽንዖቱ "እውነተኛ በሆነው በርሱ" በጌታ ኢየሱስ ላይ ሆኖ የምናገኘው ይመስለኛል (ራእ 3፥7):: ማንኛችንም ብንሆን ሉዐላዊ መመለስን የሚወክል መሆኑን ሳንገነዘብ መጽሐፉን ማንበብ የምንችል አይመስለኝም:: በሙሉ የአራት ዘፍጥረት ሙሉ ተገላቢጦሽ መሆኑን ያመለክታል:: በመጀመሪያ በነገሮች ሁሉ ላይ ገብቶ የነበረው አለመሳካትና መፈራረስ ሁሉ አሁን ተሸሮአል፤ ጠፍቶ የነበረው ነገር ሁሉ አሁን ተመልሶ ተገኝቶአል፤ እዚያ ላይ ተነሥቶ የነበረው ጥያቄ ሁሉ እዚህ ላይ ተመልሶአል::

በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ ላይ እባብን አያለሁ:: የዚህ መጨረሻው ምን ይሆን? ርግማንን አያለሁ:: የዚህ መጨረሻው ምን ይሆን? ሞትንና ኀጢአትን አያለሁ:: ያ የት ላይ ያከትማል? አንድ ሰው ከሕይወት ዛፍ ተከልክሎ አያለሁ:: የእነዚህ ነገሮች ጉዳይ ምን ይሆናል? ጅማሮአቸውን አያለሁ፤ መጨረሻቸው ግን ምን ይሆን? የእኔስ መጨረሻ ምን ይሆን? እግዚአብሔር በጸጋ ከእኔ ጋር ጅማሮ አድርጎአል፤ ሆኖም ድነት በአሁኑ ሕይወት ብቻ ቢያከትምስ? የዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ ዐላማ ኢየሱስ ምንጊዜም ዘላለማዊ፣ አልፋና ዖሜጋ መሆኑን ለእኔ በማሳወቅ እነዚህን ጥያቄዎች መመለስ ነው::

ራእይ የተገለጠው የኢየሱስ ክርስቶስ፣ *አቡቀለምሲስ* ነውና:: መጋረጃውን ገለጥ አድርጎ የእርሱን ማንነት ይገልጣል:: ዐላማው የክርስቶስ ተቃዋሚን፣ ተሐድሶን ያገኛል የተባለውን የሮምን ግዛት፣ ከፍተኛ ሐሤትን፣ ሚሊኒየምን፣ ወይም የሰይጣንን የመጨረሻ ዕጣ ፈንታ አስመልክቶ ስለ እነዚህ ስለሚመጡት ነገሮች ለእኛ ብርሃን መስጠት አይደለም:: ለሕመማችን ሁሉ የዮሐንስ





መፍትሔ የብዙ ማኅተሞችና መለከቶች ጉዳይ አይደለም፤ ወይም ሐሤቱ "ከፊል" ወይም "ሙሉ" ስለ መሆኑ አይደለም፤ ግን ክርስቶስን ራሱን በሙላት በመግለጥ መንፈሳዊ ፍላጎታችንን እንድናረካ ነው፣ ያም እርሱን እናውቀው ዘንድ ነው::

ርግጥ ነው፣ የዮሐንስ ራእይ፣ ከሕልማችን በላይ በሆነ መንገድ እንኳ፣ ጥያቄዎቻችንን ለራሳችን ይመልሳል:: ዮሐንስ በመጨረሻ ላይ የሚያቀርብልን በመጀመሪያ ላይ ካጣነው በላይ ነውና:: እግዚአብሔር በአትክልት ቦታ ጀመረና፤ በከተማ ይደመድማል:: በዘፍጥረት ላይ የፈጠረውን (የሠራውን) ሰው ኀበኘው፤ በዮሐንስ ራእይ ማደሪያው፣ እንዲያውም ዙፋኑ በሰዎች መካከል ነው:: በጳውሎስ መልእክቶች ላይ ቤተ ክርስቲያን የነበረችው በዮሐንስ ራእይ ላይ ቅድስቲቱ ከተማ ሆናለች:: ሆኖም ይህ በመለኮታዊ ዕቅድ ውስጥ ምን ጊዜም እንደዚሁ ነበር:: በመጀመሪያ እግዚአብሔር ለመሥራት የተዘጋጀበትን፣ በርግጥ ይፈጽመዋል፤ ያን የተዘጋጀበትን ነገር በሐሳቡ የፈጸመው መሆኑንም የዮሐንስ ራእይ ያረጋግጥልናል:: ቀደም ሲል እንዳደረገው፣ ዮሐንስ በመሠረቱ ዐዲስ ነገር ስለማያቀርብልን፣ እግዚአብሔር ያቀደውን የሚፈጽመው መሆኑን ብቻ ያሳየናል::

እንደ ገና እናገራለሁ፤ ይህ ዮሐንስ የሚሠራው ሁሉ፣ ወደ መለኮታዊ ጅማሮ (ዋና ጉዳይ) እኛን መልሶ ለማምጣት ነው:: የዚህ ዓለም ዕጣ ፈንታ ምንድን ነው? የቤተ ክርስቲያን ግጭት ውጤት ምን ይሆናል? የእኔስ መጨረሻ ምን ይሆናል? ሁሉም ነገር በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ መልስና ፍጻሜ ያለው መሆኑን ዮሐንስ ያረጋግጣል:: ክርስቶስ ጅማሮዬ ነውን? እርሱ መጨረሻዬም ነው:: እርሱ አልፋዬ ነውን? እርሱ ዖሜጋዬም ነው:: ክርስቶስ ለጥያቄዎቼ ሁሉ መልስ ነው:: በመጀመሪያ ስለ እርሱ ግልጽ የሆነ ነገር ካለኝ፣ ስለሚመጡት ሁኔታዎች ዐውቃለሁ:: ስለ እነርሱ ያለውን አመክንዮ እና ስለ እነርሱ ያለውንም አግባብነት ማወቅ ያለብኝን ሁሉ ዐውቃለሁ:: ይሁን እንጂ ይህ የማይታለፍ መለኮታዊ ቅደም ተከተል ነው:: ማንም የመጀመሪያውን የራሱን የጌታን ራእይ ካላየ፣ ዮሐንስ ያሰፈራቸውን ተከታታይ ራእዮች ለማጥናት ብቁ አይሆንም:: ያ ራእይም እርሱ ማን እንደ ሆነ ይነግረናል፤ የተነሣው፣ እና ድል አድራጊው የነገሥታት ንጉሥ መሆኑንና ተከትለው የመጡትም ሁኔታዎች እርሱ እንደዚያ የመሆኑ ውጤት መሆናቸውን ይነግረናል::

ይህ ለዮሐንስ በግሉ እውነት ነበር:: በኢየሱስ ዕቅፍ የነበረው የተወደደው ደቀመዝሙር እንኳ፣ ትቢያ ላይ የደባለቀው የዘላለሙ ጌታው ራእይ

ያስፈልገው ነበር:: "የሚመጡት ነገሮች" ሲገለጡለት የቻሉት ከዚያ በኋላ ብቻ ነበር:: የመጀመሪያው መታየት ለሌሎቹ መታየቶች ሁሉ መሠረታዊ ነው:: በእይታ ውስጥ ያለው መንግሥት ነውና፤ ናቸው የመንግሥቱ ጠላቶች በሆኑት ሁሉ ላይ ጦርነት የሚያውጁ ንጉሡና ሰራዊቱ ነገር ግን የትንቢት ባለሙያዎች የሆኑ አይደሉም:: የሚመጡት ሁኔታዎች የተገለጡት ለሥራ ፈት ግምቶች ምግብ ለማቅረብ አይደለም፤ ግባቸው ጠላትን ከሥልጣን ማውረድና የክርስቶስን መላለማዊ ግዛት እውን ማድረግ እንጂ::

ስለዚህ እግዚአብሔር በወንጌላቱ ላይ ስለ ልጁ ያላየነውን ገጽታ በዮሐንስ ራእይ ላይ ያሳየናል:: በወንጌላቱ ላይ አዳኝ ሆኖ እናየዋለን፣ በዮሐንስ ራእይ ላይ ግን ንጉሥ ሆኖ እናየዋለን፤ በዮሐንስ ወንጌል ላይ አልፋ ሆኖ እናየዋለን፤ በዮሐንስ ራእይ ላይ ደግሞ ዖሜጋ ሆኖ እናየዋለን:: የመጀመሪያው ፍቅሩን ያሳያል፤ ሌላኛው ግርማውን ያሳያል:: በላይኛው ክፍል ኢየሱስ፣ ለአገልግሎት፣ ወገቡን ይታጠቃል፤ በፊጥሞ ለጦርነት ወገቡን ሲታጠቅ ይታያል:: በወንጌላቱ ትሑት ዐይኖቹ ጴጥሮስን አቀለጡት፤ በዮሐንስ ራእይ ላይ እንደ የእሳት ትንታጎች ናቸው:: በወንጌላቱ ላይ በጎቹን በሰላም በመጥራት ድምፁ፣ ትሑት ነበር፣ የጸጋ ቃሎችም ከአንደበቱ ወጡ፤ በዩሐንስ ራእይ ላይ ድምፁ እንደ ብዙ ውኆች ድምጽ አስፈሪ ነበር፤ ከአፉም ጠላቶቹን ለሞት የሚያደርስ ባለሁለት ስለት ሰይፍ ወጣ::

ኢየሱስን እንደ የእግዚአብሔር በግና እንደ የዓለም አዳኝ አድርጎ ማወቅ በቂ አይደለም፤ እንደ የእግዚአብሔር ክርስቶስ፣ እንደ የእግዚአብሔር ንጉሥ፣ እንደ የእግዚአብሔር ዳኛ አድርገንም ማወቅ አለብን:: እንደ አዳኝ ሆኖ ስናየው፣ "እንዴት የደስ ደስ ያለው (ፍቅር) ነው!" እንላለን፤ እናም በደረቱ ላይ እንደገፋለን:: እንደ ንጉሠ ነገሥት ሆኖ ስናየው፣ "እንዴት አስፈሪ ነው!" እንላለን፣ እናም በእግሮቹ ሥር እንዘረራለን:: አንዱ በምስጋና ነው፤ ሌላኛው ደግሞ በአምልኮ ነው:: አንድ ሰው፣ አሁን እርሱን እንደ ንጉሥ ሆኖ ማየት "ሌላ" ክርስቶስ ማየት ነው፤ "ሌላ" ድነትንም ተመክሮ ማድረግ ነው ሊል ይችላል:: አሁን የእግዚአብሔር ዐላማዎች እንቅፋት ሊያጋጥማቸው የሚችል ቢሆንም እንኳ፣ በመጨረሻ ከቶ ሊጨናገፉ የማይችሉ ለመሆናቸው እርሱ እነሆ ታማኝና እውነተኛው ምስክር መለኮታዊ ዋስትናም ሆኖ እናየዋለን::





## እርሱ እውነተኛ የሆነ

አቡቀለምሲሳዊ የሆነውን ስናጠና፣ የምናነበውን ከልክ በላይ መንፈሳዊ አድርግን እንዳናነብ በምናደርገው ጥረት ላይ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን:: የዮሐንስ ዐዲስ ሰማይና ዐዲስ ምድር ምናባዊ ሳይሆኑ እውናዊ ናቸው፤ ዐዲሲቱ ኢየሩሳሌምም፣ የተነሣው ጌታ በእውነት እማናዊ እንደሆነ ሁሉ እማናዊ ናት:: መለኮታዊ ነገሮችን መንፈሳዊ (ረቂቅ) አድርጎ ማየት ነባራዊ ነገር የሌላቸው ሰዎች ተስፋ ቢስ የሆነ ማምለጫ መንገድ ነው:: ብዙ ተወዳጅ ወገኖች መንፈሳዊና ትንቢታዊ እውነት ብቻ ያከማቻሉ፤ በእነዚህም ለራሳቸው ነባራዊ ያልሆነ ዓለም እንዳይገነቡ እሠጋለሁ:: ይህን ማድረግ ከእውነታ ማምለጥ ነው፣ ይኸውም ቀደም ሲል እንዳየነው፣ ዛሬም በኤፌሶን መንፈሳዊ ድባብ ለመኖር ዝግጁ እንደ ሆኑት ግን ከቆሮንቶስ ተግባራዊ ተግዳሮት ለማምለጥ ጥረት እንደሚያደርጉት መሆን ነው:: ነገር ግን ልብ በሉ፤ ይህ በሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ላይ ድንገት እንደ ደረሰው አሳሳች እምነት፣ ውሸትን ያምኑ ዘንድ እንዳስቻላቸው ነው::

የመንፈሳዊ ኅብለት ምልክት ክርስቶስ ለእኛ አማናዊ በመሆኑ መለኮታዊ ነገሮችም ሁልጊዜ አማናዊ ሆነው መገኘታቸው ነው:: እርሱን አማናዊ ሕይወት፣ አማናዊ ቅድስና-እንዲያውም እንደ "እውነት" ሆኖ እናየዋን፤ ከዚህ ላይ፣ "እውነትን" የምጠቀመው ቀደም ሲል "ትንቢታዊ እውነት" ብዬ ከተጠቀምኩበት በተለየ መልኩ ነው:: ብዙዎች እውነትንና አስተምህሮን ያምታታሉ፤ ሁለቱ ግን አንድ አይደሉም:: አስተምህሮ ማለት ስለ ዘላለማዊው እውነት በምድር ላይ የተነገረው ማለት ነው:: በቻይንኛ እውነትን የሚወክለው ቃል ቸን- ሊ (ይህም ከሞላ ጐደል 'አማናዊ- አስተምህሮ') ማለት ሲሆን የግሪኩ ትርጉም ግን ያለ 'ሊ' 'ቸን' ሲሆን "አስተምህሮ" ሳይኖርበት "እውነታ" ማለት ነው:: "እውነትንም ታውቃላችሁ" (ዮሐንስ 8፥32) ያለው ኢየሱስ እውነት የሆነውን ነገር ሁሉ አካቶ ይዞአል (ራእ 3፥7፤ ከዮሐ 5፥20 ጋር ያነጻ)፤ እርሱን ማወቅ ያለብንም ከዚህ የተነሣ ነው::

"... እውነትም በኢየሱስ እንዳለ ሁሉ" (ኤፌ. 4፥21)፤ ጸጋም "በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ" (ዮሐንስ 1፥17):: ጸጋውን እንቀበላለን፤ ነገር ግን የእርሱን እውነት እናውቃለን? ራሱን በመስቀል ላይ በሰጠ ጊዜ ጸጋ በታሪካዊ ድርጊት ወደ እኛ መጣ፤ እውነት በስብከቱ እንዲሁ የተገለጸ ብቻ ሳይሆን፣ እውነት በርግጥ ከእርሱ ማንነትና ሥራ ጋር በጥብቅ የተሳሰረ ነው:: ስለዚህ ጸጋ አሁን ወደ እኛ የሚደርስ ከሆነ፣ በዚያ በተፈጸመው ሥራ በእምነት በኩል፣ ከእርሱ

"ይህማ በጣም አስቸጋሪ ነው!" ብላችሁ ትደነቃላችሁ:: ያለ ጥርጥር ቤተ ክርስቲያን መንጻት ያስፈልጋታል! እስቲ ወደ ኤፌሶን ምዕራፍ 5 ተመለሱና ቤተ ክርስቲያን በቃሉ ውሃ በመታጠብ የነጻች መሆኗን እንዴት እንደምትገልጹልኝ ንገሩኝ:: መልካም አካሄድ ነው፤ አስቀድሞ ግን ዐውዱን አስተውሉ:: ባልና ሚስት እንዴት መተባበር እንዳለባቸው ይነግረናል:: ከባል የሚፈለገው ፍቅር ነው፤ ከሚስት ደግሞ መገዛት ነው:: ጉዳዩ እንዴት ባል ወይም እንዴት ሚስት መሆን እንደሚገባ አይደለም፣ ግን ባል ወይም ሚስት ተሁኖ እንዴት መኖር እንዳለባችሁ ነው:: ባል ትሆን ዘንድ መውደድ አለብህ፤ ሚስት ትሆኚ ዘንድ መታዘዝ አለብሽ ሳይሆን ባል እንደመሆንህ መጠን መውደድ አለብህ፤ ሚስት እንደ መሆንሽ መጠን መታዘዝ አለብሽ ነው:: በመታየት ላይ ያለው ሙሉው ሐሳብ፣ ለመሆን ማከናወን ሳይሆን ሆኖ ከመገኘት የተነሣ ማከናወን ነው::

እንግዲህ ተመሳሳይ መርሕ ቤተ ክርስቲያንን አይመለከትምን? እነዚያ የተጠሩት ቤተ ክርስቲያን እንዲሆኑ አልታጠቡም፤ ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን በመሆናቸው ታጥበዋል:: ቀደም ሲል ጳውሎስ ከዚህ ላይ እየተመለከተ ያለው ከኀጢአት ጉዳይ ባሻገር ነው በማለት ሐሳብ ያቀረብሁት ከዚህ የተነሣ ነው:: የእጥበት ዐላማው፣ በዮሐንስ 13፥10 ላይ በጌታ ቃል ላይ በአንድምታ እንደ ተመለከተው፣ የዓለምን ድብዛዜና አቧራ በማስወገድ መታደስ ሊሆን ይችላል:: ከዚህ ላይ የታሰበውም ይኸው ይመስለኛል:: ቤተ ክርስቲያን ታጥባችኋል በተባለው መሰረት ታጥባ ነበር (1ቆሮ 6፥11)፣ በእጥበትም አሁን ታድሳ ትገኛለች:: ባል እንደ ባል የሚያከናውነው ባል በመሆኑ ነው፤ ሚስት እንደሚስት የምታከናውነው ሚስት በመሆኗ ነው፤ ቤተ ክርስቲያን የታጠበች የሆነችው የታጠበች በመሆኗ ነው:: ቤተ ክርስቲያን ከብቃት መለኪያው ላይ ደርሳለች፤ ስለዚህ በብቃት መለኪያው ልክ ትኖር ዘንድ እገዛ ተደርጎላታል፤ በአንጻሩ ግን ቤተ ክርስቲያን ያልሆነችው፣ የቱንም ያህል ትታጠብ፣ ከቶ ቤተ ክርስቲያን ልትሆን አትችልም::

ቀደም ባለው ምዕራፍ ላይ እንደ ገለጽነው፣ በቤዛነት ሙሉ ታሪክ በኩል በመሥራት "ያጸደቃቸውንም . . . አከበራቸው" ይላል (ሮሜ 8፥30):: የኤፌሶን መልእክት ሆን ብሎ ከጊዜ ገደብ ውጭ ወዳላለፈውና ወደፊቱ ዘላለም ይጓዛል፤ ዘላለማዊ ሙሉነትንም መነሻው ያደርጋል:: የመጨረሻው እውነታ ምንጊዜም በእግዚአብሔር ፊት ነውና፤ እግዚአብሔር ስለ ቤተ ክርስቲያኑ የሚናገረውም ከዚያ እውነታ አኳያ ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የጊዜ ጉዳይ ለሰው አእምሮ አስቸጋሪ ከሆኑት ነገሮች አንዱ ነው፤ ነገር ግን በቅዱሳኑ ዘንድ ጌታ





ያለውን የርስቱን ክብር ለማወቅ ልቦቻችን በበሩ ጊዜ ከአድማስ ይጠፋል:: እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን የሚያያት ፍጹም ንጹሕና ሙሉ በሙሉ እንከን አልባ ሆና ነው:: ዛሬ በመንግሥተ ሰማይ ላይ የሚገኘውን የመጨረሻ ክብር ማወቅ ማለት በምድር ላይ በዚያ ክብር ኀይል ለመኖር ርግጠኛ የሆነ መንገድ ነው::

## የመንግሥተ ሰማይ ዜጎች

ብዙ ክርስቲያኖች የክርስትናን ውጫዊ ገጽታ ብቻ ማየታቸው የሚያሳዝን ሐቅ ነው፣ ደግሞም እውነተኛ ኪሣራ ነው:: የክርስትናን ውስጣዊ እውነታ ከቶ አላዩም፤ በመሆኑም ዐይነተኛ ገጽታውን ገና አላወቁም:: ዛሬ ብዙ ውጫዊ የሆነው ነገር ከቤተ ክርስቲያን ጋር በመያያዙ፣ የእግዚአብሔር የሆነው በትክክል የቱ እንደ ሆነ ለመለየት አስቸጋሪ መሆኑ የሚያስገርም አይደለም:: ሆኖም ክርስትና እንዲሁ ውጫዊ ሥርዐት አይደለም:: ክርስትና "እውነት" ነው::

እዚህ ላይ የዮሐንስ ወንጌል፣ መንፈስ ቅዱስ የእውነት መንፈስ መሆኑን በማሳየት ይረዳናል፣ ወደ እውነት ሁሉ እንደሚመራንም ያረጋግጥልናል:: ስለዚህ ጉዳይ በመደምደሚያው ምዕራፍ ላይ የምንለው ብዙ ነገር ይኖረናል:: በርግጥም ከዚህ መግለጫ በመነሣት ከመንፈስ ቅዱስ ትምህርትና ዐብሮሆት ውጭ የሚመጣው ነገር ሁሉ ከእውነት ያነሰ ነው ብለን መደምደም እንችላለን:: በሐሳብና በጥናት፣ በዐይን በማየትና በጆሮ በመስማት የምንደርስበት ሁሉ፣ ከዘላለሙ እውነትነት ውጭ ነው፤ በመንፈሳዊ ረገድ እውናዊ የሆነ ጉዳይ አይደለም::

የሰው አእምሮ በመለኮታዊ ነገሮች ላይ እጅግ ጽንፈኛ የሆነውን አመለካከት ገንዘብ አድርጎ ይዞአል:: ለምሳሌ የሮም ቤተ ክርስቲያን ለመለኮታውያን ነገሮች ሥርዐታዊ ወይም ቁሳዊ ገለጻ ለመስጠት ፍላጎ አድርጋለች:: ሰዎች በውሃ ጥምቀት ላይ ትኩረታቸውን አሳርፈዋል፤ ለዳግመኛም መወለድ ምክንያት ነው ብለዋል:: ለጌታ እራት የሚሆኑት በዐይን የሚታዩት ነገሮችም ወደ ክርስቶስ ሥጋና ደም በተአምር ይለወጣሉ ተብለው ውላጤያዊነት (transubstantiation) የሚለውን አስተምህሮ አትርፈውልናል:: እነዚህ ሐሳቦች እንደ ተጠበቁ ሆነውም፣ በዐይን የምትታየዋ የሮም ቤተ ክርስቲያን በእርሷ ቤት እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን እርሷ ብቻ እንደ ሆነች ይታመናል:: በተቃራኒው ደግሞ ምሑራዊው ሰው፣ እንዲህ ያለው አመለካከት እውን ባደረገው አዝልቆተ ቢስነት ግራ በመጋባት፣ የነገሮች ተሐድሶአዊ አመለካከት

ብለን የምንጠራውን ይፋ በማድረግ፣ እነዚህን ለማስወገድ ወይም ምንነታቸውን በማንጠር እነርሱን ያስወግድ ዘንድ ፍለጋ አካሂዶአል:: በጥምቀት ውጫዊ ሥርዐትና በውስጣዊ እውነታው መካከል ልዩነት ያያል:: የጌታ እራት ግባቶች እንደ ምልክቶች ማለትም ውክሎችና ምሳሌዎች መሆናቸውን ያያል:: በውሸት ፈንታ ለእውነት፣ ምድራዊ በሆነው ፈንታ ሰማያዊ ለሆነው፣ "በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቤተ ክርስቲያን" ለተባለውም ጥብቅና በመቆም ለቤተ ክርስቲያን ችግር መፍትሔ ይሰጣል::

እስቲ ልጠይቃችሁ፤ እነዚህ ግራ ቀኝ ጽንፋዊነቶች የቅዱስ መጽሐፍን ግልጽ ሐሳቦች በእውነት ያብራራሉን? ቃሉ ስለ ሐቅ ጽኑ ሐሳቦችን ይናገራል እንጂ ስለ እውነትና ስለ ሐሰት ወይም ስለ ውክል አሊያም ስለ ትእምርት (ምልክት) ምንም አይናገርም:: ጳውሎስ "ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን" ይላል (ሮሜ 6፥4፤ ቆላ 2፥12):: ከክርስቶስ ጋር መሞትና ከእርሱ ጋር መነሣት የሌለበት ጥምቀት ለእርሱ ጥምቀት አይደለም:: ክርስቲያን በአንድ በተወሰነ ቀን ስለ መጠመቁና ከተወሰነ ጊዜ በኋላም ከክርስቶስ ጋር ሞትንና ትንሣኤን ተመክሮው (ገጠመኝ) የሚያደርግ ስለ መሆኑ ሐሳብ የለውም:: እንደዚሁም ጽዋውን አስመልክቶ የጌታችን ቃል ተመሳሳይ ነው:: "ይህ ደሜ ነው"፣ የሚለው በአንድ በኩል ከትእምርትነት ዐልፎ ይጓዛል፣ በሌላ በኩል ግን ከእርሱ ጋር ያያዘው እንድምታ "የወይኑ ፍሬ" የሚለው የውሳጤያዊነትን ሐሳብ የያዘ ነው ተብሎ ከሚታሰበው የተለየ አይደለም:: ደሙ ነው፤ ይሁን እንጂ በጽዋ ውስጥ ያለ ወይን ነው:: ከዚህ ላይ አንድ መለኮታዊ እውነታ እንጂ "ተወካዩ" ወይም "አማናዊ"፣ ምስያ ወይም ኢምስያ የሚባል ነገር የለም::

ለማየት የተቀቡ ዐይኖች ያስፈልጉናል:: ወደ ጥምቀት እውነትና ወደ ጌታ እራት እውነት መምጣት የምንችለው በእውነት መንፈስ ነው:: እንድንመጣ ስንሆን የእነዚህ ነገሮች "አስተምህሮ" መሆኑ ያቆማል፤ ብቻውን የሚቀረው እውነታ ነው:: ለጽንፈኛ ተሐድሶአውያን ሮም እንደምትናገረው ዐይነት አስፈሪ የሚመስሉ ቃሎችን ልንናገር እንችላለን፤ ይሁን እንጂ ሮም ከቶ ያላየቻውን የምናይ እንሆናለን:: የመጨረሻውን ሳዩት፣ አስተምህሮና አምሳያ ለጌታ ራእይ ቦታን ይለቃሉ:: ያለው እውነት የሆነው ብቻ ነው::

ነገር ግን ስለ ቤተ ክርስቲያን እውነታ ለመናገር ስንመጣ፣ ስለ ጥምቀትና ስለ ጌታ እራት እውነታ የተናገርነው ዝቅ ያለ እውነት አይደለም:: በዚህ ዘመን፣ "ቤተ ክርስቲያን" የሚለው ሲነሣ፣ ብዙ ወንጌላውያን ክርስቲያኖች ፍርሃት





ውስጥ ይገባሉ:: ርእሰ-ጉዳዩ ሲነሣ ዳራውን ግልጽ ለማድረግ ብዙ ጥንቃቄ ይደረጋል፤ አለዚያ ብዙ ግራ የሚያጋቡ ነገሮች በተደራስያኑ አእምሮ ሊፈጠር ይችላል:: በእውነተኛዋና በሐሰተኛዋ ቤተ ክርስቲያን መካከል መለያ ለማድረግ ጥንቃቄ ይወሰዳል:: ይሁን እንጂ በጌታ ቃል፣ እና በእግዚአብሔር ሐሳብ ውስጥ፣ እንዲህ ያለ ልዩነት የለም:: ጌታ ስለ ቤተ ክርስቲያን ሲናገር በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ የግርጌ ማስታወሻ አላስቀመጠም:: በውስጣዊና በውጫዊ፣ በአማናዊና በኢአማናዊ መካከል መለያ በማሳየት መንፈሳዊ እውነታን ለመጠበቅ ጥንቃቄ ማድረግ አላስፈለገውም:: በአጥቢያና በመላለም ቤተ ክርስቲያን መካከል እንኳ ጉልሕ የልዩነት መስመር አልዘረጋም:: በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ያለችው "ቤተ ክርስቲያን" ብቻ ናት::

ጉዳዩ እንዲህ ቢሆንም እንኳ፣ የቤተ ክርስቲያን ርእስ ጉዳይ አከራካሪ ጉዳይ ነው ተብሎ በሰፊው ይታሰባል፤ ለወንጌላዊነት አንድነት ሲባልም ጥንቃቄ በተሞላበት መልኩ እንዳይወሳ ይደረጋል:: በእንግሊዝ አገር ተካሂዶ በነበረ ታላቅ ጉባኤ አንድን ሠራተኛ እንዲህ ስል ጠየቅሁት፤ "በዚህ ጉባኤ ላይ ስለ ቤተክርስቲያን ሲወሳ ለምን አንዴም አይሰማም? እርሱም "ይህ ጉባኤ በመንፈሳዊ ሕይወት ጥልቀት ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ነው" በማለት ገለጸ:: ስለዚህ፤ ይህ አመለካከት ወካይ አመለካከት ነው ከተባለ፣ በብዙዎችም ዘንድ ቤተ ክርስቲያንና የክርስቲያን መንፈሳዊ ሕይወት ግንኙነት የላቸውም ተብሎ የሚታሰብ ከሆነ፣ ነገሩ እንዲህ ሆኖ ቢገኝም እንኳ፣ ከእግዚአብሔር ልጆች መንፈሳዊ ሕይወት ጋር ተያያዥነት ያለው ከቤተ ክርስቲያን በቀር ሌላ ነገር የለም::

"ጌታ ሆይ፤ እንዳንተ እንድሆን!" የሚለውን መዝሙር ቤተ ክርስቲያን ሳትሆን ግለሰብ ሊዘምረው ይችላል፤ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ሰማያዊ አካል ናትና:: ይህን ፈልጎ ማግኘት ማለት የራስን የክርስትና ሕይወት ሥር ነቀል በሆነ መልኩ መለወጥ ማለት ነው:: አብዛኞቹ ክርስቲያኖች ሰማያዊ ለሆኑ ነገሮች መታገልና ጥረት ማድረግ ስሕተት ነው ብለው ቢያምኑም እንኳ፣ መታገላቸውና መጣራቸው አልቀረም:: ሰማያዊ ነገሮች በጥረት የሚገኙ ናቸው ተብለው ተምረው ነበር፤ እናም በእነርሱ ቤት፣ ክርስትና ሲባል ሆነው ያልተገኙትን ለመሆን ጥረት ማድረግና ማድረግ የማይችሉትን ማድረግ ነው:: በርግጥ ዓለምን በልባቸው ስለሚወዱ ዓለምን ላለመውደድ ይታገላሉ፤ ትሑት ለመሆን ጥረት ያደርጋሉ፤ ምክንያቱም በልባቸው ኩሩዎች (በራሳቸው የሚተማመኑ) ናቸው:: ይህ የተብዬ ክርስቲያንነት ገጠመኝ (ተመክሮ) ነው፣

አሁንም በድጋሚ እናገራለሁ፣ ይህ የቤተ ክርስቲያን ተመክሮ አይደለም:: በአትላንቲክ ወይም በፓሲፊክ ውቅያኖስ በኩል ወደፊት አልፈን ብንጓዝም፣ ከምድር ወደ ሰማይ ከቶ መጓዝ አንችልም:: ሰማይ ማለት በሚመጣው ዘመን ወደፊት ቤተ ክርስቲያን የምትደርስበት ቦታ አይደለም:: ቤተ ክርስቲያን ከዚያ ሰማይ ላይ ናት፤ ከቶ ሌላ ቦታ ላይ ሆና አታውቅም::

ሰማይ የቤተ ክርስቲያን መጀመሪያ (መነሻ) እና ማደሪያ ነው፤ ነገር ግን ግቧ (መዳረሻዋ) አይደለም:: ቤተ ክርስቲያን ከሰማይ በቀር ሌላ ቦታ ከቶ የማታውቅ ስለ ሆነች፣ ሰማይ ላይ የመድረሱ ጥያቄ ከቶ አይነሣባትም:: ይህ ሥር ነቀል ሐሳብ ሊመስል ይችላል፤ ሆኖም ሐቅ ነው:: በእግዚአብሔር ቃል ላይ እንዳለው እንደ ማንኛውም ነገር፣ መንፈስ ቅዱስ በልባችን ላይ በሚያደርገው መገለጥ አማካይነት የምትታይ ነገር ናት፤ እርሷን እስካላየን ድረስም ሰማያዊ ጥሪያችንን ልናውቅ አንችልም:: ይህ ጥሪ ወደ ሰማይ አይጠራንም፤ ይሁን እንጂ እኛ የሰማይ ወገኖችና በሰማይ ያለን መሆናችንን እንድናውቅ ያደርገናል:: ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን አሁን በመንግሥተ ሰማይ ያሉ ዜጎች ኩባንያ እንጂ ወደ መንግሥተ ሰማይ ለመጓዝ ጥረታቸውን የሚያካሂዱ ክርስቲያኖች ኩባንያ አይደለችም:: ዳግመኛም ልብ በሉ፣ "ከሰማይ ከወረደው ከሰው ልጅ በቀር፣ ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም" (ኢ.መ.ት):: ቤተ ክርስቲያን እንደ ክርስቶስ ትሆን ዘንድ መጸለይ አያስፈልጋትም:: የሚያስፈልጋት ከጌታዋ ጋር እዚያ ኅብረት ያላት ሆና ቦታዋን ማየት ብቻ ነው::

ስለ ቤተ ክርስቲያን ያለንን ሐሳብ እንደ ገና መከለስ ያስፈልገናል:: ዕቅድ ሊወጣላት የሚያስፈልጋት ድርጅት አይደለችም፤ ወይም ፍጻሜ ላይ መድረስ የሚያስፈልጋት የሰዎች ስብስብ (ኩባንያ) አይደለችም:: ሊስተዋል (ሊጨበጥ) የሚገባ ፅንሰ ሐሳብ አይደለችም፤ ልትገኝም የሚገባ ውብ ነገር አይደለችም:: ማንኛውም ነገር በክርስቶስ የእኛ እንደ ሆነው፣ ቤተ ክርስቲያን በቃሉ በኩል በመንፈስ ቅዱስ ርዳታ መታየት ያለባት እውነታ ናት:: የቤተ ክርስቲያንን እውናዊ የሰማይ ባሕርይ ስንገነዘብ፣ የታደሰው ተፈጥሮአችን (ሰማያዊ ማንነታችን) በእኛ ላይ ወገግ ይላል፤ ከዚያም ክርስቲያናዊ ጂማሮአችን ምድር ሳይሆን ሰማይ መሆኑን እናውቃለን:: ቤተ ክርስቲያን ፈጽሞ መሻሻል የማያስፈልጋት ፍጹም አካል ናት:: የነገረ መለኮት ሊቃውንት በአግራሞት፣ "ያ የቤተ ክርስቲያን አቋም ነው፤ ያለችበት ሁኔታ ግን እንዲህ አይደለም" ይላሉ:: ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት በዘላለማዊቷ ቤተ ክርስቲያን ላይ ኢፍጹምነት





የለም:: ከአሮጌው ፍጡር ጋር ግንኙነት ባላቸውና ማብቂያ በሌላቸው ጥያቄዎች ላይ መጨነቅ ለምን ያስፈልጋል? በመለኮታዊ ጸጋ ዘላለማዊ እውነታን ስናይ፣ ከእይታ ይጠፋሉ:: ቤተ ክርስቲያን ማለት እግዚአብሔር በምድር ላይ ሥልጣኑን የሚፈጽምባት ቦታ ናት፤ እንግዲያውስ ዛሬ በዚህ በተበከለው መላለም ውስጥ ለራሱ ማደሪያ የሚሆን ስፍራ አለው::

## የወርቅ መቅረዞች

ስለ ቤተ ክርስቲያን የቱን ያህል ብስጩ ነን! ራሳችንን ለቤተ ክርስቲያን አሳልፈን ለመስጠት የቱን ያህል ፈቃደኞች ነን! ቤተ ክርስቲያን ስሕተት የምትሠራ ቢሆን ምን ይሆናል? ከተሳሳተ መደመደሚያ ላይ ብትደርስስ ምን ይሆናል? እንላለን:: ነገር ግን በዚያ ለሚከሠት ለማንኛውም ዐይነት አለመሳካት ጌታ ደንብ አላበጀም:: በሐሳቡ፣ እንዲህ ያለ ክፍተት ይከሰታል ብሎ ያልጠረጠረውን ያህል ነው:: ስለ ቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ስናስብ፣ ከተጠበቀው ሚዛን በታች የወረደች ቤተ ክርስቲያን ናት ብለን እናስባለን፤ ነገር ግን ጳውሎስ "ታጥባችኋል፤ .... ተቀድሳችኋል፤ ጸድቃችኋል" ያለው ለዚያች ቤተ ክርስቲያን ነበር:: እንዲያውም በመጨረሻ በሮም አቀንቃኞች እንኳ፣ ዴማስና እንጥረኛው እስክንድሮስ እንዲሁም ሌሎች ሐሰተኛ ወንድሞች የሆኑ የሐሰት የሆኑት ሁሉ፣ እውነተኛ ከሆነው በጥንቃቄ ይለዩ ዘንድ አስፈላጊነቱን አይመለከትም:: ጳውሎስ በመልእክቶቹ ሁሉ ቤተ ክርስቲያንን ሲያነሣ፣ ስለ እርሷ የሚናገረው ሙሉ በሙሉ ፍጹም እንደ ሆነች ነው፤ አለመግባባት እንዳይኖርም አሻሽሎ የሚገልጽበት ሐረግ አላስፈለገውም::

በሐዋርያው በዮሐንስ ዘንድም ከዚህ የተለየ አይደለም:: በዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 2 እና 3 ላይ የሰው ልጅ በመቅረዞቹ መካከል ሲንቀሳቀስ እናያለን፤ ብሎም እያንዳንዱ ግለሰብ ለእርሱ ያለውን ኀላፊነት ሲያረጋግጥ እናያለን:: ዐይኖቻችን የእርሱን ዐይኖች በመከተል የቤተ ክርስቲያንን ብዙ ጒድለት ወዲያውኑ ያያሉ፤ ይሁን እንጂ ዮሐንስ ትክክል በሆኑ ቤተ ክርስቲያናትና ትክክል ባልሆኑ ቤተ ክርስቲያናት መካከል ልዩነት አለማድረጉን እስተውለን ይሆን? ጒድለታቸው ሁሉ እንዳለ ሆኖ፣ ለእነርሱ የሚጽፍላቸው ጌታ እንደሚያያቸው ነው፤ ይኸውም "ሰባቱ የወርቅ መቅረዞች" *ሙሉ በሙሉ ከወርቅ የተሠሩ ሻማዎች ሆነው ነው::*

የመለኮት እውነታ አንድ ጊዜ ለበራላቸው ሁሉ ያለው ነገር ያው እውነታ ብቻ ነው:: ከእግዚአብሔር እይታ አንጻር ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ወይም

እንዲያ መሆን አለባት እንላለን። እንዲህ አይሆንም፤ ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ወይም እንዲያ አይደለችም! ቤተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር እይታ አንጻር መሆን ያለባት ናት፤ ምክንያቱም ክርስቶስ እንደዚያ ነው። በክርስቶስ ዘላለማዊውን እውነታ ማየት ማለት ቤተ ክርስቲያን ልትሆን በምትችለውና በእውናዊው ገጽታም መካከል ያለውን ልዩነት ማየት ማቆም ማለት ነው። ጌታ ዐይኖቻችንን መከፈት ሲጀምርም፣ ጥቃቅን ነገሮችን እንንቅም። በአንድ ቦታ ላይ አፍኝ የማይሞሉ አማኞችን ስናይ፣ "ይህ ለእግዚአብሔር ምን ጥቅም አለው? ከዚህ ያሉት በጣም ጥቂት ናቸው!" አንልም። "በዚህ በኢ-አማንያን ከተማ ከእኔ ጋር ያለው አንድ ወንድም ብቻ ነው!" ብለን ብሶት አናሰማም። የሐዋርያት ሥራን በምዕራፍ 13 ላይ ስንመለከት እነዚህ ጥቂቶች ያመጡትን አያሌ ውጤት ስንመለከት (ሆነው የተገኙት እንደዚያ ነውና)፣ በአማኞች ቍጥር አነስተኛነት ጭንቀት ውስጥ አንገባም። እንዲህ ብለን ማሰብን እናቆማለን፦ በዚህ ቦታ በቂ የቤተ ክርስቲያን ውክልና አልነበረም፤ እንደነዚህ ያሉ ዋና ዋና ርምጃዎች የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አጠቃላይ ጉባኤን መጠበቅ ነበረባቸው ብለን ማሰብን እናቆማለን።

ነገሩ እንዲህ አይደለም፤ እነዚያ አማኞች ሰማያዊውን እውነታ በማየታቸው ረክተናል፤ በመሆኑም ቴክኒካዊ አሠራሮች ባይዋጡ አንጨነቅም። የቤተ ክርስቲያንን እውነታ እነርሱ እንዳዩት ስናይም፣ ቤተ ክርስቲያንን ባገኘናት ቦታ ሁሉ እየሠራች መሆኗን እናስተውላለን፤ ሰዎች፣ መገኘት የሚገባቸው ተወካዮች "በቂ ውክልና አልነበረም" ባሉት ላይ እንኳ በጥቂት አማኞች ስብስብ ትሠራለች። ራሳቸውን በሁሉም ነገር ራስ ለሆነው ቢያስገዙ፣ ለራሳቸው ወይም ለቤተ ክርስቲያን ሳይሆን ለክርስቶስ ብዙ ቢሠሩ፣ ከዚያ ቀጥሎ የእግዚአብሔር መንፈስ ለእነርሱ ምንጊዜም ይመሰክርላቸዋል።

እስኪ ጽንፍ ያለውን ነገር ተመልከቱ። ሐናንያ በደማስቆ ሳለ ወደ ሳውል የሄደው ብቻውን ነው፤ እርሱ ብቻም በሳውል ላይ እጁን ጫነ። "ከሥርዐት ውጭ ነው!" ብላችሁ ትጮኻላችሁ። "ይህ የአካል መርሖች ተቃራኒ ነው! በርግጥ፤ ያ በብቻ የተከናወነ ሥራ ነው!" ፈጽሞ አይደለም! ሐናንያ ደቀ መዝሙር ነበር፤ ይህ እውነት ነው፤ ይህ ደቀ መዝሙር ግን ራስ በሆነው የሚንቀሳቀስ (የአካል ብልት መንቀሳቀስ ባለበት ሁኔታ) ነበር። በዚያ ሰዓትም የጌታ ዐይኖች በሐናንያ ላይ ብቻ ሳይሆኑ በሌላው ሰውም ላይ ነበሩ። ሐናንያ ለዚህ ዐዲስ ወንድም የፈጸመው ተግባር ለክርስቶስ መገዛቱን በጉልሕ መልኩ





የገለጸ ነበር፤ በእነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች መሠረትም ሐናንያ ሲንቀሳቀስ ሙሉው አካል ተንቀሳቀሰ ማለት ነው።

ወደ ቤተ ክርስቲያን ዘላለማዊ እውነታ እንድትመጡ የሆናችሁ ከሆነ፣ ለናንተ ራሳችሁ ስለ መላዋ ቤተ ክርስቲያን እንድትናገሩና እንድትሠሩ የምትጠሩበት ጊዜ ሊመጣ ይችላል። ታዲያ ይህን ኀላፊነት ለመያዝ ፈቃደኛ አትሆኑ ይሆን? አንድ ብልት ለክርስቶስ መንፈስ በእውነት የተገዛ ሆኖ የሚያደርገው እንቅስቃሴ የሙሉው አካል እንቅስቃሴ ነው። በዚያ ሰዓት የዚያ ዐይነቱ ሰው ሕይወት ውጫዊ የሆነውን ነገር ሁሉ ይበልጣል፤ እግዚአብሔር ዝ ዚያ አባል በኩል እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ሰዎች ይገነዘባሉና።

የዚህ ሁሉ እንድምታዎች እጅግ ታላላቅ ናቸው። ነገሮችን በሮም ወይም በተሐድሶ ዐይኖች፣ ሥዕላዊ በሆነ መልኩ ወይም ምሑራዊ በሆነ መልኩ የምናይበት ምክንያት የለንም። እግዚአብሔር የሚያየው "ሰባት የወርቅ መቅረዞችን" ነው። እርሱ የሚያውቀው "ቤተ ክርስቲያኒቱን" ብቻ ነው፤ የእውነት መንፈስ ወደ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ እውነት እንዲመራን ስንፈቅድ እግዚአብሔር የሚያያትን ቤተ ክርስቲያን ብቻ እናያለን።

ስለ እነዚህ ነገሮች በልዩ ልዩ አገሮች ለሚገኙት ክርስቲያኖች ስናገር ሁሉም፣ መሪዎችን ጨምሮ፣ አንድ ዐይነት ጥያቄዎች አሏቸው። "*በዚህ ምድር ላይ እንደ እግዚአብሔር ሐሳብ አንድ ነገር ማግኘት ይቻላል ነው የምትለን?* በማለት በአንክሮ ይገልጻሉ። አንተ ሐሳባዊ ነህ። እየተከተልህ ያለኸው ቅዠትን ነው። ሆኖም አንተ ትክክል ነህ ብለን እናስብ፤ እነዚህ ነገሮችም በአንተ የሕይወት ዘመን በተወሰነ መልኩ ይፈጸማሉ፤ ቀጥሎ ያለው ትውልድስ? አንተ አሁን ተመክሮህ እያደረግኸው ያለው ነገር እንደማንኛውም ነገር ይጓዛል። ባሕርዩ (መልኩ) ይለወጣል፤ በጥቂት ዓመታትም ውስጥ ሲኖር የሚችለው የሕልምህ አስቂኝ ምስል (ነጠላ ምስል) ብቻ በመሆን ነው።"[5]

ርግጥ ነው፣ በዐዲስ ኪዳን ውስጥ ነገሮችን ከጳውሎስ አገልግሎት አኳያ ብቻ የምታዩ ከሆነ፣ እንዲህ ያለው አዝማሚያ እውነት መስሎ ሊታያችሁ ይችላል ብዬ ዐስባለሁ፤ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን፣ የዮሐንስ

---

[5] ላለፉት ሰላሳ ዓመታት ቃሉን በመስበክ በኩል ጸሐፊው እድገትን አረጋግጦአል። ይህም በቻይና አገር እጅግ ፍሬያማ የሆነ የእግዚአብሔር መንፈስ ሥራ ነው፤ የክርስቶስ ኀይል የራሱ በሆኑት በማደርም ብርቱ ማዕበሎችን ያቆመ መሆኑን እንባቢን ማስታወሱ መልካም ሳይሆን አይቀርም - አርታዒ።

አገልግሎት ገና አለ። እግዚአብሔር በእነዚህ ሰዎች በኩል ሲሠራ የነበረው ለዘላለሙ ነው ለዐሥር ወይም ለሃያ ዓመታት አይደለም። ስለ እግዚአብሔር መንፈሳዊ ቤት "የመጀመሪያ ትውልድ" እና "ሁለተኛ ትውልድ" ብሎ ነገር የለም[6] "ከትውልድ እስከ ትውልድ" ነው። እርሱ ራሱ ከቶ የማይለወጥ ከመሆኑ በቂ ምክንያት የተነሣ፣ እግዚአብሔር በእይታው ውስጥ የያዘውን ከቶ አይተወውም። ታዲያ ሌላ መለኪያን ለመቀበል እንደፍራለን? ዕንቊዎችን ለመግዛት የማትችል ሴት የአርቲ ጌጣጌጥን ገዝታ የዕንቁ ቅብ እንደ ሆኑ ታስባለች። ዕንቊ ማሰር የቻለች ሴት ግን የዕንቊ ምስል ቢሆንም እንኳ ስለ አርቲ ጌጥ አትጨነቅም። በእርሷ ዘንድ ከዕንቊዎች በቀር እውነተኛ ዕንቊና የሐሰት ዕንቊ የሚባል የለም። በእርሷ ዘንድ የአርቲ ጌጥ ከዕንቊ ጋር ቅንጣት ግንኙነት እንደሌለው ሁሉ የዕንቊ ቅቦች ከእውነተኞቹ ዕንቊዎች ጋር ግንኙነት የላቸውም፤ ዕንቊዎች ናቸው ብላ የምታስባቸው እውነተኛ ዕንቊዎችን ብቻ ነው።

"ዘወርም ብዬ ሰባት የወርቅ መቅረዞች አየሁ"። "በመንፈስም ወደ አንድ ትልቅና ረጅም ተራራ ወሰደኝ፣ ቅድስቲቱ ከተማ ኢየሩሳሌም ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አሳየኝ። .... የብርሃኗም ድምቀት እጅግ እንደ ከበረ ድንጋይ .... ነበር።" (አመት) ዐይኖቻችንን በዚያ እንዳተኰርን፣ ስለ ዮሐንስ አገልግሎት እግዚአብሔርን ማመስገን እንችላለን!

[6] ልዩነት የመጣው፣ በአንደኛውና በሁለተኛው ክርስቲያናዊ ትውልድ መካከል በተከሠተ ልዩነት ነው - ይኸውም በመጀመሪያው ሚሲዮናዊ የወንጌል እንቅስቃሴ ማዕበል በክርስቶስ ከአረመኔነት ትድግናን ባገኙት መካከልና ከእነርሱ በኋላ በስም ብቻ ክርስቲያኖች ሆነው በተገኙት መካከል ነው - አርታዒ።





# ምዕራፍ ዐሥራ አንድ

## ድል የሚነሣ

ሐዋርያው ዮሐንስ የእግዚአብሔር ግብ አይቀሬ መሆኑን ያረጋግጣል፤ መንገዶቹም ከግቡ ጋር አዝልቆት አላቸው። በመጨረሻ ላይ በሰማያዊ ከተማ፣ የአካል መርሖች የመጨረሻውን እድገትና መገለጫ እንደሚያገኙ ሁሉ ተቃራኒውም እውነት ነው። ዘላለማዊነት ያላቸው ነገሮች ዛሬ በእኛ ላይ ነጻ እንቅስቃሴ እንዳላቸው ሁሉ፣ የሰማያዊ ከተማ ገጽታ፣ የጌታ ኢየሱስም እውነተኛ ባሕርይ በዚህ በምድር ላይ በአካሉ ላይ ተገልጦ እናገኛለን። የሰማያዊውን ሰው ማንነት በውልብታ ያየ ሁሉ ከዚያ ዝቅ ባለ ነገር ከቶ እንዴት ሊረካ ይችላል?

ነገር ግን አሁን የተግባር ሰዎች መሆን አለብን፤ ብሎም በዙሪያችን ያለውን ሁኔታ ማየት አለብን። ውጫዊ የሆነው ክርስትና ዛሬ በሚያሳዝን ሁኔታ የሚገኝ መሆኑን ብዙዎቻችን እንስማማለን። የዓለምን በሽታና ድካም ሁሉ አጉልቶ ያሳያል። የክርስትና ተግባር ወደ መለስተኛ ስብከትና ወደ አነስተኛ ማኅበራዊ አገልግሎት ወርዶአል። በሰዎች ላይ ያለው ተጽዕኖ ጉልቶ የሚታይ አይደለም። ይህ ሐቅ ነው፤ ነገር ግን በግላችን ሊያስጨንቀን የሚገባው ነገር፣ እንደ እግዚአብሔር ሕዝብ፣ ጎሊናችን በዚህ ጉዳይ ላይ የማይጨነቅበት የመሆኑ አሳዛኝ ሁኔታ ነው። ነገሮችን እንደ አመጣጣቸው እንይዛለን፤ ብዙዎችም በዚያ ባሉበት መገኘት አለባቸው ብለው ያስባሉ። ጳውሎስ በፊታችን ያስቀመጠውን ነገር ዛሬ ክርስቲያኖች የሚቻል ነው ብለው አያስቡም። እንዲህ ያለ አለማመን ወደ ዮሐንስ አገልግሎት ተመልሰን እንድናመራ ማድረግ አለበት፤ ልዩ ባሕርዩ እንደ ገና እንድናይም ማስገደድ ነበረበት።

ቀደም ሲል እንዳየነው፣ የክርስቶስን አካል አስመልክቶ ጌታ በጳውሎስ በኩል የገለጠው፣ በእያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ያ አካል እንዲገለጥ ታቅዶ ነበር። በተለያዩ አጥቢያዎች የልዩ ልዩ አካላት ሠራዊት ሳይሆን የአንዱ አካል እውነተኛና ተግባራዊ መገለጫ ይኖራል። ይህ መለኮታዊ ዕቅድ ነበር፤ ነገሮች የጀመሩትም በዚህ መልኩ ነበር። ይሁን እንጂ በሚያሳዝን ሁኔታ እንዴት እንደ ወደቁ፣ ጌታም ራሱ ከሰማይ ሆኖ እንዴት መናገር እንደ ነበረበት እናውቃለን። ይህን በማድረጉም ቤተ ክርስቲያንንና አብያተ ክርስቲያናትን አስመልክቶ ዐዲስ ሐሳብን ዳሰሰ፤ የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ ሁለትና ምዕራፍ

ጉበዛዝት፣ አባቶች ብሎ ሲመድብ፣ በዘሌዋውያን ካለው ጋር አንድ ተደርጎ መታየት እንደሌለበት ልብ እንበል:: እየተናገረ ያለው የኀጢአት ይቅርታ ርግጠኝነት ላላቸው፣ የእግዚአብሔር ቃል ማደሪያቸው ለሆነው፣ ለመንፈሳዊ ተዋጊዎች፣ ለሕፃናት፣ ለልጆች፣ ለጦር ሰዎች፣ የነገሮች ሁሉ ምንጭ የሆነውን ሙሉ በሙሉ ያውቁ ዘንድ እነዚህን ሁሉ ይዘው ለሚጓዙት ለመንፈሳዊ አባቶች ነው:: ዛሬ ማንም ሰው በየትኛውም መንፈሳዊ የዕድሜ ምድብ ቢሆን በውጊያ ላይ ከመካፈል ነጻ አይሆንም:: ርግጥ ነው፣ በመንፈሳዊ ነገሮች ረገድ የጡረታ ዕድሜ እንደሌለ ሁሉ፣ በክርስትና ሕይወትም ውስጥ ለነገ የሚባል ብስለት መኖር የለበትም ("ጉበዛዝት" የሚለው ቃል በዘሌዋውያን ላይ ይህ እውነት ቢሆንም እንኳ፣ በመንፈሳዊ መለኪያ የውትድርና ፋይዳ መሠረት ኩረዳዎችንም ያካትታል::)

እንግዲህ መንፈሳዊ ታሪካችን የቱንም ያህል ይርዘም፣ እያንዳንዳችን ራሳችንን መጠየቅ ያለብን ጥያቄ ይህ ነው፤ በማደሪያው (በመቅደሱ) ውስጥ የእኔ የአሁን የሆነው ፋይዳ ምን ይሆናል? ነው:: እያንዳንዳችን ለእርሱ የቱን ያህል ዋጋ እንዳለን እግዚአብሔር ቁርጠኛ የሆነ ስሌት አለው:: በግላችን ያውቀናል፤ ለእያንዳንዳችን የማደሪያው ፋይዳም (ዋጋም) በመንፈሳዊ ብርታት ሚዛን ተመዝኖአል:: ዘመናችን የቱንም ያህል ሠላሳ ወይም ዐምሳ ተብለን ልንለካ ስንችል፣ ዐሥራ አምስት የብር ሰቅል ተብለን የምንጻፍበት የለም:: እያንዳንዳችን የካሌብን የአልበገርነት መንፈስ ዛሬውኑ መጠጣት አለብን!

## የወንድሞች ከሳሽ

ዮሐንስ "ልጆቼ ሆይ"፣ ላላቸው ልጆች ስለ ኀጢአት ይቅርታ ርግጠኝነት ጻፈላቸው:: በአንድ በኩል ሲታይ፣ እንደ ዮሐንስ አገላለጽ፣ ምንጊዜም ልጆች ነን፤ በዚህ ሕይወት እስካለን ድረስ ከቡር የሆነው የጌታ ደም ከማያስፈልገን ደረጃ ከቶ አንደርስምና:: ይህ በርግጥም የድል ነሺው የመጀመሪያ የጦር መሣሪያ ነው:: በዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 12 ላይ ስለ ወንድሞች ከሳሽ ሲጽፍ እንዲህ ይላል፤ "ቀንና ሌሊት በአምላካችን ፊት የሚከሳቸው የወንድሞቻችን ከሳሽ ተጥሎአልና:: እነርሱም ከበጉ ደም የተነሣ ከምስክራቸውም ቃል የተነሣ ድል ነሡት፤ ነፍሳቸውንም እስከ ሞት ድረስ አልወደዱም" (ቁ 10፣ 11)::

በመንፈሳዊ ጦርነት ውስጥ ምንጊዜም የድል ነሺነት መሠረት ከቡር የሆነው ደም ነው:: ደሙ በሌለበት ቦታ ማንም ከቶ የትም ሊደርስ አይችልም:: ሰይጣን ነፍሰ ገዳይና አታላይ ነው፤ ያባብላል፣ ያጠቃልም፤ ዛሬ ግን በከሳሽነት





የሠለጠነ ነው:: እንደ እውነቱ ከሆነ የወንድሞች ከሳሽ ነው፤ ጌታችን ሊቀ ካህናትና አስታራቂ ሆኖ እርሱን የሚቋቋመውም ከዚህ ላይ ነው:: ሰማይ የሰይጣንን ሥራ ያውቃል፤ እያንዳንዱ ክርስቲያንም እንዲሁ ማወቅ አለበት:: ሌሊትና ቀን ይከሰናል፤ ከሱ የተነጣጠረውም እርሱን ለመዋጋት ዐቅሙ የለንም ብለን በሚሰማን በኀሊናችን ላይ ነው:: ዐላማው ተስፋ በመቍረጥ እንድናስብ ነው:: "እኔ ለእግዚአብሔር ምን እጠቅማለሁ?" እንድንል:: አንዳንድ ክርስቲያኖች ከጧት እስከ ማታ "እኔ ተስፋ የሌለኝ ሰው ነኝ፤" "እግዚብሔር እኔን ሊያስተካክል አይችልም::" እያሉ ራሳቸውን የሚወቅሱት፣ ደግሞስ የሚጮኹት ለምንድን ነው? የጠላት ክስ መልስ ሊሰጥበት አይችልም ብለው ራሳቸውን ለጠላት ክስ በማመቻቸታቸው ነው:: ከዚህ ደረጃ ላይ የሚያደርሰን ከሆነ፣ ጦርነቱን መዋጋት በመተዋችን እርሱ (ሰይጣን) በርግጥ ድል አድራጊ ነው:: የእግዚአብሔርን ክብር በማየት ፈንታ ክሱን ብቻ የምንቀበል ከሆነ እርሱን የምንዋጋበት ኀይል በርግጥ የለንም ማለት ነው::

ኀሊና እጅግ ውድ የሆነ ነገር ነው፤ ባለማቋረጥ "እኔ ከንቱ ነኝ! እኔ ከንቱ ነኝ!" ማለት ግን ክርስቲያናዊ ትሕትና አይደለም:: በደላችንን መናዘዝ ጤናማነት ነው፤ ሆኖም ኑዛዜአችንን፣ ኀጢአተኝነታችንን ከክርስቶስ ሥራ ይልቅ ጉልሕ ሆኖ ይታያል ከሚል ደረጃ ላይ ማድረስ የለብንም:: ይህን ዐይነት ግራ መጋባት የሚፈጥር ሌላ መሣሪያ እንደ ሌለ ዲያብሎስ ያውቃል:: መፍትሔው ምንድን ነው? "ጌታ ሆይ እኔ ጥሩ ሰው አይደለሁም" ካልን በኋላ ከቡር ወደ ሆነው ደሙ በመመልከት፣ "ጌታ ሆይ እኔ በአንተ እኖራለሁ" የሚለውን ማከል ነው::

ሰይጣን ያለ ምክንያት አይከስም:: የሚያመለክተን እያሌ በደሎች እንዳሉ ጥርጥር የለም፤ ነገር ግን የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኀጢአት ሁሉ ያነጻናል:: ይህንን እናምናለን? ይህ ከሆነ፣ ለክሱ የሚሰጠው መልስ ይኸው ነው:: ኀጢአት ደም ያስፈልገዋል፤ ነገር ግን በደለኞች ነን እስካልን ድረስ መጽሐፍ ቅዱስ ኀጢአት ክስን ያመጣል አላለም:: በርግጥ፣ ኀጢአት የለብንም ካልን፣ በሩ በሰፊው ለከሳሹ ክፍት መሆኑን ዮሐንስ ያስጠነቅቀናል:: ይሁን እንጂ፣ በእግዚአብሔር ብርሃን ፊት በመቆም በደላችንን ለእርሱ ብንናዘዝ፣ ደሙ ለማንጻት ኀይል አለው፣ የሰይጣንም ክሶች ሁሉ ዋጋ የሌላቸው ይሆናሉ:: እንዲህ ያለ ጠበቃ ስላለን እግዚአብሔር ይመስገን! እንዲህ ያለ ሊቀ ካህናት ስላለ አመስግኑት! ጥሩ ጠባይ ስላለን ጐራ በመንዛት ወይም በደላችንን

በማግዘፍ ለሰይጣን ከቶ፣ ደግሜ እላለሁ፣ ከቶ መልስ አንስጥ፣ ሆኖም ደሙ ብቻ ዘወትር መልሳችን ይሁን:: እርሱ ሙሉ በሙሉ በቂ መከላከያችን ነው::

መከላከያችን የክርስቶስ ክቡር ደም ነው፤ የምስክርነታችን ቃል የማጥቂያ መሣሪያችን ነው:: እንዲህ ሲባል ለሰው የእኛ ምስክር መሆን (ምስክርነት) ማለት ሲሆን፣ ምስክርነታችን ለሰው ብቻ ግን አይደለም:: የክርስቶስ ድል ነሺነት፣ እርሱ እየገዛ የመሆኑ ሐቅ፣ መንግሥቱ ቅርብ መሆኗ፣ ከሰይጣን መንግሥት ወደ እርሱ መፍለሳችን (መሸጋገራችን)፣ እነዚህ ሁሉ መታወጅ ያለባቸው ሐቆች ሲሆኑ የሚታወጁትም ለሰዎች ብቻ ሳይሆን ለጨለማ ኀይላት ጭምር ነው:: እግዚአብሔር ንጉሥ እንደ ሆነ አረጋግጡ፣ ልጁ አሸናፊ ሲሆን ሰይጣን የተሸነፈ መሆኑን፣ የዚህ ዓለም መንግሥት በቅርቡ የአምላካችንና የእርሱ ክርስቶስ እንደሚሆን ዐውጁ:: እነዚህ አወንታዊ የመለኮት ሐቆች ናቸው፣ የመከላከያ መሣሪያዎቻችንም ናቸው:: እንዲህ ያለውን የመንፈሳዊ ሐቅ ዐዋጅን ሰይጣን ይፈራል:: የምስክርነታችን ቃል የሲኦልን በር ወደ ኋላ ይመልሳልና:: ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ፤ ስሙም ከስሞች ሁሉ የበላይ እንደሆነ ዐወጁ:: ዐውጁት! ለጠላት ይህንኑ ንገሩት:: ብዙ ጊዜ እንዲህ ያለው ምስክርነት ከጸሎት ይልቅ የላቀ ውጤቶችን ያመጣል::

ጸሎት ሁለት ገጽታዎች አሉት፤ ወደ እግዚአብሔር እና ወደ ተራራው:: 'ይህን ተራራ ከዚህ ተነሥተህ ወደዚያ ሂድ ብትሉት ይሄዳል' (አመት):: ሰይጣንን "ይህን ቦታ ለቀህ ሂድ!" ማለት እንችላለን:: ጴጥሮስ ሽባውን ሰው 'በናዝሬቱ በኢየሱስ ስም ተነሥና ተመላለስ አለው':: ጴጥሮስና ዮሐንስ ጉዳዩን በቀጥታ ተጋፈጡት በዛሬ ጊዜ እኛ ምናልባት የጸሎት ስብሰባ የምንጠራበት ጉዳይ ነው:: ጸሎትን አትናቁ፤ ነገር ግን በክቡር ደሙ ብቃት ተማምኑ የምስክርነትንም ቃል ተናገሩ:: ብዙ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ስንመጣ የአየሩ ድባብ የሚያስጨንቅ ነው፤ እኛም መጸለይ አንችልም:: ምን ማድረግ አለብን? ተስፋ አትቍረጡ፤ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ቃል ይዛችሁ ተመላለሱና ለሰይጣን ንገሩት:: የጌታን ድል አድራጊነት ዐውጁ:: በእባቡና በጊንጡ እንዲሁም በጠላት ኀይላት ሁሉ ላይ እንድትራመዱ (እንድትጫሙ) ሥልጣን እንደሰጣችሁ ዐውጁ:: ከዚያም ጸልዩ!

ዛሬ ለወንጌል አስተምህሮ የላቀ ትኩረት የምንሰጥ መሆናችን የሚያሳዝን ነው:: ለሐቁ ግን እጅግ አነስተኛ ትኩረት እንሰጣለን:: ሐቁ ከሌለን፣ ምስክርነት አይኖረንም:: ይሁን እንጂ ቀራንዮ የታሪክ ሐቅ ነው:: የዚህ ሐቅ የምሥራች የሆነው - ወንጌል - ከእኛ ጋር አለ:: ይህ የወንጌል ሐቅ ለሁለት ሺህ





ዓመት ያህል በምድር ላይ ነበር:: ጌታ የከበረ ደምና ርግጠኛ የምስክርነት ቃል ሰጥቶናል:: በእነዚህ ጠላትን እንግጠመው::

በመጨረሻም በመስቀል ላይ መቸንከር ምን ማለት እንደ ሆነ የሚያውቁ ድል ነሺዎች እነዚህ ወንዶችን ሴቶች ናቸው:: ይኸውም የድል ነሺነት ስሜት የማይሰማቸው ወገኖች ማለት ነው:: ምንም ዐይነት ድል ያግኙ ክብሩ የእርሱ ብቻ ነው:: ደግሞ ከዚህ ላይ እንደ ገና ብዙ ማብራሪያ አያስፈልገንም፤ ሆኖም ኢዮብን በተመለከተ፣ እግዚአብሔርን የተገዳደረው ሰይጣን እንደ ነበር አስታውሱ:: "ቍርበት ስለ ቍርበት ነው፤ ሰው ያለውን ሁሉ ስለ ሕይወት ይሰጣል" (ኢዮብ 2፥4):: ነገር ግን አሁን፣ ለዚህ መልስ እንደ ሆነው ያህል፣ እነዚህን ድል ያደረጉትን አስመልክቶ የሰማይ ታላቅ ድምጽ ያረጋግጣል፤ "ነፍሳቸውንም እስከ ሞት ድረስ አልወደዱም" (ራእ 12፥11):: ታዲያ ያው ድምጽ እንዲህ በማለት ማወጅ ይችላል እኮ፤ "አሁን የአምላካችን ማዳን፣ ኀይልና መንግሥት፣ እንዲሁም የእርሱ ክርስቶስ ሥልጣን መጥቶአል!" (አመት)

## "ይህስ እንዴት ይሆናል?"

ከበድ ስላሉ ስለ አንዳንድ ጉዳዮች ተናግረናል፤ እለዚያ ራሳችንን ከልክ በላይ እንለጥጣለን፤ ጌታን ለማገልገል ለሚሹት ወጣት ወንድሞች በጣም ተግባራዊ ስለ ሆነው ነገር ዕጥር ምጥን ባለ መልኩ መናገሩ ጥበብ ይመስለኛል:: በዮሐንስ ወንጌል በመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ጌታችን ለደቀ መዝሙሩ ለጴጥሮስ ተከታታይ ጥያቄዎችን አቀረበለት:: ከዚያም አንድ ደረጃ ላይ እንደ ተደረሰ፣ ጴጥሮስ ፈራ ተባ እያለና ትኩረቱ ከእርሱ ላይ ተነሥቶ በሌላ ላይ እንዲሆን ጥረት የማድረግ ያህል፣ በዓሣ አጥማጅ ባልደረባው በዮሐንስ ላይ ድንገተኛ የሆነ ሐሳብ ያደረበት መሰለ:: ጴጥሮስም ይህን "ኢየሱስ የሚወደው ደቀመዝሙር" እንደሚከተላቸው አይቶ ኢየሱስን "ጌታ ሆይ፤ ይህስ እንዴት ይሆናል?" አለው:: ይሁን እንጂ ኢየሱስ የትኩረት አቅጣጫው ወደ ሌላ ሰው ዘወር እንዲል ስላልፈለገ "እስክመለስ ድረስ በሕይወት እንዲኖር ብፈልግ እንኳ ምን ቸገረህ? አንተ ራስህ ተከተለኝ" አለው (አመት):: ይህ ሁኔታ፣ እንደሚመስለኝ፣ እያንዳንዳችን ስለራሳችን ተመሳሳይ ጥያቄ በመጠየቅ ግዴታችንን አድበስብሰን እንድናልፍ የማይፈቅድ መሆኑን ነው፤ "ጌታ ሆይ፣ ይህ ሰው እንዴት ይሆናል?" ወይም በጳውሎስ ቃል "ጌታ ሆይ፣ ምን ላድርግ?" (ሐሥ 22፥10) ማለት አለብን::

ከዓመታት በፊት በ1938፣ በእንግሊዝ አገር፣ ወጣት ወንዶችንና ሴቶችን እንዳነጋግር ተጋብዤ ነበር፣ በዚያን ጊዜ ከእነዚህ ብዙዎቹ በምሥራቅ አገሮች የወንጌል መልእክተኛ ሆነው ጌታን ለማገልገል እየተዘጋጁ ነበር። የወንጌል መልእክተኛ ዐይነተኛ መለኪያዎች ምን እንደ ሆኑ እነግራቸው ዘንድ ጠየቁኝ። የወንጌል መልእክተኞች ዘመን ያላለፈ መሆኑን፣ እግዚአብሔርም ከየትኛውም ወገን የሚገኙትን ባሪያዎቹን በዚሁ መስክ ተጋግዘው እንዲሠሩ እየጠራቸው መሆኑን ገለጽሁ። ቀጥሎ ያለው ማስታወሻ በዚያን ጊዜ ለእነርሱ የነገርኳቸውን ዐይነተኛ ነጥቦች የያዘ ነው። በእነዚህ ጥናቶች ላይ በሰፊው ከተወያየንባቸው ውስጥ አንዳንድ ነገሮችን የሚያስተጋቡ ሆነው ይገኛሉ።

*የድነት ርግጠኝነት፦* መነሻ ነጥቡ ይህ ነው፤ እንደነዚህ ያሉ የብቃት መለኪያዎች ሲዘረዘሩ ወይም እንደነዚህ ያሉትን ወገኖች ማለትም ወንዶችን ወይም ሴቶችን ሲያነጋግሩ፣ "ይህንማ ያውቁታል" ብሎ መገመቱ ትክክል እንዳልሆነ ተመክሮው ያስጠነቅቀናል። ለጌታ የምናደርገው (የሆነው) አገልግሎት ሁሉ መሠረት፤ በግላችን እርሱን መገናኘታችን፣ ለራሳችንም ማወቃችን፤ በእርሱ አማካይነትም ለዘላለሙ የዳንን ለመሆናችን ፍጹም ርግጠኛ መሆናችን ነው።

*ክርስቶስ ሕይወታችን፦* ብዙዎች የምሥራቅ የጥንት ሃይማኖቶች ከፍተኛ የሆነ ሥነ ምግባራዊና ግብረ ገባዊ ሕግ ያላቸው መሆኑን ክርስቲያኖችን ለማስታወስ እንወዳለን። በቻይና ኅብረተሰብ፣ በሌሎች ኅብረተሰቦች እንደ ሆነው ሁሉ፣ አንዳንድ ጒዳዮችን በተመለከተ ይህን ያህል ጠበቅ ያለ ደንብ ባይኖርም፣ ቍጣ ወይም ትዕግሥት ማጣት በወንድ ወይም በሴት ላይ ከታየ አሳሳቢ የሆነ ራስን የመግዛት ጒድለት እንዳለ ይታሰባል። ይሁን እንጂ ድል አድራጊ የሆነ የክርስቲያን ሕይወት የማያውቁ የወንጌል ሰባኪያን እነዚህ ጒድለቶች ይታዩባቸዋል፣ ምስክርነታቸውም ከዚህ የተነሣ የቱን ያህል እንደሚሰናከል ልብ አይሉም። በዚህም ምክንያት፣ ሊመሰክሩላቸው የሚፈልጓቸው ሰዎች፣ በሃይማኖትና በግብረ ገብ ረገድ "እኛ ከእነርሱ እንበልጣለን" የሚል አመለካከት ይኖራቸዋል። "እኛ እንበልጣለን" የሚል አምልኮ ላላቸው ሰዎች፣ ከዚህም በላይ መዝናናትና ምቾት የሚፈልጉትን ሰዎች ለሚንቁት ክርስቶስን የምንሰብክ ከሆነ፣ የራስ ለሆነው ነገር በእውነትና በሚያሳምን ሁኔታ በመሞት እውነተኛ የሆነ የማረጋገጫ መልስ መስጠት ያስፈልገናል። መስቀሉን ከኀጢአትና ከሥጋ ምኞት ትድግናን ያገኘንበት





አድርገን ማወቅ አለብን፣ በዐዲስ ሕይወት ለመመላለስም ከተነሣው ክርስቶስ በቂ ኀይልን ማግኘት አለብን።

*በጌታ ሙሉ በሙሉ መደገፍ፦* የአንድ "የቡድን እምነት" መለማመድ ቀላል ነው፤ ዐይኖቻችን እርሱን ትተው ወደ የአቅርቦት ምንጭ ሳይቅበዘበዙ፣ እግዚአብሔርን ብቻ መታመን ግን እጅግ ከባድ ነው። የምዕራብ ሰዎች "የሩቅ - ክርስቲያኖች" በማለት ይናገራሉ፤ ነገር ግን በዘመኑ አባባል፣ "የእምነት ሕይወትና ምልክቶች" ብለን ልንጠራው የምንችለውን፣ ወይም አንድ ሰው "እምነትና የፖስታ ቴምብር" ብሎ እንዳስቀመጠው ዐይነት በሁላችንም ላይ ድብቅ የሆነ አዝማሚያ ማየት እንችልምን? የእግዚአብሔር ባሪያዎች "ስለ ሥራው ብቻ" መናገራቸው ወይም መጻፋቸው በጣም ስሕተት ነው፤ ከዚህ ይልቅ ስለዚሁ ጒዳይ ከጌታ ጋር በእጅጉ ታማኝ መሆን አለባቸው። በዚህ ዐይነቱ መንገድ እጆቻችን በእግዚአብሔር ታምራት ላይ ባላረፉ ቍጥር የተሻለ ይሆናል። ለእግዚአብሔር ነገሮችን ብርቱ ለማድረግ መፍራት የለብንም - ብርቱ ማድረግ ያለብን ግን አንድ ሰው ካልተጠራ በቀር "ለወንጌል አገልግሎት" እንዳይደፍር ነው። ምናልባት ርግጠኛ የሆነው በጎ ነገራችን የሌሎችን ፍላጎት ማሟላት ሊሆን ይችላል። እነርሱን እንከባከብ፣ እግዚአብሔር ለእኛ ያስብልናል።

*ልዩ አገልግሎት፦* ልጆቹ እንደ መሆናችን መጠን፣ ሁላችንም ለጌታ እንድንመሰክር ጥቅል የሆነ ግዴታ አለብን፤ ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ባሪያ ከዚያ ባለፈ መሥራት አለበት። ግልጽ በሆነ መልኩ የራሱ በሆነው፣ በመንፈስ በተሠራ በእግዚአብሔር ዕውቀት ተለይቶ የሚታወቅ መሆን አለበት። የእርሱ አገልግሎት ከዚህ ውስጥ መመንጨት አለበት። በቻይና ወይም በየትኛውም ቦታ ለምትገኝ ቤተ ክርስቲያን፣ ማድረግ የምንችለው ወንጌልን መስበክና በአጠቃላይ መልኩም ማገዝ ከሆነ፣ ጠቃሚነታችን እጅግ አነስተኛ ይሆናል። ይህ ተግባር ከማንኛውም ክርስቲያን የሚጠበቅ ነው፤ ይሁን እንጂ ቻይናውያን አማኞች ከእኛ የላቀ ነገር፣ ልዩ የሆነ ነገር (አገልግሎት) ይጠብቃሉ፤ የቱንም ያህል የተዋጣለት ወይም ያማረ ይሁን በልዩ ትምህርት ወይም አስተምህሮ የእነርሱን ፍላጎት አናሟላም፤ ደግሜ እላለሁ፣ ፍላጎታቸውን ማሟላት የምንችለው በተለየ መልኩ የእኛና የእኛ መገለጫ ባሕርይ በሆነው በጌታ ዕውቀት ብቻ ነው። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ለቃሉ ጥማት (ረሃብ) የላቸውም ብለን ቅሬታ እናሰማለን፣ ሆኖም እመኑኝ፣ የምንሰጣቸው ልዩ የሆነ ነገር ካለን ለቃሉ የተጠሙ ይሆናሉ። በመካከላቸው በመገኘታችን፣ ሰዎች ለእግዚአብሔር

ጥማት እንዲኖራቸው እያደረግን ነውን? በሚገባ የተዘጋጀ ምግብ ራሱ ረሃብን ይሰቃል፤ ሰዎች፣ እንዲያው ዝም ብሎ የሚሰብኩትን ወይም አጠቃላይ ዕውቀት የሚሰጡትን ሳይሆን፣ ከጌታ ጋር በግል የመቆየትን ውጤት የሚያመጣ መንፈሳዊ ሀብትን የሚያገለግሉ፣ በመንፈስና በፍቅር የተሞሉ ወንዶችና ሴቶችን ሲያዩ ይራባሉ:: ርግጥ ነው፤ ረሃብን የማናሳድር ከሆነ በእኛ ዘንድ ጉድለት አለ ማለት ነው::

*የተማሪው ጠባይ::* ምንጊዜም ቢሆን በጀርባችሁ ላይ "ተማሪ" የሚለውን ፀዝላችሁ ተጓዙ[7]:: ሌሎችን "እናስተምራን" የሚሉ ራሳቸውን ለአደገኛ ሁኔታ ያጋልጣሉ:: ብዙዎች ራሳቸውን ከልክ በላይ ይዘረጋሉ፣ በተመክሮ ስላላፉበት ነገር (ገጠመኝ ሳይኖራቸው) በመናገርም በገራገር ቅዱሳን አእምሮ ላይ ችግር ይፈጥራሉ:: ከልክ በላይ ርግጠኞች ብንሆንና በጥድፊያ አንድ ነገር ለማለት ዝግጁዎች ከሆንን፤ ባለፈው ጊዜ ምን መልስ እንደ ሰጠን ለማስታወስ እንቸገራለን፤ ወይም በዚህ ጊዜ ሌላ ዐይነት እንደ ሰጠን ሊሰማን ይችላል! ብዙ እናውቃለን ባልን ቊጥር፣ እድማጮቻችን እኛኑ እንዲተቹን ይበልጥ የምናመቻች እንሆናለን፤ ምክንያቱም ከእኛ ብዙ እንዲጠብቁ ይገፋፋሉ:: እናውቃለን የሚለው ከልክ በላይ የሆነው የመታመን ስሜት፣ ማለትም እንዲህ ያለው የበላይነት ስሜት፣ ለሌሎች እንድናካፍል የተሰጠንን ነገር እንዳናካፍል በሩን ይዘጋብናል:: ይልቁን አላዋቂነታችንን ለመቀበልና ስለዚሁ ሁኔታ ጌታን እንድንጠይቀው ጸጋ ያስፈልገናል:: "አላውቅም" ለማለት ፈቃደኞች መሆን አለብን:: "የምትለው ነገር ካለህ ለመስማት ዝግጁ ነኝ፣ ምክንያቱም እኔም የጌታ ደቀ መዝሙር ነኝ" ሠራተኛ ላይ ሰዎች አይጨክኑም:: በሚል የምሰጣችሁ ምክር የዕድሜ ልክ ተማሪዎች እንድትሆኑ ነው:: "ተማሪ" የሚለውን ምልክት ቢያንስ ቢያንስ ለዐሥር ዓመት ጀርባችሁ ላይ ለጥፉት!

*የእግዚአብሔር ሥራ ታሪክ፡* እንዲህ እምናለሁ፤ እያንዳንዱ የእግዚአብሔር ባሪያ የእግዚአብሔር ኀይልና ህልዎት በራሱ ታሪክ ውስጥ ያለ ለመሆኑ ኗሪ ማረጋገጫ ይኖረው ዘንድ ያስፈልጋል እላለሁ:: ዝናብ እንዲዘንብ የቀረበውን የእምነት ጸሎት እግዚአብሔር የመለሰ ስለ መሆኑ በሌላ ጽሑፌ[8] ላይ አወሳቻለሁ:: ይህን ሁኔታ ማንኛችንም አልረሳነውም:: ይሁን እንጂ

[7] ይህ ንግግር በቀረበበት ወቅት የተማሪነት ፈቃድ ባላቸው ተማሪዎች መኪና ላይ 'የተማሪነት' መለያ ምልክት በእንግሊዝ አገር ቀደም ብሎ የታወቀ ነበር፤ ስለዚህ ራሰን በይፋ "ተማሪ ነኝ" ብሎ ማስታወቅ ጸሐፊውን በብርቱ ማርኮ ነበር - አርታዒ::

[8] "ተቀጥሮ፣ ተመላለስ፣ ቁም" በሚል ጽሁፍ ምዕ. 3





የምዕራብ የወንጌል መልእክተኞች ባህላዊና ታሪካዊ ዳራ አላቸው:: መግለጫ ያወጡላቸው አንዳንድ ነገሮች አሉ፤ ዛሬ ደግሞ በእኛው ዘመን ታምራት ዘወትር ባለመከሠታቸው ክርስቲያን አስተማሪዎች አስተምህሮን አስደግፈው ገለጻ ለመስጠት ዝግጁዎች ናቸው:: እንዲህ ያለው ምክንያት በገራገር አማኞች ከቶ ተቀባይነት አይኖረውም፤ የእግዚአብሔር እጅ ሲሠራ ራሳቸው ብዙ ጊዜ አይተዋልና::

ቾን የተባለ ልብስ ሰፊውን ሰው አስታውሳለሁ:: በእጅጉ ትሑት ሰው ነበር:: ከዚህም በላይ ከሌላ ክርስቲያን ጋር ተገናኝቶ አያውቅም ነበር:: ያለው ነገር ቢኖር የማርቆስ ወንጌል ብቻ ነበር፤ ሆኖም የማርቆስ ወንጌልን ዘልቆ በማንበብ አዳኝ የሆነውን ጌታ አገኘ፣ አመነም:: ከዚያም "እጠራጣሪ ከተባለው ምንባብ" ከምዕራፍ 16 ላይ ደረሰ! በጥንቃቄ ካነበበውም በኋላ ወደ ጌታ "ጌታ ሆይ፤ ምስኪን ሰው ስለ ሆንኩ አንድ ስጦታ ብቻ ይበቃኛል:: የፈውስ ስጦታን ስጠኝ!" አለ:: ወዲያውኑም መጣ፤ ከቤትም ቤት በመሄድ በመንደሩ ውስጥ ላሉት ሕመምተኞች ጸለየ:: ከጊዜ በኋላ እርሱን አግኝተን ጠበቅ አድርገን ስንጠይቀው፣ የተቋቋመው በሽታ ከባድ ቢሆንም ወይም ቶሎ መልስ የሚያስፈልገው ነባራዊ ሁኔታ ቢኖርም እንኳ፣ ትሕትናው በእግዚአብሔር ላይ ካለው ፍጹም መታመን ጋር ተደምሮ በዚያ መንደር ውስጥ አስደናቂ ክሥተቶች እውን እንዲሆኑ አብቅቶአል:: ጌታ የአማልክት ሁሉ አምላክ መሆኑን ጣዖት አምላኪዎች ተቀበሉ፤ ከእነርሱም ውስጥ አንዳንዶች አማኝ ሆኑ:: ይሁን እንጂ እላስፈላጊ እኔነት ወይም ጉራ ሳይሰማው ተራ የመንደር ልብስ ሰፊነት ሙያውን እንደ ያዘ ትሑት ወንድም ሆኖ አገኘነው::

በምዕራቡ ዓለም በአንድ አጋጣሚ፣ በአንድ ቅኖች በሆኑ ወንድሞች ጉባኤ ላይ ተገኝቼ ነበር፣ እነርሱም አስቸጋሪ በሆኑ በአንዳንድ አስተምህሮአዊ ውይይት ላይ እያደር እየተመሰጡ ሲሄዱ ስሰማቸው፣ ከረጅም ውይይት በኋላ ጣልቃ እንድገባ ተገድጄ ነበር:: "የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ!" በማለት በአግራሞት ጀመርኩ፣ "በእኔ አገር ሁኔታው እስገድዶ እያለ ኢጋንንትን ማስወጣት ካልቻላችሁ፣ ስለ እነዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዝርዝሮች ያላችሁ ዕውቀት ሁሉ ምንም ጥቅም የለውም!" ዛሬ በጣም ሥልጡን ሆነናል፤ ከዚህ የተነሣ፣ ብዙ ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ በሩን እንዘጋለን:: እግዚአብሔር ወደ አንድ አጋጣሚያዊ ዕድል የሚያመጣን ይመስለኛል፤ ከዚያም፣ ተፈጥሮአዊ ጥንቃቄአችን በእምነት ወደ እርሱ እንዳንወጣ ስለሚያደርገን በታምራዊ ሕይወት ፈንታ፣ የምናተርፈው ዐዲስ ትምህርት ብቻ ነው:: ይሁን እንጂ

በርግጠኝነት እናገራለሁ፤ እግዚአብሔር ቃሉን በምልክቶችና በታምራት እንዲያትም ተስፋ ማድረግ አለብን። እግዚአብሔርን በእውነት ካወቅነው፣ አስደናቂ ሥራዎቹ ሩቅ አይሆኑም። ዛሬም ቢሆን የሰይጣን መቀመጫ በሕያው እግዚአብሔር ላይ ባለን እምነት ተሸቀንጥሮ መጣል አለበት።

## የእግዚአብሔር ጥሪ

ማንም አዛዥ እንደ ጌታችን እጅግ ብዙ ባሪያዎች የሉትም፤ ለእያንዳንዱም ተስማሚ የሆነ የሥራ ድርሻ አለው። እስራኤልን ከረሃብ ለመታደግ ለዮሴፍ የተለየ የሥራ ደርሻ ነበረው። በኋላ ላይ ኤልያስ በንጉሡ ምትክ ነቢዩን ለመተካት ቢመጣም እንኳ፣ ሊቀ ካህናቱን ትቶ ንጉሡን ለመተካት ለሆነ ለተለየ ሥራ ሳሙኤል በተመረጠው ሰዓት መጣ። ንዕማን በተቸገረ ጊዜ ለእርሱ ለመመስከር ታናሽ የሆነችው እሥራኤላዊት ባሪያ መጣች። ወደ ኢየሩሳሌም ለመጓዝ አህያ እንኳ ለኢየሱስ ዝግጁ ነበረች።

ብዙዎች እግዚአብሔር በሰጣቸው ኀላፊነት ላይ፣ ወይም በአካሉ (በቤተ ክርስቲያን) ውስጥ በሰጣቸው ዐደራ ያጕረመርማሉ። እነርሱ ይህን ማድረግ ይፈልጋሉ፤ እግዚአብሔር ግን በዚያ ላይ ያስቀምጣቸዋል። በዚህኛው ቦታ ሊያገለግሉት ብርቱ ምኞት አላቸው፤ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ለእነርሱ ያለው ዕቅድ በሌላ በአንድ ቦታ ላይ ነው። እንዲህ ያለ ግልጽ አለመግጣጠም ሲደርስ፣ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ለእኛ ያለው ዐላማ ከመለወጣችን በፊት መሆኑን ማስታወስ ተገቢ ነው፤ በአስቀድሞ ማወቁ አማካይነት ሁኔታዎችን አዘጋጅቶአል፤ ከመወለዳችን በፊት አስቀድሞ መንገዳችንን ወስኖአል። ኢሳይያስ እንደ ተወለደ ተመርጦአል፤ የተርሴሱ ሳውል "ከማሕፀን"፣ ኤርምያስ ደግሞ በማሕፀን ውስጥ ተበጃጅቶ ከመሠራቱ በፊት ተመርጦ ነበር። ስለዚህ "የተመረጠ ዕቃ!" ስለ ሳውል ሐናንያ ከሌሎች ከሰማው ወሬ የተነሣ ግራ ተጋብቶ እንደ ነበር እውነት ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር ለባሪያዎቹ ሙሉውን መንገድ በሚያስደንቅ ሁኔታ አዘጋጅቶአል። ምናልባት ተገቢ ካልሆነው ቤተ ሰብ ተወልደናል ብለን እናስብ ይሆናል፤ ግን የማን ልጅ እንደምንሆን እርሱ ይወስናል። አንዳንዶቻችን ወላጆቻችንን እንቀበላለን፤ ይሁን እንጂ ምናልባት ወንድሞቻችንንና እኅቶቻችንን ወይም ሌሎች ዘመዶቻችንን መለወጥ ያምረናል። ሆኖም ዮሴፍ፣ "ነገር ግን እግዚአብሔር ሕይወታችሁን በታላቅ ማዳን ለመታደግና ..... ከእናንተ አስቀድሞ ወደዚህ ላከኝ" አለ (እመት)። በምርጫው ላይ





የእግዚአብሔርን እጅ ያላየን ከሆነ፣ እርሱን ለማመስገን ያለንን ታላቅ ዕድል አጥተናል ማለት ነው።

የዳዊት ሥራ የጀመረው በጎልያድ ላይ ነው፤ ትምህርቱን የተማረው ግን በግ ጠባቂ እያለ ነው። "ከአንበሳ መዳፍ .... ያዳነኝ እግዚአብሔር" ማለት ቻለ (እመት)። ጴጥሮስ ዓሣ አጥማጅ ነበር፣ ስለ ተኵላች መረብ ያውቃል። በኢዮጴ የታየውን "ታላቅ ሸማ" በላቀ መልኩ ሊረዳ የቻለው ከዚህ የተነሣ ሳይሆን አይቀርም። ጳውሎስ አቂላንና ጵርስቅላን ማግኘት የቻለው ድንኳን በመስፋት ችሎታው በኩል ነው። እነዚህ ሁለቱ ጥንቁቅ የእግዚአብሔር ቃል ገላጭ ይሆኑ ዘንድ፣ ያን ሙያ ገንዘብ ያላደረገ ሰው ምንም ማድረግ አይችልም ነበር። በኤፌሶን የማፈግፈግ ሁኔታ በተከሠተበት ወቅት ገና ከሕፃንነቱ ጀምሮ ቅዱሳት መጻሕፍትን የተማረው ጢሞቴዎስ ዝግጁ ሆኖ ቀርቦ ነበር።

እግዚአብሔር ምንም ነገር በድንገት ከቶ አያከናውንም፤ እርሱ እጅግ በጣም ቀደም አድርጎ ሁሉንም አዘጋጅቶታል። ስለዚህ በእግዚአብሔር ጥሪ ውስጥ፣ ብሶት የሚሰማበትና የሚኩራሩበት ነገር የለም። የሚቀናበት ሰውም አይኖርም፤ የሌሎች ሰዎች መልካም አጋጣሚ ከእኛ ጋር ግንኙነት የለውም። "እንግዲህ ምሕረት ለወደደ ወይም ለሮጠ አይደለም፣ ከሚምር ከእግዚአብሔር ነው እንጂ" (ሮሜ 9፥16)። ቅርሳችን (ዘራችን)፣ ትውልዳችን፣ ተፈጥሮአዊ መሣሪያዎቻችንም - እነዚህ ሁሉ እግዚአብሔር አስቀድሞ የወሰናቸው ናቸው። ሁልጊዜ ስለምንማር አግረ መንገዳችንን ሌሎች ነገሮችን ልናገኝ እንችላለን፤ ይሁን እንጂ መንገዱ የእርሱ መንገድ ነው። ሕይወታችንን ዘወር ብለን ስንመለከት፣ ዝቅ ብለን በመጐንበስ ሁሉንም ነገር እግዚአብሔር ያዘጋጀው መሆኑን በትሕትና እንገልጻለን። አንድ ነገር አጥተናል ብለን መፍራት አስፈላጊ አይደለም። እንዲህ ያለውን የልብ ሁኔታ ማግኘቱ፣ ያ እውነተኛ ዕረፍት ነው።

እግዚአብሔር የሚሠራ አምላክ ነው፤ ሥራውን የጀመረውም ከብዙ ዓመታት በፊት ነው። የተለየ ዐይነት ባሪያ ሲያስፈልገው፣ ወይም ቤተ ክርስቲያን ልዩ ዐይነት ርዳታ ሲያስፈልጋት፣ እግዚአብሔር ለዚህ ሁሉ ተዘጋጅቶ ነበር። ድንገተኛ ነገር ከቶ አጋጥሞት አያውቅም። በልጆቹ ታሪክ ውስጥ እርሱ የሌለበት የለም። እያንዳንዳችን ለአንድ ደቂቃ ያህል ካሰላሰልን፣ "በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ጸጋው ተከትሎኛል" እንላለን። የጳውሎስ ቃሎች፣ ከሌላ ጋር በተያያዘ ሁኔታ አገልግሎት ላይ የዋሉ ቢሆኑም፣ ስለ እግዚአብሔር መግቦት ያለውን ዝንባሌ ውጤታማ በሆነ መልኩ አሳጥረው እንዲህ ያቀርቡታል፤ "እያንዳንዱ በተጠራበት መጠራት እንደዚሁ ይኑር" (1ቆሮ

7፥20)፡፡ የእግዚአብሔርን ዐላማ ስናይ፣ እንዲህ ያሉት ቃሎች ከፍ ያለ ትርጉም ይኖራቸዋል፡፡ እግዚአብሔር እያንዳንዳችንን ጠርቶናል፤ እርሱ አስቀድሞ ላወቀው ተግባርም እያዘጋጀን ነው፡፡ ጳውሎስ በሌላ ቦታ እንዲህ ይላል፤ "ነገር ግን ስለ እርሱ በክርስቶስ ኢየሱስ የተያዝሁበትን ያን ደግሞ እይዛለሁ ብዬ እፈጥናለሁ"፡፡

## የእውነት መንፈስ

በመጨረሻ፣ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥራ መጠነኛ የሆነ ነገር እናገራለሁ፡፡ በተለይ የጳውሎስን አገልግሎት አስመልክቶ ሐተታ ባቀረብንባቸው ቀደም ባሉት ምዕራፎች ላይ፣ ስለ መለኮታዊ ነገሮች መገለጥ አስፈላጊነት አዘውትረን ተናግረናል፡፡ በተደጋጋሚ የእግዚአብሔርን ዐላማ፣ የክርስቶስን ማንነትና የክርስቶስን ሥራ፣ የክርስቶስ አካል የሆነችውን ቤተ ክርስቲያንን ማየት በጣም አስፈላጊ ነው ብለናል፡፡ አንባቢ (አንዳንድ አንባብያን)፣ ከእነዚህ ነገሮች አንዱን ወይም ሌሎችን አስመልክቶ፣ "ያን ነገር አላይም፡፡ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ምን ትመክሩኛላችሁ?" ብሎ ለመጠየቅ ይገፋፋ ይሆናል፡፡

ለመልሱ ወደ እውነት መንፈስ ማመልከት እችላለሁ፤ እርሱ በቅርብ ያለና ማንነትም ያለው አካል መሆኑን በማስታወስ፣ እንዲያውም አሁን በልቦናችን ውስጥ የሚኖር መሆኑን፣ በሚያስፈልገንም ሁሉ እያንዳንዳችንን ሊረዳን ዝግጁ መሆኑን ልብ እንድንል አመለክታለሁ፡፡ ሐዋርያው ዮሐንስ እንደሚነግረን፣ ደቀ መዛሙርት እጅግ ግራ ተጋብተው በነበሩበት ወቅት፣ ስለ እርሱ ለመመስከርና ወደ እውነት ሁሉ እነርሱን ለመምራት መንፈስ ቅዱስ እንደሚመጣላቸው ኢየሱስ አረጋግጦላቸው፡፡

መለኮታዊ ነገሮችን ለልባችን በመነሻነት ለመግለጥም ይሁን፣ ወይም እነዚህ መለኮታዊ ነገሮች የእኛ ከመሆናቸው በፊት ተከትለው መምጣት ስላለባቸው እርምቶች ግንዛቤ ለማግኘትም ይሁን፣ በድካማችን ጊዜ ወደሚደርስልን ቸር አጋዥ በተደጋጋሚ መመለስና መቅረብ ያለብን መሆኑን ማመን አለብን፡፡ መንፈሳዊ እውነታዎችን ማየት የምንችለው እርሱ በሚያደርገው መገለጥ ብቻ ነው፤ ወደ እነዚህ እውነታዎች መግባት የምንችለውም በርሱ ፍቅር በተሞላበት እርምት ነው፡፡ በመጀመሪያው (በመገለጥ)፣ ወደ እድገት የሚያመራውን መንገድ ያመለክታል፤ በኋለኛው (በእርምት)፣ ወደ እድገት ጎዳና ይመራናል፡፡ የመጀመሪያው መሠረት ነው፤ ኋለኛውም ለዕላይ መዋቅር ነው፡፡ ያለ መንፈስ ቅዱስ መገለጥ በቀር፣ የተያዘውን ጉዳይ መጀመር አንችልም፤ ደግሞም ያለ





መንፈስ ቅዱስ እርምት (ተግሣፅ) መጨረስ አንችልም፡፡ እነዚህ ሁለቱ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ገጽታዎች እኩል አስፈላጊ ናቸው፤ በመሆኑም ስሁለቱም በእርሱ (በመንፈስ ቅዱስ) ላይ በርግጥ መተማመን እንችላለን፡፡

አብ ዕቅድን አወጣ፤ ወልድ ፈጸመው፤ ወልድ የፈጸመልንን ለእኛ የሚገልጥልን መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ወልድ "ተፈጸመ" ባለ ጊዜና በግርማው ሞገስ በቀኝ በኩል ሲቀመጥ፣ የወልድ ሥራ የተፈጸመ መሆኑን እንቀበላለን፡፡ ነገር ግን አብ የሰጠውን ዐደራ ወልድ የፈጸመው መሆኑን የማንጠራጠር ከሆነ፣ ታዲያ ወልድ የሰጠውን ሥራ መንፈስ ቅዱስ አይፈጽምም ብለን ለምን እንጠራጠራለን?

የወልድ ሥራ እንደ አብ ሥራ ሁሉን አካታች ነው፡፡ ከዚያ ቅንጣት እያልፍም፤ ቅንጣት ያህልም አይቀርም፡፡ የአብ ሥራ ትልቅ እንደ ሆነ ሁሉ፣ የወልድ ሥራም ትልቅ ነው፤ የወልድ ሥራ ትልቅ እንደ ሆነ ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ ሥራም እንደዚሁ ትልቅ ነው፡፡ በወልድ ለእኛ ያልተፈጸመ ቅንጣት ሥራ እንኳ በኛ ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ የሚፈጸም ቅንጣት ሥራ አይኖርም፡፡ በክርስቶስ ያለው የመንፈሳዊ እውነታ ሙላት በክርስቶስ መንፈስ በኩል ለእኛ ያስተላልፍልናል፡፡ ስለ ራሱ ኢየሱስ "እኔ እውነት ነኝ" አለ፤ ስለ መንፈስ ቅዱስም "ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል" አለ፡፡ ሙሉ ወደ ሆነው መንፈሳዊ እውነታ የመምጣቱ ጥያቄ ያረፈው፣ በእኛ ላይ ሳይሆን፣ በመንፈስ ቅዱስ ላይ ነው፡፡ የእግዚአብሔር የሆነው የመንፈስ ቅዱስ ፍጹም ታማኝነት እንጂ፣ የእኛ ዐቅም ወይም ችሎታ ጉዳይ አይደለም፡፡ ወልድ ለእርሱ (ለመንፈስ ቅዱስ) ዐደራ በሰጠው ሥራ ሁሉ እምነት ሊጣልበት የሚችል ነውን? በእርሱ ላይ መታመንን መማር አለብን፡፡ የመማሩ ጉዳይ ሁለት አቅጣጫ ያለውን ሥራውን ያካትታል፡፡ ይህም የመጀመሪያው የመለኮታዊ እውነታ ባሕርይና ልክ መገለጥ ሲሆን፣ ሁለተኛው እርሱ ወደ ገለጠው ወደ እያንዳንዱ ቅንጣት እውነታ ሁሉ እኛን የማምጣቱ ጉዳይ ነው፡፡

ዙሪያችንን ስንመለከት፣ ብዙ ክርስቲያኖች አሳዛኝ የሆነ የዕጦት ገጠመኝ እንዳላቸው ሳናስተውል አናልፍም፡፡ በሕይወታቸው ውስጥ ሙላትን የሚያሳይ አንዳች ነገር የለም፡፡ ለሌሎች ማከፈል ቀርቶ፣ ለራሳቸው ፍላጎት የሚሆን በቂ የሆነ ነገር የላቸውም፡፡ ለምን ድኾች ሆኑ? የመንፈስን ተግሣጽ ባለማወቃቸው ነውን? መዝሙረኛው፣ "በጭንቀቴም አሰፋህልኝ" ይላል (መዝ. 4፥15)፡፡ የብርቱ ተጽዕኖ ሁሉ ዐላማ ሰፍቶ መገኘት ነው፡፡ ያዕቆብ በመልእክቱ ላይ ተመሳሳይ ነገር ይናገራል፤ "እግዚአብሔር በእምነት ባለ ጠጎች እንዲሆኑ

ለሚወዱትም ተስፋ ስለ እርሱ የሰጣቸውን መንግሥት እንዲወርሱ የዚህን ዓለም ድሆች አልመረጠምን?" (ያዕቆብ 2፥5)፡፡ የጊዜያዊ ድኽነት ዐላማ ዘላላማዊ ብልጽግና ነው፡፡ እግዚአብሔር ጭንቀትና ድኽነት በከንቱ እንዲደርሱ ከቶ አላቀደም፡፡ ዐላማው ጭንቀት ሁሉ ወደ እድገት፣ ድኽነትም ሁሉ ወደ ብልጽግና እንዲያመራ ነው፡፡ ለሕዝቡ የእግዚአብሔር ግብ የማያቋርጥ ችግር ወይም ማብቂያ የሌለው ድኽነት አይደለም፡፡ ችግርና ድኽነት ከቶ ግቦች አይደሉምና፤ ግን የእግዚአብሔር ግብ መንገዶች ብቻ ናቸው፡፡ ችግር የእድገት ጎዳና፣ ድኽነትም የብልጽግና ጎዳና ነውና፡፡

የራእይ ራእይ ምዕራፍ 21 ደግማችሁ አንብቡ፡፡ ሥዕል እዚያ ታገኛላችሁ፡፡ በዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ ላይ ብዙ ጊዜ አጥፍታችሁ ትርጉሙን የምትረዱት በጥቂቱ ሊሆን ይችላል፤ ይሁን እንጂ ያ ምዕራፍ በብዛት ስለተትረፈረፈ ሀብት፣ ይህች ምድር ከቶ አይታው ስለማታውቀው ክብር፣ በሰሎሞን ዘመን እንኳ ስላልነበረው ክብርና ሙላት እንደሚናገር ሳትረዱ አትቀሩም፡፡ የምድር መንገዶች በወርቅ ያማሩት መቼ ነበር? ይህች ምድር ብርሃን እንዲበራላት ፀሐይ ያላስፈለጋትስ መቼ ነበር? እንዴት ያለ ሀብት ነው! እንዴት ያለ ደማቅ ውበት ነው! ምድራዊ ግዛት ከቶ እንደ ዐዲሲቷ ኢየሩሳሌም የበለጸገና ወይም ያማራ ሆኖ አያውቅም፡፡ እንዴት ያለ ስፋት ነው! በምድር ላይ አንዲት ከተማ እንኳ የዚህን አንድ መቶኛ ደረጃ አግኝታ ታይታ አትታወቅም፡፡ ድል የሚነሣ ሁሉ እነዚህን ነገሮች ሁሉ እንደሚወርስ ተነግሮናል!

በዐዲሲቷ ሰማይና በዐዲሲቷ ምድር ላይ፣ ስለ እግዚአብሔርና ስለ በጉ ስናነብ በዚያ ላይ ስለ መንፈስ ቅዱስ ለምን አልተወሰም? ብለው አንዳንዶች ጠይቀዋል፡፡ በርግጥም መልሱ እንደዚህ ነው፡- ዛሬ ክርስቶስ ሥራውን እንደ ፈጸመ ሁሉ፣ የክርስቶስ ሥራ ውጤትም በቤተ ክርስቲያን እንደሚታይ፣ በዚያን ጊዜም መንፈስ ቅዱስ ሥራውን ይፈጽማል፤ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ውጤትም በዐዲሲቱ ኢየሩሳሌም ይታያል፡፡ በዚያ ያለው ሁሉ አማናዊ ነው - ይህም መንፈስ ቅዱስ ለመፈጸም የመጣው ሥራ ሁሉ የተሟላ ከንውን ነው፡፡ ዛሬ ቤተ ክርስቲያንን ስትነኩ፣ ክርስቶስን ትነካላችሁ፤ ይሁን እንጂ ይህኛውም እንደዚያኛው እውነት ነው፤ በዚያ ያላችውን ከተማ ስትነኩ፣ የክርስቶስን መንፈስ ትነካላችሁ፡፡ በዚያ ቤተ ክርስቲያን በሰባት ዕጥፍ ሙላቱ በእግዚአብሔር መንፈስ ትሞላላች፤ በዚያ እንደ ጌታዋ ቅዱስ ስለምትሆንም፣ እንደ ከተማ፣ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ሙላት በራሷ ላይ ትገልጣለች፡፡





ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን ከዚያ ግብ እንዴት ትደርሳለች? ከጭንቀት ወደ መስፋት፣ ከድኽነት ወደ ብልጽግና መንገድ በመጓዝ ብቻ ነው፡፡ በጭንቀት በኩል ወደ መስፋት ስንል ምን ማለት ነው? ብላችሁ ትጠይቃላችሁ፡፡ ሦስት ወደ እቶን እሳት ተጣሉ፤ ግን ሦስቱ አራት ሆኑ፤ ይህ በጭንቀት በኩል መስፋት ነው፡፡ አንዳንዶች፣ ከሦስቱ ይልቅ በተወሰነ እቶን እሳት ውስጥ በመግባታቸው መምለጫ መንገድ ይፈልጋሉ፤ ሌሎች ደግሞ ማምለጫየለሽ መሆንን ይቀበላሉ፤ ይህን ሁኔታ በመቀበልም ለአራተኛው አካል ቦታ ያዘጋጃሉ፡፡ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ከእግዚአብሔር እንዲለዩን መፍቀድ ሳይሆን፣ በእርሱ ውስጥ እያለን እንዲዘጋብን እንዲያደርጉ መፍቀድ ነው፤ በጭንቀት ውስጥ መስፋት ማለት ይህ ነው፡፡ ለጳውሎስና ለሲላስ የእስር ቤቱ በሮች ሲዘጉ ዓለምን ወደ ውጭ፣ እግዚአብሔርን ወደ ውስጥ ያደርጋሉ፤ በመሆኑም የታሰሩበት እስር ቤት መቀፍደጃ ከመሆን ይልቅ ወደ ከፍተኛ ሙላት አሻገራቸው፡፡ እግዚአብሔር በኢዮብ ላይ ተደራራቢ መከራ እንዲደርስበት ፈቀደ፣ ይሁን እንጂ መከራዎቹ ወደ እግዚአብሔር ግብ ገፋፉት፡፡ ለዮሐንስ የተገላው ጌታ ራሱ፣ በምስክርነት ደሴት ላይ በሩን ከፍቶ የነገሮችን ሁሉ ፍጻሜ አሳየው፡፡ አንዳንዶች በጭንቀት አማካይነት ከእግዚአብሔር ግብ ይደርሳሉ፤ ሌሎች በጭንቀት ውስጥ ከሕይወት መጨረሻ ላይ ይደርሳሉ፡፡ አንዳንዶች በችግር ውስጥ ሕይወታቸው ያልፋል፤ ሌሎች ደግሞ በችግር ውስጥ የሕይወትን ሙላት ያገኛሉ፡፡ አንዳንዶች ፈተናዎች ሲደርሱባቸው ያጉረመርማሉ፤ በመከራዎች ውስጥ የሚያተርፉት ውስንነትን፣ ገደብንና ሞትን ብቻ ነው፤ ሌሎች በመከራዎች ውስጥ እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ፣ በእነዚህ መከራዎችም ውስጥ የመስፋትን፣ የነጻነትንና የሕይወትን ሙላት መንገድ ያገኛሉ፡፡

ብዙዎች ክርስቲያኖች ድኾች ከመሆናቸው የተነሣ የራሳቸውን ፍላጎት ለማሟላት እንኳ በቂ ነገር የላቸውም፡፡ ርዳታ ለማግኘት ወደ እነርሱ ለሚሄዱ ይብላኻላቸው! ሌሎች ክርስቲያኖች በጣም ባለጠጋዎች በመሆናቸው ሀብታቸውን መገመት አትችሉም፡፡ እነርሱ ያላለፉበትን መከራ ፈልጋችሁ ማግኘት ከቶ አትችሉም፤ እነርሱ ርዳታ ማድረግ ያልቻሉበትን ሁኔታ ፈልጋችሁ ማግኘት አትችሉም፡፡ ችግር ገጥሞአቸው ወደ እነርሱ ለርዳታ ለሚሄዱት ሁሉ አያሌ ሀብት አላቸው፡፡ ብዙ ክርስቲያኖች ንብረታቸውን ወደ አካል አዘው ትረው በሚያፈሱት ወገኖች በመገልገላቸው የለየላቸው ችግረኞች አይሆኑም፡፡ እንዲህ ያሉት ክርስቲያኖች ለሌሎች አማኞች የቱን ያህል ባለውለታኞቻቸው እንደ ሆኑ የሚያውቁት በመጠኑ ነው፤ ከእነዚሁ ባለውለታኞች በአንዳንዶቹ ላይ ንቀት ሲያሳዩባቸው ሊፈተኑ ይችላሉ፡፡ በጉዞ ላይ ያለ አንድ ወዳጅ መጥቶ

ምግብ ቢፈልግ፣ ለእርሱ አንድ ነገር ይሰጣው ዘንድ ጎረቤታችንን እንድንጠይቀው ጌታ ይፈቅድልናል፤ ይሁን እንጂ፣ "እናንተ የሚበሉትን ስጧቸው" ሊለን ይችላል።

መንፈሳዊ ድኽነትና መንፈሳዊ ችግር፣ ሁለቱ የቤተ ክርስቲያን ዐቢይት ችግሮች ናቸው፤ ይሁን እንጂ ድኽነት ውጤት እንጂ ሳቢያ (መነሻ) አይደለም፤ ችግርም ውጤት እንጂ ሳቢያ (መነሻ) አይደለም። የድኽነትና የችግር ሳቢያ (መነሻ) የመንፈሳዊ እርምት ዕጦት ነው። ባለጠጋ የሆኑትና የሰፉት መንፈሳዊ እርምትን ተመክሮአቸው ያደረጉ እነርሱ እና እነርሱ ብቻ ናቸው። በጥልቅ ውሆች ውስጥ ነበሩ፣ ከእግዚአብሔርም ጋር መንፈሳዊ ታሪክ አላቸው፣ ምክንያቱም ለአካሉ ሲሉ ተሠቃይተዋልና። ሕመማቸው፣ የቤታቸው ችግሮች፣ ጉዳቶቻቸው ሁሉ - ክርስቶስ በሕዝቡ ዘንድ ደምቆ እንዲታይ ነው። በአንጻሩ ግን፣ እንዲህ ያለውን እርምት ችላ በማለት፣ የብልጽግናን መንገድ በመፈለግ፣ የምቾትንና ተደላድሎ የመቀመጥን ሕይወት የሚመርጡት፣ ችግር የነገሠባቸውና በድኽነት የተጐሳቆሉ ናቸው። ድኾችና ችግረኞች ርዳታ ለማግኘት ወደ እነርሱ የሚመጡት በከንቱ ነው። የተጥለቀለቀ ሀብት የላቸውምና።

ስብከት ዝም ብሎ ስብከት ይመስላችኋልን? አገልግሎትስ ዝም ብሎ አገልግሎት ይመስላችኋልን? እንዲህ እንዳልሆኑ ግን እመኑኝ። እግዚአብሔርን ማገልገል እንዲያው የቃላት ወይም የሥራ ጉዳይ አይደለም፤ የቱን ያህል በመንፈስ ቅዱስ እንደ ተሠራችሁ የሚያሳይ ነው እንጂ። መንፈስ ቅዱስ እንዲያስጨንቃችሁ ከቶውኑ ካልተፈቀደለት፣ በሕይወት ዘመናችሁ ሁሉ ድኽነት እንዳይለያችሁ ትሆናላችሁ። ለራሳችሁ ሳይሆን ለሌሎች፣ ከጌታ ሙላትን ማግኘት የቱን ያህል በረከት እንደ ሆነ ሳትማሩ ትቀራላችሁ። ያም አገልግሎት ነው።

መገለጥ ተግሣጽን (እርምትን) ይጠባበቃል። የመንፈስ ቅዱስን ተግሣጽ መቀበላችን በክርስቶስ ያሉት እውነታዎች ለእኛ ይገለጡ ዘንድ በሩን ለመክፈትና እኛን ወደ እውነታዎቹ ለማምጣት ያስችላል። ከዚያ ተግሣጽ መራቅ ይህን እንዳይሠራ ያደርገዋል። በየቀኑ እግዚአብሔር እኛን ለማስፋት ይፈልጋል፤ ይሁን እንጂ ችግሮች ሲከሠቱ ከእነርሱ እንሸሻለን፤ ፈተናዎች ሲመጡም ማምለጫ መንገድ እንፈልጋለን። አቤት፣ የቱን ያህል ተጎድተናል! የእግዚአብሔር ሕዝብስ የቱን ያህል ተጎድቶአል! ርግጥ ነው፣ ሆን ብለን ከጌታ ፈቃድ ውጭ ከወጣን ከመለኮታዊ ተግሣጽ የምናመልጥበት መንገድ አይኖርም፤





ያ እኛን ለማስተካከልና ለማዳን የታቀደ የተለየ ነገር ነው። ከዚያ ማምለጥ አንችልም፤ ይሁን እንጂ ወደ መንፈስ ቅዱስ ገንቢ ተግሣጽ ብንቀሳቀስ ከዚያ ማምለጥ እንችላለን። በአንጻሩ ግን፣ ለእርሱ አሠራር ራሳችንን አሳልፈን ብንሰጥ በእጅ ይዞ ይወስደናል፤ ወደ እግዚአብሔር ግብም ያመጣናል። "ጌታ ሆይ፣ እስከ መጨረሻው ጠብታ የምትሰጠኝን ጽዋ እጠጣለሁ፤ መስቀሉን እሸከማለሁ፣ ከሐሞት ወይም ከሆምጣጤ ለማምለጥም እልሻም ለማለት ፈቃደኞች ነን?" በሕዝቡ ውስጥ ፈጽሞ ተቀድሶ (ተለይቶ) መገኘት፣ ያ ሁኔታ እርሱ በልቡ ያቀደውን ሁሉ ለማድረግ እግዚአብሔርን ያስችለዋልና! ያ ሁኔታ የዐዲሲቷ ኢየሩሳሌም ሙላት ወደ ሆነው ወደ ሙላት ይመራል። በዚያች ከተማ ውስጥ በእቶን እሳት የጠራ እንጂ ያልጠራ ወርቅ አይኖርም፤ በእሳት ውስጥ ያላለፈ የከበረ ድንጋይ አይኖርም፤ በሥቃይ ውስጥ ያለፈ እንጂ ሥቃይ ያልደረሰበት ዕንቍ አይኖርም።

ጴጥሮስ ስለ ዮሐንስ ኢየሱስን "ይህስ እንዴት ይሆናል?" በማለት በጠየቀው ጊዜ የጌታችን መልስ ምን ነበር? ...... "እስከመጣ ድረስ ይኖር ዘንድ ብወድስ ምን አግዶህ?" *እስከመጣ ድረስ!* የዮሐንስ የተጀመረው የእውነት መንፈስ አገልግሎት፣ ታሪኩ እስከሚፈጸም ድረስ ይቀጥላል፤ የሚያቆመው ነገር አይኖርም። እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያኑ ያለው ዐላማ ይፈጸማል፤ ከቶ ሊሰናከል አይችልም። ለባልዋ ተሞሽራ ዝግጁ እንደ ሆነችው ሙሽራ፣ የቅድስቲቱ ከተማ ራእይ፣ ሳይታገድ እውን ይሆናል፤ እኛም እናየዋለን። "እስከመጣ ድረስ" ተብሎአልና ማንም ሊነካ አይችልም፤ በመንግሥት ሰማይ ላይ የተወሰነ (የማይለወጥ)ነው።

ታዲያ፣ እንግዲህ እንደ ፈቃዱ ሕይወታችንን ይመራ ዘንድ ራሳችንን በአባታችን አስተማማኝ እጆች ላይ ማድረግ የለብንምን? የመንፈስ ቅዱስ የህዳሴ ሥራ በእኛ ውስጥ በፍጹምና በአስተማማኝ ሁኔታ እውን የመሆኑ ጉዳይ፣ በተወደደው ልጁ ለእኛ ከተፈጸመው የቤዛነት ሥራ ያላነሰ መሆኑን ማየቱ የእርሱ ተግባር ነው።